# የሐይማኖት ተቋም ያልሆንነው ለምንድን ነው?

ከሶስት ወራት መጥፋት በኋላ ይመስለኛል፡ እንደገና፡ ወደ መድረክ መመለሴ፡ ደስታ ይሰማኛል። እኔና ሸኮኮዎቹ፡ ከባድ ጊዜ አሳልፈናል። በርግጥ፡ አሁን ዘና ብያለሁ፡ ወደ አገልግሎት መግባት፡ የበለጠ ፍላጎት ጨምሮብኛል። ቀጣይ ሳምንት እርብ ማታ፡ በዚሁ—ቤተ ክርስትያን፡ ሪቫይቫል ለማድረግ እየተዘጋጀን እንገኛለን። እና እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ አዲስ ነገር ይዤ መጥቻለሁ... ጌታ የተለየ እና አዲስ የአገልግሎት አቅጣጫ ቃል ገብቶልኛል። ይህን ለማድረግ ከወደደ፣ በሚቀጥለው ሳምንት አዲሱን አገልግሎት—አስቀድመን በዚሁ ቤተ ክርስትያን፣ ለማስጀመር፡ ተሰፋ አደርጋለሁ።

2 ከዚህ በኋላ፡ መጪው ጥር በአውስትራሊያ እና በኒውዚላንድ ብቻ እንጂ፡ ሌላ የታቀደ ሰብሰባ የለኝም። ወንድም ኦሰቦርን ከተወሰነ ጊዜ በፊት እዚህ በቱልሳ ውስጥ፡ ቃል የገባሁለትን የጋራ ሰብሰባ ላይ ኑ እያለን ነው። ምናልባት ትንሽ ቆይተን፡ ምን እንደሚሆን አናውቅም።

3 ወንድም ጀፈሪሰም፡ ለሰላምታ እጅህን መጨበጤ፡ ልጅህም መሳርያ እየተጫወትክለት፡ ሲዘምር ማየቴ፡ እጅግ አስደሰቶኛል። አባት እና ልጅ፡ ደስ ትላላችሁ። ደስ አይሉም? "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው።" ትክክል ነው፡ አቶ፡ ጌንተር፡ እውነት እንደሆነ፡ ሁለታችሁም—ታውቃላችሁ። "ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፡ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።" በትክክል። አንዳንዴ ከመንገድ ሊወጣ ይችላል፡ ከእርሱ ግን አይለይም። አያችሁ? ዘወትር—አብሮት ይኖራል። እንዲሆንላችሁ ፈልጋችሁ በልጅነት የምትሰጡት ትምህርት፡ በትክክል—አብሮት ይዘልቃል። አሁንም፡ ይህ ነው...

4 ወንድም ጀፍረይሰ ጋር ውጪ ተገናኝተን፡ "ወንድም ጀፍረይሰን፡" እንዲህ አልኩት... በእንግድነት የሚመጡ ወንድሞች ማየት፡ እንደሚያስደስተኝ፡ የምታውቅ ይመስለኛል፡ እንዳንተ ያለ ወንድም መምጣት ግን ልዩ ምሽት ያደርገዋል! ይህ ምሽት ከሪቫይቫሉ በፊት፡ ወደ ቤተ ክርስትያን የመጡ የወዳጆች ምሽት ሆኗል። በዚህ ምሽት... ከዛሬ ማታ ጀምረን፣ ነገ ጠዋት፣ እስከ ነገ ማታ ድረስ፣ በዚሁ ቤተ ክርስትያን የምናምናቸው ነገሮችን፡ ለመከለስ ያክል—እንደ ርዕስ እንወስዳለን። አንዳንድ በጣም እንግዳ፡ ግን በአንዱም በሌላም መንገድ በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው፡ ያልተለመዱ እምነቶች አሉን። የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ትምህርቶችም ናቸው።

5 ስለዚህ አሁን፡ ከሌላ የሐይማኖት ተቋም የመጣችሁ—ምናልባትም፡ ትምህርታችን ጋር የማትስማሙ፡ ዛሬ ግን ከእኛ ጋር ያላችሁ፣ ወንድም እና እህቶች፣ እንኳን ደህና መጣችሁ ነጻነት እንዲሰማችሁ እንፈልጋለን። አያችሁ፡ እስከ ጥግ ድረሰ ነጻነት ይሰማችሁ። የዛሬ ጉዳይ ግን... ከባድ ማድረጋችን አይቀርም። ስለዚህ፡ እኔ የምለው ነገር ካልተሰማማችሁ፡ አትጨነቁ፡ እኔ ቼሪ ፓይ ሰበላ የማደርገውን ዓይነት ነገር አድርጉ። ቼሪ ፓይ፡ የዘወትር

ምርጫዬ ነው፡ እና ቼሪ ፓይ ሰበላ፡ እየበላሁ... ፓዩን እየበላሁት፡ ፍሬ ከአገኘሁ፡ ፓዩን አልጥለውም። ፍሬውን ጥዬ—ፓዩን መብላቴ እቀጥላለሁ። የዶሮ ስጋ ስመገብም፡ እንዲሁ። እናንተም ሁላችሁ፡ የዶሮ ስጋ ወዳጆች፡ ናችሁ። አጥንቱ ጋር ስትደርሱ፡ መመገባችሁን አታቆሙም፡ አጥንቱን እያገላበጣችሁ ስጋውን ትበሉታላችሁ። አሁንም፡ እኔ የምናገረው ነገር ስምታችሁ፡ ከከበዳችሁ፡ ዛሬ ማታ... ማለት ያለባችሁ፡ ይህ ነው፡ "ከዛሬ፡ እስከ—ሶስተኛው ቀን ድረስ... የቤተ ክርስትያን አስተምህሮ፡ የሚያምኑት ነገር፡ መከለሳቸው የማይቀር ነው። እኔ ዝም ብዬ ምንም ሳላደርግ—እስኪጨርሱ ድረስ፡ ልከታተል በሉ።"

6 አንድ ሰው እንዲያምን ማድረግ የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ፡ ነገሩ ትክክል እንደሆነ እስኪያውቁት ድረስ እንዲቀርቧችሁ ጠንክራችሁ በመስራት ነው። ጠበቅ የሚልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። ለምሳሌ አብሮኝ የነበረ ጓደኛዬ፡ አቶ፡ ዉድ፤ ሚስማሩን እስከ ግማሽ ድረስ መትተህ ግድግዳውን ከተውከው፡ ይላላል፡ ምንም ሳይቆይ ንፋስ መጥቶ ይወስደዋል። ስለዚህ በደንብ በመምታት፡ ጠብቆ እንዲገባ ማድረግ አለብህ። እንዲህ በማድረጌ ምናልባት በአንዳንድ በኩል፡ ወይም እዚህ ያላችሁ እንግዶችን የሚያሳዝን ነገር ካደረግኩ፣ የምናምነው ነገር ለዚህ ቤተክርስትያን በማሳሰብ ወደ ቤት ለማድረስ መሞከሬ ነው እንጂ። እናንተን—ለማሰቀየም አይደለም። ይሄን በደንብ የተረዳችሁ፡ ሁላችሁ "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤውም "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] እሺ እንግዲህ። ጥሩ—ነው። ይሄን እና ሌላ—ሌላው ነገር... ከዚህ አንሱልኝ። ምናልባት ወደፊት፡ እኛ የምናምነው ነገር፡ ወይም እኛ የቆምንለት ዓላማ፡ ማወቅ የሚፈልጉ ቢመጡ፣ ቅጂዎቹ እራሳቸው ስለሚናገሩ፡ አሁን እየተቀዱ ይገኛሉ። ምክንያቱ እኛ እያለፍን—ሌሎች ትውልዶች ስለሚተኩ፡ ሳናቋርጥ የምንተጋበት ጉዳይ ነው። ስለዚህ ዛሬ የምንፈልጋቸው ጥቂት አስተምህሮዎች ብቻ እንጂ—የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ሁሉ፡ መሸፈን አንችልም። አሁንም፡ እሮብ ምሽት፡ የሚጀምር፡ ቢሆንም...

7 ሰኞ፡ እና ማክሰኞ፡ ለጸሎት፡ እወጣለሁ፡ እናንተም ለፈውስ ጉባኤ ተዘጋጁ። በሰልክ፡ ወይም በተመቻችሁ መንገድ መከታተል ትችላላችሁ፡ በተጨማሪም በዚህ ሪቫይቫል፡ መጋበዝ የፈለጋችሁት ሰው ሁሉ ጋብዙ። በችኮላ እንዳይመጡ ብቻ ንገሯቸው፡ ማለት፡ "ዛሬ ማታ፡ ወይም ነገ ማታ፡ ይጸለይልኛል። እና ቶሎ ብዬ፡ ልድረስ... " ብለው እንዳይቸኩሉ። እንደዛ አይሁን። ጊዜ ወስደን የእግዚአብሄር ቃል እንድንሰብክ፡ ዲያብሎስን መፈናፈኛ በማሳጣት እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ እንፈልጋለን ስለዚህ መጥታችሁ በርጋታ ታዳምጣላችሁ። ከዚያ በኋላ እስክታምኑ ድረስ፡ እምነታችሁ እስከ ጥግ ድረስ ማሰራት ስትጀምሩ፡ ከዚያ በኋላ ንቃተ ህሊናችሁ ይበረታል፡ የእግዚአብሄር እምነትም ይደግፋችኋል። ከዚያ በኋላ ትሄዳላችሁ። እሺ?

ምክንያቱ፡ እምነታችሁ ብቻውን እምብዛም አይጠቅምም። ንቃተ ህሊናችሁ ከእምነታችሁ ጋር በአንድ መንገድ መራመድ አለበት፣ ከኋላው የእግዚአብሄር እምነት ተከትሎ መጥቶ ያጸናላችኋል። አያችሁ? እምነታችሁ ብቻ ከሆነ፡ ግን፡ "ኦህ፡ አሁን፡ ገና ገባኝ!" ንቃተ ህሊናችሁም፡ ወደ ኋላ ተስቦ፡ "በእኔ ይሰራ ይሆን፡" ሊል ይችላል። አዎን ወድያው፡ ላይሰራ ይችላል። አያችሁ? ቀኑ ትክክለኛ የፈውስ ጉባኤ እንዲሆን ፈልገናል። ስለዚህ ማንም ሰው ወደ አዳራሹ፡ ለፈውስ፡ ወደ አዲሱ ጉባኤ፡ ወዘተ፡ ከመግባታቸው በፊት፣ የመጡበትን

ምክንያት በትክክል ተረድተው እንዲገቡ እፈልጋለሁ። ስለዚህ ይሄን አትርሱ፡ መጥታችሁ ጎብኙን፡ በደስታ እንቀባላችሁለን።

8 አስታውሱ አሁን፡ ነገ ጠዋትም፡ የቤተክርስትያን አስተምህሮትን፡ በተመለከተ እንቀጥላለን። ነገ ማታም እንዲሁ። ሁላችሁ ተጋብዛችኋል፡ ሰው ሁሉ መምጣት ይችላል። ሰውን ሁሉ ማስተናገድ ደስታችን ነው። አሁን ግን፡ ዛሬ ማታ፡ የዚህ ጉባኤ አባላት ለሆኑ በዚህ አስተምህሮ ላደጉት ሰዎች፡ በዋናነት—የሚመለከት ይሆናል። ምክንያቱ፡ ወንጌልን ለማስፋት፡ በየሰፍራው ሰንሄድ፡ መሰረታዊ የሆኑ፡ የቃሉ ኢቫንጀሊካል አሰተምህሮቶች ላይ እናተኩራለንና። በዚህ ተበርናክል ውስጥ ግን፡ እ—እንደ—እንደ ቤተ ክርስትያን፡ የራሳችን አመለካከት እና እምነቶች አሉን፣ ዛሬም፡ ትክረታችን በዚሁ ነው።

9 እና ቅዱስ ቃሉን ከማንበባችን በፊት፡ አንድ አፍታ አንገታችንን ዝቅ አርገን እንጸልይ?

10 ሁሉን ቻይ ኃያል አምላክ ሆይ፡ የመጀመሪያ አቶም፡ በአለም ከመታየቱ በፊት፡ አምላክ የነበርህ። አሁንም ፈጽመህ ያው ነህ። አለም ሁሉ በሚጠፋ ጊዜ፡ አቶሞችም ሁሉ በሚያበቁ ጊዜ፡ አምላክ ሆነህ ትኖራለህ። አንተ ከዘለአለም፡ ዘለአለማዊ ነህ። አንተ አምላክ ነህ። የቀናቶች መጀመርያ፡ ወይም የህይወት ፍጻሜ የለህም። ዘለአለማዊ ሆነህ ትኖራለህ። አሁንም፡ አባት ሆይ፡ አንተ ፍጻሜ የለህም፡ እኛ ግን አለንና፡ አቤቱ አምላክ ሆይ፡ መንፈሳችን፡ ዘለአለማዊ ወደሆነው፡ ከዚህ ፈራሽ አካል ወጥቶ፡ ወደ ዘለአለም እንደሚሄድ አውቀናልና አቤቱ መለኮታዊ ምሕረትህ እንለምናለን። ስለዚህ፡ ጌታ ሆይ፣ መደናችንን ለመመርመር፣ በቃልህ ፊት እንዴት እንደቆምን ለማየት እዚህ መጥተናል፣ በልማዶቻችን ውስጥ እንዴት እንደምንኖር ለማየት። በኑራችን አንተን ደስ ማሰኘታችን አለማሰኘታችን ለመመርመር? መንፈሳችን ከመንፈስህ ጋር ይስማማል አይስማማም? ትምህርታችንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ይስማማል ወይ? አባት ሆይ፡ በሚቀጥሉ ሶስት ጉባኤዎች፡ ይህን ጉዳይ፡ በአንክሮት፡ መመርመር ይሁንልን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

11 ፓስተሩን፣ ዲያቆናቱ፣ ባለ አደራዎቹ፣ እና ምእመናን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡትን ሁሉ ባርካቸው። ጌታ ሆይ፡ በቆይታዬ፡ ሰሞቻቸውን እና ከየት እንደመጡ የማላውቃቸው፡ ብዙ፡ እጅግ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ፣ አንተ ግን ስለ ሁሉም በርግጥ ታውቃለህ። አሁንም በዚህ ምሽት፡ ጌታ ሆይ፡ አንዲት ዓላማ ኖሮን መጥተናል፡ ይህም በቃልህ ዙርያ ሕብረት ለማድረግ ነው። እናም በሰላም፡ በንቃት፡ እና እግዚአብሔርን በመፍራት እንድንቀመጥ፡ በቃሉም ህይወትችንን ይመረምር ዘንድ፣ መንፈስ ቅዱስን በህይወታችን ስጠን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

12 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በዚህ ህንጻ ውስጥ፡ ከተለያየ የቤተ ክርስትያን—ሕብረት የመጡ ብዙ ወንድሞች አሉ። ጌታ ሆይ፡ ሕብረት ለማድረግ ስለመጡ፡ ስለነሱ አመሰግንሃለሁ። ምናልባት በትንንሽ የዶክትሪን መርሆች ላንሰማማ እንችላለን። በዋናው አንዱ መርህ ውስጥ ግን፡ በግንባር ቀደምትነት በአንድነት እንደ ወንድሞች ቆመናል። ይህም፡ አምላክ ሆይ፡ አንድነታችንን—ያጠንክርልን፡ የእግዚአብሄር የጸጋ እና የፍቅር ማሰርያ… በእኛ ላይ ይብዛ። ምክንያቱ፡ ጌታ ሆይ፡ ይህን ስራ ለሰው ከባድ እንደሆነ፡ ተገንዝበናል፡ በውስንነት የምንኖር ነንና፡ ዛሬ ምሽት፡ የነፍሳት መዳረሻ ዘለአለም ነውና። በዚህም ምክንያት መንፈስ ቅዱስ በቀጥታ በቃሉ ላይ እንዲወርድ፣ እንድናውቅ

የሚፈልገንን ሁሉ፡ በራሱ መንገድ ገልጦ እንዲያብራራልን እንጸልያለን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ጉባኤዎቹ... ሶስቱ ጉባኤዎች ካለቁ በኋላም፡ ከሌሎች የእግዚአብሔር መንግስት ዜጎች ጋር፡ በተለየ መልኩ ወደፊት ለመገስገስ፡ እንደ አንድ ቤተ ክርስትያን ልባችንን እና አሳባችንን፣ አንድ በማድረግ፡ ሕብረት ያላቸው ጠንካራ ሆነን መመለስ ይሁንልን።

13 ጌታ ሆይ፣ አሁን ለብዙ ሳምንታት ጥሩ እረፍት ስለሰጠኸኝ፡ በቤተክርስቲያኑ፡ እና እዚህ ባለ ህዝብ ፊት፣ ላመሰግንህ እፈልጋለሁ። በመገኘትህ እና በበረከትህ ምክንያት በዚህ ምሽት አስደናቂ ስሜት እየተሰማኝ ነው። አምላክ ሆይ፡ ህይወቱን ለወንጌል አሳልፎ በመስጠት፡ እሩቅ ለሚሄደው፣ እጅግ እሩቅ እና ጨለማ፡ ጭጋጋማም ወደ ሆኑ ከተሞች፡ ለሚሄደው ወንድም እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ ወንድማችን ጄፍሪስ በሚሄድበት ሁሉ እና ልጁን፡ እና ሚስቱም፡ ባርካቸው፡ ታላቅ እድገትም ስጠው። የወንጌል ብርሃን በሩቅ እና በሰፋት እስኪያበራ ድረስ ጨለማን መግፈፍ ይሁንለት። ስማን፡ አባት ሆይ፡ ይህንን ልመና በልጅህ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም እንለምናለን። ኣሜን።

14 ዛሬ ማታም፡ ከትንሿ፡ የስኮፊልድ መጽሐፍ ቅዱሴ አነባለሁ። በቅርቡ፡ ሃያ-አምስት አመታት አልፏታል። እየደበዘዘኝ መጣ እንጂ፡ አሁንም ማንበብ እችላለሁ። ስለዚህ ማጥናት እንድችል አንድ መነጽር ገዝቼአለሁ፡ እንዴት እንደሆነ፡ ገና ዛሬ ለመጀመርያ ጊዜ ልሞክረው ነው።

አሁን፡ “ቤተክርስትያን የግድ... ” እና የመሳሰሉ፡ ብዙ ርዕሶችን ይዣለሁ፡ ኦህ፡ ጊዜ ካገኘን፡ ብዙ ናቸው። ከእነዚህ አንዱ፡ “ቤተ ክርስትያን ተብለን ለምን ተጠራን? ለምንድነው የሐይማኖት ተቋም ያልሆንነው? የአማኞችን ነፍስ በዘለአለማዊ ደህንነት የመኖር እምነት ለምን—እናምናለን? ሴት ሰባኪዎችን ለምን እናወግዛለን? በመጥለቅ ለምን እንጠመቃለን? እና ቤተክርስቲያን በመከራ ውስጥ ታልፋለች? ” እና ለሚቀጥሉት ጥቂት ምሽቶች፡ ከእነዚህ አስራ አምስት ወይም አስራ ሰምንት ርዕሶች፡ እንወስዳለን።

15 ስለዚህ ዛሬ ምሽት፡ እንደ መነሻ፡ ለመጀመር፡ ጌታ በልቤ ውስጥ፡ እንደ ርዕስ ሰጥቶኛል ብዬ፡ የማስበው... **የሐይማኖት ተቋም ያልሆንነው ለምንድን ነው?** የሚል ይሆናል... ማለት፡ በሐይማኖት ተቋም ያሉ ሰዎች ለመቃወም አይደለም። ከእነርሱ ጋር ምንም ችግር የለብንም፡ ይሁን እንጂ ከሐይማኖት ተቋሞች ጋር ፈጽመን አብረን የማንኳዝበት ምክንያት መግለጽ እፈልጋለሁ። በትንሿ ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ እንደነበርኩ፡ ታውቃላችሁ። እና እስከ ቅርብ ጊዜ፡ ባፕቲስቶች የሐይማኖት ተቋም አልነበሩም፡ አሁን ግን እንደሌሎቹ የሐይማኖት ተቋም እየሆኑ መጥተዋል። እኛ የሐይማኖት ተቋም ያልሆንበት፡ ምክንያት ግን...

16 በርግጥ፡ ድርጅት ነን። ክርስቶስን፡ በአንድነት ለማምለክ—የተደራጀን፡ ሕጋዊ ምዝገባ ተሰጥቶን—የተደራጁ ሰዎች ነን፡ የሐይማኖት ተቋም ግን አይደለንም። የሚገዛን የበላይ አካል የለንም፡ አያችሁ። የሐይማኖት ተቋም አይደለም። በክርስትያን አማኞች መካከል—የሕብረት ድርጅት ነው። ሰዎች ወደዚህ ቤተክርስትያን ይመጣሉ። በህይወት እስካሉ ድረስ፡ በፈለጉት ጊዜ እንደ ቤተ ክርስትያናቸው ይመርጡታል።

17 በዚህ ሁሉ ግን ቢመጡም ከምናስተምረው አስተምህርት ጋር ላይስማሙ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ችግር የለውም። አሁንም፣ አንተ ክርስቲያን እስከሆንክ ድረስ፣ ህብረት አለህ፣ እንደ ሌሎቹ አንድ አይነት እጅ ማውጣት ትችላለህ። አየህ? የውሃ ጥምቀት በጥልቅ ውሃ ነው ብዬ ካመንኩ፡ አንተ ግን በመረጨት ብታምን፡ በዚያም ብትጸና፡ በመካከላችን መግባባት ካለ እንደ ድሮአችን አንድ ነን። ምናልባትም አይን-ለ-አይን ላንተያይ፡ እንችል ይሆናል። ወንድም እህት ሆይ ክርስትያን እስከሆናችሁ ድረስ ግን፡ ኢያችሁ፡ ሁላችሁንም፡ በፍጹም ልብ እንቀበላችኋለን።

18 የሐይማኖት ተቋም የወንድማማች ሕብረት ከፋፋይ ስለሆነ፡ ምንም አይነት የሐይማኖት ተቋም የለንም። አንዳንዶቹ "ይሄ'ኮ፡ የሜቶዲስት ሪቫይቫል ነው። እኛ በዚያ ሪቫይቫል አንሳተፍም፡" ይላሉ። "ይሄ'ኮ፡ የባፕቲስት ነው። እኛ አንሄድም... ሜቶዲስቶች ነን። በዚያ ሪቫይቫል አንሳተፍም ይላሉ።" ወንድሞች ሆይ፡ ክርስቶስ ያለበት ሁሉ፡ እኛም—እንሳተፋለን። ኢብረን መከራን የምንቀበል—የክርስቶስ አካል—ነንና... መደጋገፍ ይገባናል። ዛሬ ግን በየ ቦታው ይሄ ነገር፡ የተለመደ ሆኗል... አሁንም፡ ይህ በእናንተ የታወቀ ይሁን። ክርስቶስ፡ ቤተክርስትያንን፡ የሐይማኖት ተቋም አድርጎ ያደራጀት ዘመን፡ ፈጽሞ አልነበረም።

19 አሁን፡ ነገ፡ ምናልባት ማወቅ ከምትፈልጓቸው ነገሮች፡ መካከል እኔ ከምጠቅሰው ታሪክ፡ ወይም ሌላ ሌላ ነገር ካለ፡ ነገ ማታ እንጠያየቃለን። ርዕሱን ለመጨረስ በቂ ጊዜ አይኖረኝም፡ በአንዱ ርዕስ ሳምንታት ልንፈጅ እንችላለንና፣ እንዲህ ከሆነ ወደ ሌላ ርዕስ ማለፍ አንችልም። ይሁን እንጂ ቦታውን፡ ወይም ሌላ ነገር ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ጠይቁኝ፣ እዚህ ጠረጴዛው— ላይ አስቀምጡልኝ፡ መልሱን እመልስላችኋለሁ።

20 አሁን፡ ካቶሊክ ቤተ ክርስትያን፡ ከጥንት ጀምሮ የሐይማኖት ተቋም የነበረች ቤተ ክርስትያን፡ እና የመጀመርያ የሐይማኖት ተቋም ናት። የመጨረሻው ሐዋርያ ከሞተ በኋላ፡ ከሶስት መቶ አመታት ገደማ በኋላ የተደራጀች ናት። ይህም እውነት ነው። ከጆሲፈስ ጽሑፎች፡ እና ከንቅያ አባቶች ታሪክ፣ እና፡ ኦህ፡ ከብዙ ታላላቅ የታሪክ፣ ሊቃውንት—ማግኘት ይቻላል። ኢያችሁ? በቤተ ክርስትያን ዘመን፡ ካየን... የመጨረሻ ሐዋርያ—እስከሞተበት ዘመን ድረስ፡ ወይም ሐዋርያቶች የነበሩበት ሶስት መቶ አመታትን ጨምሮ፡ የሐይማኖት ተቋም የሆነ ቤተክርስትያን አልነበረም። ስለዚህ ተቋም የሆነች ቀዳሚ ቤተክርትያን ካቶሊክ ቤተክርትያን ናት።

21 የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስትያናት ግን ከሐይማኖት ተቋማት የወጡ የሐይማኖት ተቋም ናቸው። የመጀመርያው ተሐድሶ፡ በሉተር የጀመረ ሲሆን፡ ከሱ በኋላ ዝዊንግሊ መጣ፡ ከዝዊንግሊ በኋላ ካልቪን መጣ፡ ከዚያም በኋላ ቀጠለ። እስከ ዌስሊ ሪቫይቫል ድረስ፡ ከሱ በኋላም አሌክሳንደር ካምቤል፣ ጆን ስሚዝ፣ እና ሌላ-ማን ቀረ፡ ኢያችሁ፡ እንዲህ እያለ ቀጠለ። አሁን ያለን የመጨረሻው እንቅስቃሴ በየደረጃው የሚታይ የጴንጤቆስጤ ዘመን ብቻ ነው።

22 በእያንዳንዱ ዘመንም እግዚአብሔር እንደሰራበት አምናለሁ። አስተውላችኋል፡ ቤተ ክርስቲያን በወደቀች ቁጥር፡ ልክ እንደ ተደራጁ መውደቅ እንደሚጀምሩ? እንዴ ሲወድቁ፡ እግዚአብሄር የወደቀችውን ቤተክርስትያን ፈጽሞ አያነሳትም። በቀጥታ ዘር ወደ መሆን ትወርዳለች። እናንተም...

በታሪክ ውስጥ፡ አንዴ የወደቀች—ቤተክርስትያን፣ በመላው የቤተ ክርስትያን ታሪክ፡ ተቋም በመሆን የወደቀች ቤተ ክርስትያን ተነሰታ—እንደማታውቅ፡ ከታሪክ ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ማምጣት እንችላለን። ባፕቲስት፣ ሜቶዲስት፣ ፕሪሰባይቴሪያን፣ ሉተራን፣ ምንም ይሁን ምን፣ በወደቁ ጊዜ፣ አብቅቷል። ይሄም፡ እውነት ነው። አሁን፡ ይሄን፡ አስቀድሜ—ተናግሬአለሁ፡ በደንብ ጠበቅ ስለምናደርገው፡ ጃኬታችሁን ልበሱ ብያለሁ። አያችሁ? መቼም፡ ተነስታ አታውቅም። አንድ ግለሰብ ተነስቶ ቤተክርስትያንን ሲያደራጅ፡ ጅማሬ ይሆናል።

23 እግዚአብሄርም ከግለሰቦች ጋር እንጂ ከሐይማኖት ተቋሞች ጋር አይሰራም። እግዚአብሄር ከሐይማኖት ተቋም ጋር የሰራበት ዘመን አልነበረም። ሁሌም ከግለሰቦች ጋር ይሰራል። በብሉይ ኪዳን፡ ከግለሰቦች ጋር ሰርቷል። በአዲስ ኪዳንም፡ ከግለሰብ ጋር ይሰራል። በሁሉም ዘመናት፡ ከግለሰብ ጋር እንጂ፡ ከሐይማኖት ተቋም ጋር ሰርቶ አያውቅም። ስለዚህ፡ እግዚአብሄር፡ ከሐይማኖት ተቋም ጋር ጉዳይ ከሌለው፡ እኔ ከሐይማኖት ተቋም ጋር ምን ጉዳይ ይኖረኛል? አሁን፡ የምናገረው ነገር ስለ ተቋሙ ራሱ እንጂ፡ በሐይማኖት ተቋም ውስጥ ስላለ ህዝብ አይደለም፣ የእግዚአብሄር ህዝብ በየሐይማኖት ተቋም ውስጥ ተይዞ ይገኛልና።

24 አሁንም እግዚአብሄር፡ አስቀድሞ ሳያስጠነቅቅ የሚሆን ነገር የለም። እንደዚህ አይነት ነገር አለ ብዬ አላምንም…

25 አሁን በቅርቡ፡ በአብያተ ክርስትያናት ውስጥ፡ የተነሳ ጉዳይ፣ በቅርቡ ስለ ደም ስለ ዘይት፡ ወዘተ ተነስቶ ነበር። ደባዳቤውን ታስታውሳላችሁ "የተወደድክ ወንድም ብራንሃም፡" ወዘተረፈ። እኔ ይህ ነገር የተቃወምኩበት ብቸኛው ምክንያት፡ በቃል ውስጥ ስለሌለ ነው። የሐይማኖት ተቋም የምቃወምበት ብቸኛው ምክንያትም፡ ቃል ውስጥ ስለሌለ ነው። ደግሞም እምነታችን የራሱ መሰረት ሊኖረው ያስፈልጋል። ስለዚህ የሐይማኖት ተቋም መሰረት ማድረግ ካልተቻለ፡ መሰረታችን ከእግዚአብሄር ቃል ማድረግ አለብን። የእግዚአብሄር ቃል፡ ምትክ የሌለው መሰረት ነውና።

26 ስለዚህ የእግዚአብሄር ቃል የሐይማኖት ተቋም የማይቀበል ከሆነ፡ ይልቅ ግን የሚያወግዝ ከሆነ፡ እንግዲያውስ ከቃል ጋር መስማማት አለብን። ቢሾፑ ምንም ቢል፣ ወይም ሌላ ሰው ምንም ቢናገር፣ ሰው ምንም ቢያስብ፣ ጥሩ ሰውም መጥቶ ቢናገር፣ ወይም ማንም ምንም ቢል፣ እንደ እግዚአብሄር ቃል ካልሆነ፡ ስሕተት ነው። አያችሁ? ቃል የሁሉ ነገር፡ የሁሉ ነገር መደምደምያ መሆን አለበት። የጌታ ቃል የአሜን ፍጻሜ ይሁን።

27 አሁን ይህን አትርሱ፡ ሐይማኖት ተቋም ውስጥ ያለውን ማንንም ሰው ክርስትያን አይደለህም እያልኩ አይደለም (ይሄን መገንዘብ አለባችሁ።) በሐይማኖት ተቋማት ውስጥ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ፡ የእግዚአብሄር ልጆች የሆኑ ድንቅ ነፍሳት አሉ። እነሱን በመነጠል እና በማዳላት፡ እኔ ይሄን እቃወማለሁ። የእግዚአብሄር ቃልም ይቃወመዋል።

28 ደግሞም በእግዚአብሄር ቃል ምድሪቱ ላይ ይመጣል ከተባለው ርዕዮተ ዓለም በቀር፣ ዛሬ በምድሪቱ የመጣ፡ ሌላ ርዕዮተ ዓለም፡ አለመኖሩን እኔ አምናለሁ። የእግዚአብሔር ቃል፡ በዚህ ቃል ውስጥ የሚያስፈልገን ሁሉ አቅርቦት እንደሚሰጠን አምናለሁ። ከ… ከጅማሬአችን እስከ ፍጻሜው ድረስ፡

በእግዚአብሄር ቃል ዘንድ የሌለ ነገር የለም። ስለዚህ—እንደማምነው አስቀድሞ ከተነገረ በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ካለ... እንታዘዘው። የእግዚአብሄር ቃል ያስጠነቅቃልና።

29 የእግዚአብሄር ቃል፡ ጋዜጣን እንደማንበብ የሚነበብ ጽሑፍ አይደለም። የእግዚአብሄር ቃል ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚነበብ ነው፡ ምክንያቱ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ በኩል እራሱ ይናገራል። ክርስቶስ እራሱ እነዚህን ነገሮች ከአስተዋዮች እና ከጥበበኞች አይን ሰውሮ፣ መማር ለሚወዱ ለህጻናት ስለገለጠላቸው እግዚአብሄርን አመሰግኗል። ስለዚህ፡ አስተውሉ፡ የተማረ ብሎ ነገር የለም፡ በተቋም መያዝ ብሎ ነገር አይኖርም። እውነት ለመያዝ ብቸኛ መንገድ አንድ ናት፡ ይህም በእግዚአብሄር መንፈስ መመራት ነው። ልምምዳችሁ ከዚህ ቃል ጋር መስማማት አለበት። አያችሁ? እንዲህ ከሆነ አግኝታችሁታል። አያችሁ?

30 ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፡ ወግ አጥባቂ ካልቪንሲት የሆኑ—ሰዎችን... ሌሎቹም ወግ አጥባቂ የሆኑ አርመንያን፡ እና—የተለያዩ ዓይነት መንገድ፡ እያየን እንቀጥላለን። አሁን፡ ለሁለት የሚከፈል ምንም አይነት ነገር፡ የተከፈለው ነገር ሁለት ገጽ መያዙ አይቀርም። ይህ ፍጹም እውነት ነው። ሁለቱ ገጾችም አከራካሪ ነገሮች ይኖራቸዋል። ዋናው ቁም ነገር ግን፡ እውነታው የት ይገኛል፡ ነው? ሐሳባችን እና፡ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ፡ ወደፊት የምንመጣበት ርዕሰም ይህ ነው፡ እውነቱን እናሳያችኋለን። አሁን ሁላችንም... አንዳንድ የቤተክርስትያን ዶክትሪኖች እዚህ ላይ ጽፌ ይዣለሁ።

31 ስለዚህ ሁላችን፡ ለጥቂት ደቂቃዎች፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን እንከፍታለን። ከራእይ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 1 እንክፈት፤ ወይም ለመጀመር ያክል፡ 17ኛው ምዕራፍ፡ እንከፍታለን። እናንብበውና እና አብያተ ክርስቲያናት ከየት እንደጀመሩ፡ እና ምን—ምን እንዳስጀመራቸው ለማወቅ እንሞክር። አሁን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ያስጠነቅቃል። የምንኖርበትን—ቀናት አስቀድሞ አስጠንቅቋል። አሁን፡ በራዕይ፡ ምዕራፍ 17፡ ከደረሳችሁ። 13ኛ ብዬ ነበር፡ ይህን ማለቴ አይደለም፡ ያ በ... ይሄኛውም፡ የዩናይትድ ስቴትስ ትንቢት ነው፡ ከአፍታ በኋላ እናየዋለን። አሁን ግን በጽሞና አድምጡ።

> **ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላእክት፡ አንዱ** ወደ እኔ **መጥቶ፡ እንዲህ ተናገረኚ... ና፡ በብዙም ውኃዎች** ላይ **የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ** አሳይሃለሁ... **አለኚ፤**

32 አስታውሱ፡ ይህ ሚስጥራዊ ነገር ነው። አሁን፡ ስለዚህች ሴተኛ-አዳሪ ሴት፡ እንወቅ ካልን፡ በመጀምርያ ደረጃ በውስጥ ያሉ ገጸ ባህርያት ምንነት ማወቅ አለብን። ስለዚህ፡ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ፡ **ሴት፡** "የቤተ ክርስትያን፡" ምሳሌ ናት። ቤተ ክርስትያን ሙሽራ ናትና። እኛ ሙሽራ መሆናችን ሰንቶች ታውቃላችሁ?

33 "ና ፍርዷን አሳይሃለሁ።" በብዙ ውኆች ላይ በተቀመጠችው ርኩስ ሴት፡ በታላቂቱ ጋለሞታ ላይ፡ ፍርድ ይመጣባታል። **ሴቲቱ፡** "የቤተ ክርስትያን" ምሳሌ ስትሆን፡ **ውኃ** "ህዝብን" ይወክላል። በተጨማሪም፡ ካስተዋላችሁት፡ ባላችሁበት፡ ከዚያው ምዕራፍ ሳትወጡ፡ እዚያው፡ 15ኛው ቁጥርም፡ ተመለከቱት።

**እንዲህም** አለኝ፡ **ጋለሞታይቱ የተቀመጠችበት፡ ያየሃቸው ውኆዎች፡ ወገኖችና፡... ብዙ ሰዎች፡... አሕዛብ፡ እና** ቋንቋዎችም **ናቸው አለኝ።** (እያችሁ? )

34 ይህች፡ ታላቅ ሴት፡ ይህች ታላቅ ቤተ ክርስትያን፡ ሴተኛ-አዳሪ መባልዋ አትርሱ። እንግዲህ፡ ሴት የቤተ ክርስትያን ምሳሌ ከሆነች፡ (የክርስቶስ ቤተ ክርስትያንም ሙሽራ፡ ቅድስት ሙሽራ ከተባለች)፡ እዚህ የምናያት ሴት ግን ያልተቀደሰች ሴት ናት። ስለዚህ ሙሽራይቱን ለመምሰል የምታታልል፡ የረከሰች፡ ሌላ ሴት ናት። እያችሁ? ሌላስ፡ ምን አድርጋለች? "በብዙዎች ላይ የተቀመጠች፡" ማለት፡ "በብዙ ውኆች ላይ ሰልጣን እንዲኖራት፡" **የበላይ** የሆነች። በሌላ አባባል፡ በሕዝቦች እና ቋንቋዎች በብዙ ሰዎች ላይ ሰልጣን አላት ማለት ነው። ይህች ሴት፡ ታላቅ ሴት ናት።

እና፡ **የምድርም ነገሥታት ከእርሰዋ ጋር ሴሰኑ፡...**

35 "የምድርም ነገሥታት ከእርሰዋ ጋር ሴሰኑ፡" ባለጸጎች እና፡ ታላላቅ ሰዎች አመነዘሩ። እንዴት ነው የምታመነዝሩት፡ አንድ ንጉስ፡ ከቤት ክርስትያን ጋር እንዴት ያመነዝራል? መነፈሳዊ ምንዝርና ነው። መንፈሳዊ! ምንዝርና ምንድነው? ምንዝርና፡ ለባልዋ እንደማትታመን ሴት፡ ማለት ነው። ባል እያላት ከሌላ ወንድ ጋር የምትኖር ሴት ማለት ነው። እንግዲያውስ፡ ይህች ቤተ—ክርስትያንም፡ በረከሰ አኗኗርዋ፡ እና በረከሰ ሰራዋ፡ በዓለም ካሉ ነገስታት ጋር እያመነዘረች፣ እራሷን እንደ ክርስቶሰ ሙሽራ በማሰመሰል ታቀርባለች። ኦህ፡ እንዴት ጥልቅ እና የማይመረመር ነው። ቃሉን እጅግ አፈቅረዋለሁ። አሁን አስተውሉ።

**... የምድርም ነገሥታት ከእርሰዋ ጋር ሴሰኑ፡ በምድርም የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ ብሎ ተናገረኝ።**

36 ለካ የምትሰጣቸው "ወይን ጠጁ" ነው፡ እሱም መነቃቃት ነው፡ "ቤተ ክርስትያኒቱ እኛ ነን! ዋናው ከእኛ ነው ይላሉ።" እያችሁ? ይሄን፡ በአእምሮአችሁ ሳሉት። በጣም ጥሩ። "ወደ በረሀ ወሰደኝ-... "

37 መልአኩም ለዮሐንስ "ወደዚች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን የሚመጣውን ይህን ፍርድ አሳይሃለሁ፡" አለው። አሁን ተከታተሉኝ።

**በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት** ተቀምጣ **አየሁ፡...**

38 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ **አለላ** "የዘውድ፡" ምሳሌ ነው። **አለላ** ማለት "ቀይ" ቀለም ነው። **አውሬ** ማለት ደግሞ "ሰልጣን" ይወክላል።

በራእይ መጽሐፍ፡ 13ኛው ምዕራፍ፡ ከባሕር የሚወጣውን አውሬ እንዳለ፡ አስተውላችኋል። ይህ አውሬ ከባህር ሲወጣ ማየታችሁ፡ ይህ ሰልጣን ከሕዝብ መካከል እንደሚነሳ የሚያሰረዳ ትርጉም አለው።

በራዕይ 13 ላይ፡ የሚነሳው በግ፡ ከሕዝብ ሳይሆን፡ ከምድር እንደሚወጣ ይናገራል፡ ማለት ከዩናይትድ እስቴትስ። ነገር ግን፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ሁለት ትንንሽ ቀንዶች ያወጣል፡ ይህም ህዝባዊ እና ሐይማኖታዊ ሰልጣን ነው። ሰልጣን ከተሰጠው በኋላ፡ ከእሱ በፊት እንደነበረ እንደ አውሬ ተናገረ። ይሄን

ጽፋችሁ ያዙ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት እምነት አልባ ሮማውያን እንዳደረጉት አሁንም ወደ ሐይማኖታዊ ሰደት፡ እየገባን ነው **ይላል ጌታ ሰራዊት**።

አሁን ተከታተሉ። “አውሬ ላይ፡ ማለት ስልጣን ላይ ተቀምጣለች።”

39 ኤልዔዘር፡ ርብቃን ሲያገኛት ታስታውሱታላችሁ? ማታ ነበር፡ እና ግመሎቹን ውኃ አጠጣችለት። ኤልዔዘርም ሲጸልይ፡ ጌታ ሆይ፡ “አሁን መጥታ ግመሎቹን የምታጠጣ... እኔንም ጠጣ የምትለኝ፡ ኮረዳ፡ የባርያህ፡ የይስሐቅ ሚስት ትሆን ዘንድ፡ የተመረጠች፡ እሷ ትሁን ብሎ ጸለየ።” ገና እሱ እየጸለየ፡ ርብቃ መጥታ ውኃ ሰጠችው፡ ለግመሎቹም ውኃ አጠጣቻቸው። አሁን ግመሉ፡ አውሬ መሆኑን አትርሱ። ርብቃ ውኃ ያጠጣችው ያንኑ አውሬ፡ ወደ ሙሽራዋ፡ ወደ ይስሐቅ ያደረሳት እሱ እንደሆነ እወቁ።

40 አሁንም፡ ዛሬ፡ እያመለከችው እና እያጠጣችው ያለውን የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን፡ ቤተ ክርስትያንን ከሙሽራዋ ጋር ለማገናኘት፡ ከምድር የሚያነሳት ኃይል ነው። በትክክል፡ ይስሐቅም ሲመሽ፡ ወደ ሜዳ ወጣ። እኛም ጌታ ጋር የምንገናኘው በክብሩ ሰፍራ አይደለም። ኤፌሶን፡ 5ኛው ምዕራፍ፡ አየር ላይ እንደምንቀበለው ይናገራልና። ኦህ፡ ሜተዲስቶችን የሚያንጫጫ ነገር ነው። አሰቡት እስኪ! አያችሁ? ጌታ ራሱ...

ይስሐቅ ርብቃን በግመል ሰትመጣ ባየ ጊዜ፡ ከአባቱ ቤት ወጥቶ ሜዳ ላይ ጠበቃት። እሷም ገና እንዳየችው፡ ወደደችው፡ ከግመል ወርዳ ልታገኘው ቸኮለች። እውነት ነው። ውኃ ያጠጣችው ግመል፡ ወደ ባሏ አደረሳት። እኛም ጌታን የምናገኘው አየር ላይ ነው።

አሁን ቤተክርሰትያን የምታመልከው ይህ ኃይል፡ ቤተክርሰትያን የምታመልከው ኃይል፡ ዓለም ወግ አጥባቂነት የምትለውን ነው፡ “ቤተ ክርሰትያን ከጌታዋ ጋር ለማገናኘት፡” በአየር ላይ የሚያነሳት ኃይል እሱ ነው። መንፈስ ቅዱስ ነው! አያችሁ? ሌላ...

ሌላው ደግሞ፡ ርብቃ፡ ድንግል እንደነበረች አስታውሱ።

41 አሁን ስለሷ የምናወራው ሴት ግን፡ ጋለሞታ ናት። አሁን፡ ስልጣን ምን ማለት እንደሆነ የተረዳችሁ ይመስለኛል? የዚህች፡ ስልጣን፡ ማለት—አውሬው፡ ነው። ቀይ ላይ ነበረች። አሁንስ፡ ምን አይነት አራዊት ቢሆን ነው? **ቀይ፡** “የባለጸግነት” ስልጣን ነው። አሁንስ ይህች ቤተክርሰትያን ምን አይነት ትሆናለች? ባለጸጋ ቤተ ክርሰትያን ናት፣ ታላቅ ቤተክርሰትያን ናት። ብዙ ህዝብ እና ወገኖች ማፍለስ የምትችል፡ ታላቅ እና ኃይለኛ ቤተ ክርሰትያን ናት። በምድር የሚኖሩ ነገስታት ከእርሷ ጋር መንፈሳዊ ምንዝርና አመነዘሩ፡ ማለት በምድር የሚኖሩ ታላላቅ ሰዎች ማለት ነው። አሁን ሰለ ማንነቷ አሁን እንማራለን፡ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ፡ የሐይማኖት ተቋማት ምንነት እናያለን።

> **ሴቲቱም በሐምራዊ ልብሰ ተጐናጽፋ ነበር** (ንጉሳዊ)፡ ... **በቀይና በሐምራዊ** ቀለማት፡... **ልብሰ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች... በዕንቈችም ተሸልማ ነበር፡ በእጅዋም** የሚያሰጸይፍ ነገር **የዝሙትዋም ርኵሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤**

42 በእጇ ምን ይዛለች? ሰዎችን ለማጠጣት የያዘችው፡ አስተምህሮቷ ነው፡ “ቤተ ክርሰትያን እኛ ነን። እኛ **እንዲህ** ነን።” የምድር ነገሥታትን ከእርሰዋ ጋር፡ እንደዚህ አሰከረቻቸው። “እኛ **እንዲህ** ነን። ታላቅ ሰልጣን አለን!

መንግስታትን ሁሉ ማስወገድ እንችላለን። አለን ከሚሉ ቸርቾች ሁሉ ዋናው እኛ ነን። ኑና፡ እንካችሁ... ትንሽ ከዚህ ቅመሱ፡ ከትምህርታችን ጠጡ። **እንካችሁ** ተካፈሉ። **እንካችሁ** ተካፈሉ።" ይሄ ነው፡ አያችሁ። ተመልከቷት። በእጇም ጽዋ ያዘች ይላል።

> **ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ** ቀለማት፡... **ልብሰ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች... በዕንቈችም ተሸልማ ነበር፡ በእጅዋም** የሚያስጸይፍ ነገር **የዝሙትዋም ርኩሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤**

43 ወዳጆቼ፡ ሆይ፡ ዘለአለማዊ ከሆነው የእግዚአብሄር የተባረከ ቃል እንጂ። የምናነበው ዕለታዊ ጋዜጣ አይደለም። ሰማይ ምድሩ ሁሉ ያልፋሉ፡ ይህ ቃል ግን ጸንቶ ይኖራል። አዎን።

> በግምባርዋም **ምስጢር** የሆነ **ስም፡** ማለት፡ **ምስጢራዊ ስም ነበር፣ ታላቂቱ ባቢሎን፡ የጋለሞታዎችና፡ የምድር** ርኩሰት **እናት፡ ተብሎ ተጻፈ።**

44 የሆነ ጊዜ ነው፡ በዚህ ቤተ ክርስትያን አይመስለኝም፡ የባቢሎን ታሪካዊ ዳራ፡ የሚያሳይ ሰብከት፣ **የግድግዳው የእጅ ጽሑፍ፡** በሚል ርዕስ ሰብከት ሰብኬ ነበር። እና፡ በአሁኑ ዓለም ውስጥ የሚገኘው የትኛውም አይነት ርዕዮተ ዓለም ይሁን ሐይማኖት፡ ውይም የተነሳ ርዕዮተ ዓለም ሁሉ፡ መነሻው ከዘፍጠረት ነው ብዬ ነበር። የሂስሎፕ **ሁለት ባቢሎኖች** የሚል መጽሐፍ፡ ወይም እንደሱ የመሳሰሉ መጻሕፍቶች እንብባችሁ፡ ከታሪክ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ ማግኘት የምትፈልጉትን የርዕዮተ ዓለም አይነት ልታገኙ ትችላላችሁ። እሺ፡ በጥቂት ደቂቃዎች፡ የሴቶች ሰባኪዎች እና ሌሎች ወደሚመለከት እመልሳችኋለሁ፡ ያኔ በዘፍጥረት ውስጥ፡ የት እንደተጀመረ፡ አሳያችኋለሁ። ይህ ብቻ ሳይሆን፡ ሌሎች ነገሮች ሁሉ እንዴት ከዘፍጥረት እንደተነሱ አሳያችኋለሁ። **ዘፍጥረት** ማለት "ጅማሬ" ማለት ነው። ይህን እውነት ሰንቶች ታውቃቂታላችሁ? ዘፍጥረት የሁሉ ጅማሬ ነው። ስለዚህ፡ ህያው የሆነ ሁሉ፡ ጅማሬ አለው።

45 ባለፋት ሁለት ወራት ሁለት፡ ወይም ሶስት ጊዜ... ጫካዎቹ ጋር ሄጃለሁና፡ ዛፎቹን ሳያቸው። ዛፎቹ፡ አቤት ውበታቸው። አስተዋልኳቸው፡ ይወድቃሉ፡ በቦታቸው ግን ሌላ ይወጣል፡ ተተካኪ ህይወት። እና አሰብኩት። ይህ ዛፍ ጅማሬ አለው። ጅማሬ ሊኖረውም ያስፈልጋል። የዘንባባ ዛፍ፣ የግራር ዛፍ፣ የዝግባ ዛፍ፣ ወይም የጥድ ዛፍ፣ ወይም የትኛውም የዛፍ ዓይነት ሆኖ ለመብቀል የሚያስችለው፡ በሰውር የሚዘውር፡ ልዩ ክህሎት ያለው መሪ ህይል መኖሩ ግድ ነው። የዝግባ ዛፍ፡ በራሱ የበቀለ ቢሆን ኖሮ ግን፡ በዓለም ያሉ ዛፎች ሁሉ ዝግባ ይሆኑ ነበር። ነገር ግን እንዲህ በየሰርዓቱ ማስቀመጥ የሚችል ታላቅ፡ የሚመራ ክህሎት መኖሩ ግድ ነው።

ጨረቃን እና ከዋክብት ሁሉ በሰርዓተ ጸሐይ ውስጥ እንዲጸኑ ያደረጋቸው እርሱ ነው። ቅዱስ ስሙ ይባረክ! ሁሉንም በየሰርዓቱ እንዲጸና አድርጓል። ቤተ ክርስትያኒቱንም በቦታዋ ይተክላታል። ወዳሰፋት ትሰፋለች፡ ወደ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ደቡብ፣ እርሱ ወዳለበት ሁሉ ትሰፋፋለች። እነዚህን የእምነት ተቋማት ከአእምሮአችን አውጥተን ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ወደ ቀራንዮ

ከወረወርን። እንደ ዛፎቹ እና እንደሌላው ፍጡር ከተገዛንለት፡ ሁሉንም እንደየ ሰርዓቱ ያስተካክልልናል። ጨረቃ ተነሰታ፦ "ዛሬ እኔ አላበራም። እንዳችሁ ከዋክብት ኑና በእኔ ቦታ አብሩ አትልም።" ኧረ እኛ፡ ከዚህ ሁሉ፡ እንበልጣለን፡ አያችሁ።

46 ሰለዚህ ሰለ ባቢሎን፡ የባቢሎን፡ ትንሳኤ ተመልከቱት። መጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ ከመነሻው ይነሣል። ቀጥሎ መጽሐፍ ቅዱሰ መሃል ላይ ይነሣል። በኋላም በመጽሐፍ ቅዱሰ መጨረሻ ላይ ይነሣል። አሁን፡ የሆነ ነገር አለ። ነገሩ፡ በናምሩድ ይጀምራል። ናምሩድም ባቢሎንን በሰናዖር ሸለቆ፡ በጤግሮሰ ወንዝና በኤፍራጥሰ መካከል አቅራቢያ መሠረታት። ኤፍራጥሰም በሷ ያልፋል። እና—በዚያም አገር ያሉ፡ መንገዶች ሁሉ፡ በቀጥታ በባቢሎን የሚያመሩ ናቸው። በሮቹም እያንዳንዳቸው ሁለት መቶ ጫማ የሚያህል ነበሩ፤ ደጆቹም ከናሰ የተሠሩ ናቸው። ወደ ባቢሎን ከተማ በገባችሁ ጊዜ፣ የመንገዶቹ ሁሉ አቅጣጫ ወደ ዙፋኑ ያቀና ነው።

47 እና፡ ዛሬ፡ ወደ ሮም ብትሄዱ፡ መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም አቅጣጫ ይወሰዳሉ። በየመንገዱ እና በየጎዳናው፡ ህጻኑ ክርሰቶሰ ያቀፈች፡ ድንግል ማርያም ቆማ፣ ወደ ሮም አቅጣጫ እያመለከተች ትታያለች። አያችሁ? መጀመርያ፡ መጽሐፍ ቅዱሰ መነሻው ላይ መጣ፣ ቀጥሎ በመጽሀፍ ቅዱሰ መሀል ይነሣል፡ አሁን በመጨረሻ በመጽሐፍ ቅዱሰ ይታያል።

እሰኪ ምናልባት እናንተም ባክግራውንድ እንዲኖራችሁ፡ ለጥቂት ደቂቃ፡ ይሄን ላንብብላችሁ። አያችሁ? በጣም ጥሩ። "ሴቲቱንም አየኋት" ይላል፡ አሁን ተከታተሉ፡ "ቤተ ክርሰትያን" ነው። **ሴት** የሚል ሰታነቡ፡ "ቤተ ክርሰትያንን" አሰቡ። እሺ?

**… ሴቲቱም በቅዱሳን ደም** ሰክራ **አየኋት፡…**

48 እዚህ ጋር፡ **ቅዱሰ** የሚል ቃል ከወዴት መጣ? **ቅዱሰ** የሚል ቃል "የተቀደሱ፡" ወይም "የታጠቡ፡" የተቀደሱ ለማለት ነው። በጣም ጥሩ።

**… በቅዱሳን ደም** ሰክራ አየኋት፡…

49 ይህች ሴት፡ ቤተክርሰትያን ከሆነች፡ ቅዱሳንን አሳድዳለች። ታላቅ ቤተክርሰትያን ናት። በብዙ ውኆች ላይ ናት። ማለት በምድር ሁሉ ሰልጣን አላት። ከዚች ሴት… የምድር ነገሰታት ሁሉ ከሷ ጋር አመነዘሩ። ታድያ፡ ማን ናት? ምሰጢራዊት ነገር ናት። መንፈሰ፡ እንድምታውቁት… በቤተ ክርሰትያን ውሰጥ፡ ዘጠኝ መንፈሳዊ ጸጋዎች አሉ፤ አንዱ የጥበብ፣ አንዱ የማሰተዋል፣ አንዱ የፈውሰ፣ ሌላ **ሌላውም።**

**… በኢየሱሰ ሰማእት ደም ሰክራ አየኋት፤…**

50 ቤተክርሰትያን ሰለምትናገረው እንጂ። ኢየሱሰ ሰለተናገረው ነገር ግድ የሚላቸው አይመሰሉም። አዎን። ይሄ፡ ትክክል ነው።

**… ባየኋትም ጊዜ፡ እጅግ ታላቅ ድንቅ አደነቅሁ።**

51 "በታላቅ መገረም ተገረምኩ። የሷ ነገር… እጅግ—ድንቅ—ነው፡ ነገሯ ሁሉ ያሰደንቃል… " እሰኪ አሁን እኔ በዮሃንሰ ቦያ ሆኜ ልመልከተውና የተወሰነ ነገር ለመክፈት ልሞክር፡ እሺ። ዮሃንሰ ሲናገር፦ "የክርሰትያን ቤተ ክርሰትያን እንደሆነች። እና የዓለምን ገንዘብ ሁሉ፡ በመያዝ የምድር ነገሰታትን ሁሉ ከእግሯ

ስር ጥላ። ተዝናንታ ተቀምጣለች ብሏታል። በብዙ ቀለማት ያጌጠች ሀብታም ሴት፡ በኢየሱስ ስማእታት እንዴት ስከረች? ቅዱሳንን እንዴት አሳደደች? የክርስቶስን ስማእት እንዴት ገደለች? ደግሞም ስለራሷ፡ እኔ ክርስትያን ነኝ፡ የክርስትያን ቤተ ክርስትያን ነኝ ብላለች።" አሁን ተከታተሉኝ።

**መልአኩም አለኝ፡ የምትደነቅ ስለ ምንድር ነው? የሴቲቱን ምስጢርና፡** እና **የሚሸከማትን ሰባት ራሶችና አስር ቀንዶች** ያሉትን... **የአውሬውን፡ ምስጢር እኔ እነግርሃለሁ።**

52 ቀጣዩ፡ ቀለል ያለ ንባብ ነው። ይሄን ያዙ። እጅግ ቀላል ነው።

ያየኸው **አውሬ አስቀድሞ ነበረ፡ አሁንም የለም፡ ከጥልቁም** ይመጣል **ይወጣ... ዘንድ አለው፡ ወደ ጥፋትም** ይሄዳል፤ **ስሞቻቸውም** ከዓለም **ፍጥረት ጀምሮ፡ ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ፡ አውሬው** አስቀድሞ **እንደነበረ፡** አሁን **ግን—ግን እንደሌለ፡** ነገር ግን **እንዳለ** ሲያዩ... **ያደንቃሉ።**

53 አሁን፡ ይሄ መስመር አለበት፡ እንዲህ ነው። አሁን ተከታተሉ፡ እንዲህ አለ፡ "በምድር ያሉ ሁሉ፡" አለ፤ ጥቂቶች ብቻ፡ አላለም፡ "በምድር የሚኖሩ ሁሉ ያደንቃሉ አለ።" ሁሉም ይደነቃሉ። መላ ምድሪቱ በሴቲቱ ምክንያት ትደነቃለች። ይህ ነገር የማያስደንቃቸው የተለዩ ሰዎች ግን አሉ፡ እነዚህም ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሀፍ የተጻፈላቸው ሰዎች ናቸው።

54 እስኪ፡ ይሄን ጉዳይ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እንመጣበታለንና፡ ትንሽ ጨመቅ አድርጌ ልናገረው። እያችሁ? ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሀፍ መቼ ተጻፈ? ከ (መቼ? ) ባለፈው ከተካፈሉት ሪቫይቫል ጀምሮ ነው? ወይስ ወደ መሰውያው የሄዱ ዕለት ነው? ወይስ የቤተክርስትያን አባል የሆኑ ቀን ነው? እናንተን ለመጉዳት አይደለም። ይሁን እንጂ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ነገር፡ ልንገራችሁ፡ "ዓለም ምስረታ በፊት ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፉ ናቸው።" በትክክል! እግዚአብሔር፡ በመጀመርያ፡ ልጁን እንደሚልክ ባየው ጊዜ ነው፡ የእግዚአብሄር ልጅ ደም ሲፈስ፡ እርሱም በሐጥያተኞች ፈንታ ሲሰዋ። መጽሀፍ ቅዱስ ደሙ ከዓለም ምስረታ በፊት እንደፈሰሰ ይናገራል። መጽሀፍ ቅዱስ፡ "የክርስቶስ ደም ከአለም ምስረታ በፊት መፍሰሱ እንደሚናገር" ይሄን እንደሚናገር፡ ሰንቶች ታውቃላችሁ? ደሙ በፈሰሰ ጊዜ፡ ስሞቻቸው በድሙ የተጻፈላቸው፡ የአካሉ ብልቶች ሁሉ፡ ከዓለም ምስረታ በፊት፡ በበጉ የህይወት መጽሐፍ እንደተጻፈላቸው። ወንድሜ፡ ሆይ! የሚያስፈራህ ምንድነው? ይሄ'ኮ በሮችን ሁሉ ይከፋፍትልሃል፡ አይደለም'ዴ?

55 አሁን፡ ይሄን እናንብበው እና፡ በትክክል ከተናገረው እንይ። እሺ? "መልአኩም አለኝ፡ 'ለምን... '" 8ኛው ቁጥር ይመስለኛል፡ እሺ። "ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ... " ይሄ ነው።

ያየኸው **አውሬ አስቀድሞ** ነበረ፡ **አሁንም የለም፡ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፡...**

አሁን፡ ወደዚህ መመለሳችን፡ ስለማይቀር፡ ይሄ ሌላኛውን ማየት እፈልጋለሁ።

**... ወደ ጥፋትም** ይሄዳል፡ **ስሞቻቸውም ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ** ሁሉ **ይደነቃሉ፡ ስሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ፡...**

56 በሌላ አባባል፡ አታላዩ የሚያታልላቸው፡ "በምድር የሚኖሩ ሰዎች አሉ፡" "እሱ ያታልላቸዋል።" የማይታለሉ ጥቂቶች ይኖራሉ፡ እነዚህ ግን ከዓለም ምስረታ በፊት ስሞቻቸው በህይወት መጽሐፍ የተጻፉ ናቸው። ከአፍታ በኋላ እንመለስበታለን።

57 አሁን ግን ይህች ሴት፡ ቤተ ክርስትያን "**ምስጢር፡ ባቢሎን**" እንደሆነች አውቀናታል። በኒምሮድ እንደተነሣች አይተናል። የኒምሮድ ዓላማ ምን ነበር? ኒምሮድ ከተማይቱን ሰርቶ ሌሎች ከተሞች ሁሉ ለዚህች ከተማ ለማስገበር ነው። ዛሬስ እንዲህ ያለ ነገር አይታይምን? እንዲህ ያለች ቦታ የለችምን? መላ ዓለም የተቆጣጠረች ቤተ ክርስትያን የለችምን? በርግጥ አለች። መንግስታትን ሁሉ የሚያስገብር አገር አሁን አለን? አንድ አገር አለን?

አሁን ወደፊት ትንሽ በመሄድ፡ ማንበባችን እንቀጥልና፡ የነገሩን ሙሉ ስዕል ታዩታላችሁ። በጣም ጥሩ።

**... አውሬው እንደነበረ፡... አሁንም** እንደሌለ፡ **ነገር ግን፡ እንዳለ** ሲያዩ **ያደንቃሉ።**

**ጥበብ** ያለው **አእምሮ በዚህ ነው።**

58 አሁን፡ ጥበብ ከመንፈስ ስጦታዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ሰንቶች ታውቃላችሁ? ታድያ፡ እንዲህ ከሆነ፡ ስለማን እየተናገረ ነው? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በዚህ ቤተክርሰትያን ለሚሰራባቸው—ለተወሰኑ ቡድኖች እየተናገረ ነው።

... **ጥበብ** ያለው **አእምሮ** በዚህ **ነው።**

59 አሁን፡ ቆም ብላችሁ፡ ይሄ ሁሉ በቤተርሰትያን ዘመን ውስጥ መርምሩ። እነዚህ ስጦታዎች በመጨረሻው ዘመን እንዴት፡ እንደሚሰሩ፡ መንፈስ ቅዱስ በግልጥ ይናገራል። ለምሳሌ፡ የፈውስ ጸጋ አሁን እየሰራ ነው። ኦህ፡ በጣም—በጣም ያስደስታል። ወንድሜ፡ ሆይ፡ ሌሎች ጸጋዎችም አሉ። ፈውስ ከሌሎቹ ጋር አንድ ነው። እንደውም ትንሹ ነገር ነው። እሺ፡ ከሁሉ የሚበልጠው ጸጋ እንደሚከተለው ነው። የትኛው ይበልጣል፡ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ የጥበብ ጸጋ ነው፡ ወይስ አንድ ግለ ሰብ በፈውስ ጸጋ ከሚፈወስ ይልቅ፡ የጌታን ቃል ቦታ ቦታውን በማስያዝ ቤተ ክርስትያን እና እኛ የቆምንበት የሚያሳይ? ሁላችንም ደህና መሆን እንፈልጋለን። እኔ ግን ከሥጋዬ ምቾት ይልቅ፡ በማንኛውም ጊዜ፡ የነፍሴን ምቾት እመርጣለሁ። ኦህ፡ ማይ!

መንፈስ ቅዱስ በፍጥሞ፡ ዮሃንስን ሲናገረው፡ እንዲህ ብሎታል፡- "ጥበብ ያለው፡ ይሄን ይሰማ።" አሁን ሙሉ የተሳለ ስዕሉን ከዚህ እያየነው ነው። "ይሄው... "

**ጥበብ** ያለው **አእምሮ በዚህ ነው። ሰባቱ ራሶች ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው፡ ሰባት ተራራዎች ናቸው።**

60 በመላው ዓለም ካሉ፡ እኔ ከማውቃቸው ከተሞች፡ ሰባት... ወይም ከዚያ በላይ፡ ተራሮች ያላት አንድ፡ ማለቴ ሁለት ከተሞች አሉ። አንደኛዋ ሲንሲናቲ

ስትሆን፡ ሲንሲናቲን በተረት ታሪክ የሚታወቅ ነው። እንደምታውቁት፡ የተኩላ እናት ትባላለች፡ እና... ወዘተ። በውስጧ ግን ከዚያ ይልቅ የበዛ ነገር አላት። ሲንሲናቲ ግን የምትቆጣጠረው አንድም ቤተ ክርስቲያን የለም።

በሰባት ኮረብታ ላይ ተቀምጣ፡ መላውን አለም የምትቆጣጠር ቤተክርስቲያን ያለችበት ስፍራ፡ በአለም ላይ አንድ ቦታ ብቻ አለች። እኔ ራሴ፡ ገና ከዚያ መምጣቴ ነው። እነዚያ ሁሉ ነገሮች።

በዚያ የተጻፈው ነገር አይቻለሁ፡ “ጥበበኛ ማለት ይህ ነው።” ራዕይ 13። “እእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፡ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና።” የሰዎች ቍጥር፡ ወይም የብዙ ሰዎች ሳይሆን፡ ለአንድ እንደሚናገር ግን “ሰው” ይላል። “ቍጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ-ስድስት ነው።”

61 በሮም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዙፋን ላይ፡ “VICARIVS FILII DEI.” የሚል የተጻፈ ጽሑፍ፡ እንዳለ፡ ሰምቻለሁ። እና ይህ ነገር እውነት ይሆን ብዬ ቆጠርኩት። መስመር አሰምሬ፡ በየሮማን ቁጥሮቹ በመደዳ አስቀምጬ፡ መረመርኩት። በትክክልም እውነት ነው። የጳጳሱ ባለ ሶስት ደረጃ አክሊል፡ በመስታወቱ **አጠገብ** ቆሜ አይቻለው፡ “የገሃነም ስልጣን፣ ገነት፣ እና የሙታን ማቆያ።” አያችሁ? እነዚህ ነገሮች፡ ሮም ውስጥ ያሉ እውነታዎች፡ ናቸው፡ እኔም ከዚያ በቅርብ ነው የመጣሁት። አሁን ቦታ ቦታውን እንደያዘ አውቀናል።

> **ስለዚህ** (በዚያ ዘመን የነበሩ) **ሰባት ነገሥታት** ናቸው፤ **አምስቱ ወድቀዋል፣ አንድ አሁን አለ** (ይህም ሊመጣ ያለው፡ ቄሳር ነው)፣ የቀረውም **ገና አልመጣም** (ይህ ማለት፡ ክፉው ሄሮድ ነው)፤...

62 አሁን ተከታተሉ። እንዴት ድንቅ እንደሆነ ተከታተሉ።

> **... ሲመጣም፡ ጥቂት** ጊዜ **ሊቆይ ይገባዋል።**

63 ሄሮድ ለምን ያህል ጊዜ እንደገዛ የሚያውቅ አለ? ለስድስት ወር። የገዛ እናቱን በፈረስ ጋሪ ጎትቶ መንገድ ላይ ገድሏታል። ከተማይቱንም በእሳት አቃጥሎ፡ በክርስቲያኖችም ላይ አላከኳል። ከተማይቱ ለስድስት—ስድስት ወራት እየተቃጠለች። እሱ ግን በተራራው ራስ ሆኖ... ሲያፌዝ ነበር። እዩት፡ “አውሬው... ” ምን ያህል፡ እርኩስ ሰው እንደነበረ ተመልከቱት። አያችሁ? አሁን ተከታተሉኝ።

> **የነበረውና፡ የሌለውም አውሬ፡ ራሱ ደግሞ... ስምንተኛው ነው፣ ከሰባተኛው** (የሰባተኛው ባሕርይ) ነው፡ **ወደ ጥፋትም ይሄዳል።**

64 **ጥፋት** ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሁሉም ሰው ያውቃል፡ “ሲኦል ነው።” ከየት እንደ ወጣም ተመልከቱት፡ “ከሲኦል ነው።” ምንድነው እሱ? ጥልቁ ጉድጓድ ነው። ስለዚህ ካቶሊካዊ አስተምህሮት መሰረት የለውም። የካቶሊክ አስተምህሮ የሚደግፍ መጽሐፍ ቅዱስ የለም። አንድም የካቶሊክ አስተምህሮን የሚደግፍ መጽሐፍ ቅዱስ የለም፡ በፍጹም። አይሰማሙም። አንድ ቄስ አለ፡ ሳክርድ ሃርት ቸርች ውስጥ የሚያገለግል ቄስ ነው እኔ ጋር መጥቶ ነበር። ሜሪ ኤልሳቤጥ ፍሬይዘርን እንዳጠመቅኳት እያጫወትኩት ነበር። እና “እሱም፡ ኦህ... ” “ኦህ፡ ድሮ ካቶሊክ ቤተ ክርስትያን እንደምታጠምቅ አርገህ አጥምቀሃታል፡” አለኝ

እኔም "መቼ ነበር? " አልኩት፤

እርሱም "በመጽሐፍ ቅዱስ፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ፡" አለኝ።

65 "ካቶሊክ ቤተክርስትያን እንዲህ አጥምቃ ታውቃለች? የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን አስተምህሮ ነው? " ብዬ ጠየቅኩት፤

"አዎን።"

66 "የካቶሊክ ቤተክርስትያን ፈጽማ የማትሳሳት ከሆነች፡ ይሄን ያክል ለውጥ ለምን ሆነ? " ብዬ ጠየቅኩት፤ አያችሁ?

67 እርሱም "እየህ፡ እናንተ የምታምኑት፡ መጽሐፍ ቅዱስን ነው። እኛ የምናምነው ቤተ ክርስትያኒቱን ነው፡" አለኝ። አያችሁ? "ቤተ ክርስቲያን የምትለው ነው እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ግድ የለንም።" አያችሁ? በትክክል እንዲህ ናቸው። ከገጠሟችሁ፡ አንድ ቀን፡ መርምሯችሁ፡ እዩት። ቤተ ክርስቲያን ለምትለው ግድ ይላቸዋል እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ቢል፤ ከምንም አይቆጥሩትም። አያችሁ?

68 እኛ ግን እግዚአብሔር የሚለውን እናምናለን እንጂ። ቤተ ክርስቲያን ለምትናገረው ግድ የለንም። ኣሜን። መጽሐፍ ቅዱስም፡ "የሰው ቃል ሁሉ ውሸት ይሁን፡ ቃሌ እውነት ይሁን፡" ይላልና። የእምነት ተቋም ያልሆንነው ለዚህ ነው።

69 አሁን ተከታተሉኝ። ለጥቂት ደቂቃ፡ ይሄን ስሙኝ። "የወደቁት፡ አምስት ነገስታት ናቸው፡ አምስት ነገስታት።" ከታሪክ ማየት ከፈለጋችሁ፡ ላሳያችሁ እችላለሁ። "እንደኛው አሁን አለ፡ አንድ ግን ገና ይመጣል።"

አሁን ተከታተሉኝ፡ ይህ፡ አውሬ ንጉስ አልነበረም። "አውሬው።" አውሬው "አስቀድሞ የነበረ፡ አሁን የሌለ፣ ግን ደግሞ ያለ፡ ደግሞ የሌለ፣ እንደገናም ያለ፡ ደግሞ የሌለ ነው።" ምን ማለት ነው? አውሬው የሚመራበት፡ ስልጣን ሲሆን፡ የጳጳሳት መተካካት ነው። ሐይማኖት አልባዋ ሮም ጳጳሳዊት ሮም የሆነችበት ጊዜ ይሄ ነው። ሐይማኖት አልባዋ ሮም፡ ጳጳሳዊት ወደ መሆን ተቀየረች፡ በንጉስ ፋንታ፡ ጳጳስ ነበራቸው፡ ጳጳሱ መንፈሳዊ ንጉሳቸው ሆነ። የኢየሱስ ክርስቶስ ወኪል በመባል፡ መንፈሳዊ ንጉሳዊነት፡ እንዲሾም ያስቻለበት ምክንያት ይህ ነው። ይሄውላችሁ እንግዲህ። ተከታተሉ።

70 ከዚህ ውስጥ የካቶሊክ አስተምህሮት ምን እንደሆነ አውጥተን ወደ ፕሮቴስታንት አብያተ ክርስትያናት እንዴት ሰርጋ እንደገባች፡ እና፡ እንዴት በፕሮቴስታንት ቤተ እምነት ውስጥ እንደምትገኝ፡ ሁሉንም አሳያችኋለሁ። ይህም፡ የመጽሐፍ ቅዱስ፡ እውነተኛ ተቃራኒ፡ ፍጹም ተቃዋሚ ሆና ነው። "ይህ የነበረ፡ ነገር ግን የሌለ፡" አውሬ። አስተውሉ፡ "ስሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ፡ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ፡ በምድር የሚኖሩ ሁሉም እንደሚታለሉ ይሄን እንዳትረሱ።" እናንብበው።

> (11ኛው ቁጥር) **የነበረውና፡ አሁን የሌለውም አውሬ፡** ራሱ ደግሞ **ስምንተኛው ነው፡ ከሰባቱም...** አንዱ ነው፡ **ወደ ጥፋትም ይሄዳል።** (በመንገዱ መጨረሻ ላይ ወደ ጥልቁ ጉድጓድ እስኪጣል ድረስ ይቀጥላል።)
>
> ያየሃቸውም **አስሩ ቀንዶች... አስር ነገሥታት ናቸው፡**

አሁን ተመልከቱ። አስደናቂ ነገር ማየት ከፈለጋችሁ፡ ይህን ተመልከቱ።

**... መንግሥትን ያልተቀበሉ፡ አሰር ነገሥታት ናቸው፡ ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ።**

71 ነገስታት ሆነው ገና አልተሾሙም፡ አምባገነኖች ናቸው። አያችሁ፡ ነገስታት ተብለው አልተሾሙም፡ ነገር ግን፡ በአውሬው መንግሰት ውሰጥ፡ ለአንድ ሰዓት ሰልጣንን ተቀብለዋል። አምባገነኖቹ የሚነሱባት ትንሿ የጊዜ መደብም ይህች ጊዜ ናት። አያችሁ? "ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት፡ እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ።" አሁን፡ እንቀጥል።

**እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው፥ ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ።**

**እነዚህ ከበጉ ጋር ይዋጋሉ፤ በጉም ድል ይነሣቸዋል፤** (ክብር!) **የጌቶች** ጌታና፡ **የነገሥታት ንጉሥ ሰለ ሆነ እነርሱን ድል ይነሣቸዋል፤ ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩ፡ የተመረጡ፡ የታመኑ ደግሞ ድል ይነሣሉ።**

72 አቤት በዚህ ርዕሰ ላይ አሁን ሰብከት ብሰብክ ተመኘው፡ "ከዓለም ፍጥረት በፊት፡ የተመረጡ፡ ለተጠሩበት ጥሪ ታማኞች የሆኑ።" ሃሌሉያ! እንዲህ ነው። "የተጠሩ፡ የተመረጡ፡ እና የታመኑ ናቸው።" **እና** የሚል መስተጻምር፡ ይታያችኋል፡ "የተመረጡ፡ እና የታመኑ።" ምንም ያህል ቢበረታ። እነርሱ ግን ድል ይነሡታል።

73 ዛሬ ዛሬ የምትሰሙት፡ ኮሙኒዝም የሚሉት ነገር፡ ኮሙኒዝም አያስጨንቃችሁ። በመጽሐፍ ቅዱሰ ላረጋግጥላችሁ። ይህ በትክክል የእግዚአብሄር የበቀል እጅ መሳርያ ነው። ሰለ ለገደለቻቸው ሰማዕት ሁሉ ፍዳዋን ይከፍልበታል። አዎን፡ ወዳጄ። ነገስታቶቹ ሁሉ ተሰማምተው፡ በአንድነት ሲጠሏት ታያላችሁ። ኮሙኒዝም፡ ሕዝብ ሁሉ፡ መላውን ዓለም ይውጣል። ለምን፡ እሷን ለመቅጣት፡ የእግዚአብሔር መሳርያ ሰለሚሆን። "እንዴ፡ ወንድም ብራንሃም። ኮሙኒዝም፡ የእግዚአብሄር መሳርያ ይሆናልን? " ብላችሁ ትጠይቃላችሁ፤ አዎን፡ በትክክል፡ የእግዚአብሄር መሳርያ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱሰ ይደግፈዋል። ነገር ግን እግዚአብሔርን በማይፈሩ እና በሚያሳፍሩ ዲቃላ ሰዎች ላይ ፍርድ ለመሰጠት እየመጣ ነው። በዚህ ዓለም ያተረፍነው ነገር ምንድነው? ምንሰ አግኝተናል? በቀደምለት...

74 ከተቻለ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ ከርዕሴ ልውጣና። በቀደም ቅዱሰ ቃልን እያነበብኩ ዲቃላ ልጅ እስከ አሰራ አራት ትውልድ ወደ እግዚአብሄር ጉባኤ አይግባ የሚል ቃል አነበብኩ። አዎን፡ ዘዳግም 23፡ ሰለ ዲቃላ ልጅ ይናገራል። ሰንቶቻችሁ ታውቁታላችሁ? አንድ ሴት፡ ሊያሰጥላት የሚችል ሰው በሌለበት፡ በእርሻ ውሰጥ፡ ሌላ ወንድ አግኝቶ ቢተኛባት፡ የተኛባት ሰውዬ ሊያገባት ይገባል። ሴተኛ አዳሪ ብትሆንም እንኳ፡ እሰኪሞት ድረሰ አብሯት ሊኖር ይገባዋል። ሌላው ደግሞ አንድ ሴት፡ ድንግል ሳትሆን፡ ድንግል ነኝ ብላ በማታለል፡ አንድን ሰው ብታገባው፡ እሰከ ሞት ሊያሰቀጣት ይችላል። ያገባ ወንድ ወይም ያገባች ሴት፡ ከጋብቻቸው ውጪ ልጅ ቢወልዱ፡ የተወለደው ልጅ፡ እሰከ አሰራ አራተኛ ትውልድ ድረሰ በእግዚአብሔር ጉባኤ ውሰጥ አይግባ።

አንድ ትውልድ አርባ ዓመት ነው። ስለዚህ ይህ ሐጢያት ከእስራኤል ለመራቅ አራት መቶ አመታት ይቆያል።

75 እግዚአብሔር ኃጢአትን ይጠላል! የአንዲት የእምነት ተቋም አባል ስለሆንክ ብቻ፡ የጌታ የኢየሱስን ቅዱስ ደም አልፈህ ለመግባት፡ እንዴት ትጠብቃለህ? በእውነት። ወደ እግዚአብሄር መሰፈርቶች ካልመጣህ በቀር ፈጽመህ አትገባትም። ዲያቆን፣ ሰባኪ፣ ወይም ሌላ ነገር ልትሆን ትችላለህ፡ ይህ ሁሉ የትም አያደርሰህም። ወደ እግዚአብሄር ሕግ ተመለስ።

76 አስራ አራት ትውልድ። ይሄን ርዕስ በተመለከተ ከእኔ ጋር ሲወያይ የነበረ ሰው በጉባኤው ውስጥ አለ። እና "ያኔ ማን እንደሚድን እንዴት እናውቃለን? " ብሎ ጠየቀኝ፤

77 "ምርጥ የካልቪን ተከታይ መሆን ያለብህ እዚህ ጋር ነው፡" አልኩት። ከዓለም ምስረታ በፊት ስምህ በመጽሐፍ ተጽፎአል። የደሙን ፍሰት የሚቆጣጠረው ጌታ ነው። ይህ የሱ ስራ ነው። አያችሁ?

"ታድያ ከዚህ ጋር ምን ያገናኘዋል... "

78 እናንተ ወጣቶች። ዛሬ፡ አድምጡኝ፡ እናንተ ወጣት ሴቶች እና ወንዶች፡ ከዚህ ቤተክርስትያን ናችሁ፡ ወይስ ከሌላ ቤተክርስትያን እኔ አላውቅም። ከእናንተ በኋላ ትውልድ ከቀጠለ፡ አሁን እናንተ ዛሬ በምታድርጉት ነገር ሁሉ፡ ልጆቻችሁ፡ እንደሚፈረድባቸው ታውቃላችሁን? ጨዋነትን አታከብሩምን? እናንተ አጫጭር ቀሚሶች እና የሚያሳፍር ነገር የምትለብሱ ሴቶች፡ በሴት ልጆቻችሁ የሚተላለፍ፡ መሆኑ እወቁ። እናንተ እራቁታችሁ—መደነስ የመጀመራችሁ ምክንያት፣ እያታችሁ ቅምጥል ሴት፡ እናታችሁም ዳንሰኛ በመሆናቸው እንደሆነ አታስተውሉምን? አዎን። ልጆቻችሁስ ምን አይነት ልጆች ይሆኑ ይሆን? አዎን፡ ወዳጄ። እግዚአብሄር የቤተሰብን ሐጥያት በልጆች እና በልጅ ልጆች ላይ፡ እስከ ሶስት እና አራት ትውልድ ድረስ አመጣለሁ ብሏል።

79 ስለዚህ ወንድሜ ሆይ፡ ዘወትር የምታደርገው መልካም ነገር፡ በልጆችህ ላይ እንደሚከፈል፡ ይሄን ታውቃለህን?

80 ዕብራውያን፡ ምዕራፍ 7ን፡ እንውሰድ። መጽሀፍ ቅዱስ—አብራሃም ነገስታትን ድል ነስቶ ሲመለስ አገኝቶ፡ መልከጸዴቅን ከምርኮውም ሁሉ፡ በባረከው ጊዜ፡ ቅዱስ ቃል፡ ግን፡ "ሌዊ... " አስራትን ስለመክፈሉ ይመሰክርለታል። እንዲህ በማለት፡- "ሌዊ ከወንድሞቹ አስራትን እንዲቀበል ጌታ ደንግጎለታል። ይህ አስራትን የሚቀበል ሌዊ ግን፡ አብራሃም መልከጸዴቅን በተቀበለ ጊዜ በአብራሃም ወገብ ውስጥ ሆኖ፡ አስራትን ከፍሏል ይላል።" አብራሃም ግን የሌዊ ቅድመ-አያት ነው። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፣ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፣ ያዕቆብ ሌዊን ወለደ፤ ሌዊ፣ አባቱ፣ አያቱ፣ እና ቅድመ-አያቱ። መጽሐፍ እንደሚል፡- "ሌዊም በአብርሃም ወገብ ሳለ፡" "ለመልከ ጼዴቅ አሥራት ከፍሏል።" ሃሌ ሉያ!

81 ዓለማዊ የሆነ እንቅስቃሴ ተነስቶ ታላቁን የእግዚአብሄር ዘለአለማዊ እቅድ ውስጥ ለውጥ መፍጠር ይችላል ብሎ ማንም አያታልላችሁ። በትክክል እየሰራ ነው! ይህም ገና ከጅምሩ የታቀደ ነገር ነው። በእግዚአብሄር ፕሮግራም ውስጥ ገብቶ ሊዘባርቅ የሚችል ሰይጣን እና አጋንንት ሊኖር አይችልም።

82 እዚህ ጋር፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ከፈለ “ይቆጠርለታል” አላለም። መጽሀፍ ቅዱስ፡ ገና በቅድመ-እያቱ ወገብ ሳለ “አሰራትን ከፈለ፡” ይለዋል። ክብር ይሁን! የኔ ጌታ ይሄ ነው። ኑህ፡ ከዓለም ምስረታ፡ በፊትም፡ ያውቀዋል። እርሱ ሁሉንም ያውቃል። በአብርሃም ዘንድ ሆኖም፡ አሰራትን ከፈለ።

83 ወንድሞቼ፡ እና እህቶቼ ሆይ፡ ለምን ወድያ ወዲህ ታያላችሁ፡ ሰዎች የሌላ ሰው ሚስት ምን አሰመኛችሁ፡ ሚሰቶች ሆይ ትዳራችሁን አፍርሳችሁ፡ በምትኖሩት ኑሮ፡ ቀጣይ ትውልድ ምን ዓይነት እንዲሆን ትጠብቃላችሁ? ውጤቱ ይህ ነው። የዲቃላ፣ እና ከሕግ-ውጪ የተወለዱ፣ የብልሹ ልጆች ሰብሰብ ይሆናሉ እንጂ ሌላ አይሆኑም። አሁን የቀረ ነገር፡ እየኖርንበት ያለው የአቶሚክ ዘመን ብቻ ነው። ይህ ትክክል ነው። በዘመን ፍጻሜ እየኖርን ነው።

84 ዛሬ ጠዋት፡ ከኬንታኪ ተራሮች ማዶ በስተጀርባ፡ አንድ ህጻን ልጅ፡ የማሽላ ሞላሰስ ስለሚሰራ፡ አሰር ጫማ እንኳን መቅረብ የማትመኙት ዓይነት ልጅ ነው። ግራው እና ቀኙ ለይቶ የሚያውቅ እንኳን አይመስልም። የት እንደነበርኩ… በትክክል አላወቅኩም። ብቻ ታች ነበርኩና። ሽኮኮዎችን ለማደን ወደ ላይ እየወጣሁ ነበር። እና አጥር ወደተሰራበት ሰፍራ ሰደርስ ልጁ ሰማኝ። እና በዚያ ቁጭ ብዬ፡ አንዳንድ ነገር አወራን። እና ወደ ጦር ግንባር እዘምታለሁ ብሎ እያጫወተኝ። ጨዋታችን ድንገት ሰለ ጌታ፡ ወደ መነጋገር ተቀየረ፡ እና “አንተ ሰባኪ፡ የመጨረሻ ዘመን ውሰጥ መኖራችን አታምንም’ዴ? ” አለኝ፤ በተራሮቹ መካከል የሚኖር ልጅ።

85 እኔም “አዎን፡ አምናለሁ። አዎን፡ የኔ ልጅ፡ በመጨረሻው ዘመን እንገኛለን፡” አልኩት።

86 ይሄውላችሁ። ወንድሞቼ፡ ዘመናችን ይሄ ነው። በቦታው ላይ ደርሰናል። ከእኛ በፊት የነበሩ እናቶች፡ አባቶች፡ ወንድ እያቶቻችን፡ ሴት እያቶቻችን አኗኗራቸውን አይታያችሁምን? እናት እና አባታችን እንዴት እንደሚኖሩ አይታያችሁም? በዚህ ጊዜ የኛ መበላሸት አይገርመኝም። ጭንቅላታችን እሰኪነሣ ድረስ ሰብከን፡ የለመዱትን አጭር ለብሰው፡ ፊታችሁ ላይ መትፋታቸው፡ አያሰገርምም። ሲጋራቸውን ምገው ፊታችሁ ላይ እያቦነኑ፡ “በማያገባህ አትግባ፡” ይሏችኋል። ለምን? ከእንደዚያ ዓይነት ዘር ሰለወጡ ነዋ። በቀጥታ፡ **የእባቡ ዘር፡** ወደሚል ርዕሰ አልፋለሁ። ወደዚህ መድረክ የት እንደገባች እንፈትሻለን፣ ሰራቸው ለምን እንዲህ እንደሆነ እናያለን። ከዓለም ምሰረታ ጀምሮ የዲያብሎሰ ልጆች ናቸው። ይህ እውነት ነው። ሌላ የቀራቸው ነገር፡ አንዳች የለም፡ የቀራቸው ፍርድ ብቻ ነው። ከፍርድ በቀር ሌላ ምርጫ የለም። ሰዎች በራሳቸው እጅ ይሄን አደረጉ። እግዚአብሄርም ፈጽሞ ይመታቸዋል። እግዚአብሄር እንዲህ እንዲሆን ከመጀምርያ ጀምሮ አይፈልግም፡ እንዲህ እንደሚሆን ግን ያውቃል። “ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ሰማቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውሰጥ ከተቀመጡት በቀር፡ በምድር የሚኖሩትን ሁሉ ያታልላቸዋል” ብሎ የተናገረበት ምክንያት ይህ ነው።

87 እንየው። ዘልቀን እናንብበው። 12ኛው ቁጥር ላይ፡ የደረሰን ይመሰለኛል።

> **ያየሃቸውም አሰሩ ቀንዶች፡ ገና መንግሥትን ያልተቀበሉ አሰር ነገሥታት ናቸው፤ ዳሩ ግን ከአውሬው ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ።**

**እነዚህ አንድ አሳብ** አላቸው፡ **ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ።**

እነዚህም **ከበጉ ጋር ይዋጋሉ፡ በጉም የጌቶች** ጌታና፡ **የነገሥታት ንጉሥ ስለ ሆነ፡ እነርሱን ድል ይነሣል፤ ከእርሱም ጋር** ያሉ **የተጠሩና—የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ።**

አለኝም፡ **ያየሃቸው ውኃዎችም፡ ጋለሞታይቱ የተቀመጠችባቸው፡ ወገኖችና፡... ብዙ ሰዎች፡... አሕዛብም፡ ቋንቋዎችም ናቸው።**

**... በአውሬው ላይ ያየኃቸውም አሰር ቀንዶችም፡ ጋለሞታይቱን ይጠሏታል፡...**

88 ተከታተሉ፡ "አሰር ቀንዶቹን፡" እነዚህ አሥር መንግሥታትን አስተውሏቸው። አያችሁ፡ እነኚህ አምባገነኖች፡ ነገራቸው ሁሉ እዚህ ላይ ይወድቃል። አምባገነኖች የሚደገፉባት መንገድ እዩአት። የሚደገፉት ምን ላይ ነው? እስኪ ኮሙኒዝምን የማይደገፍ አምባገነን—ጥሩልኝ። አያችሁ? "ጋለሞታይቱን፡" ሴቲቱን፡ ቤተ እምነቷን ምን (ያደርጓታል?) ይጠሏታል። ለምን ግን? ምን እንደሚያደርጓት እዩአት።

**... እነዚህም ጋለሞታይቱን ይጠሏታል፡ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል፡ ሥጋዋንም ይበላሉ፡ በእሳትም ያቃጥሉአታል።**

89 እዚህ መቆሜ እርግጠኛ እንደሆነ ሁሉ፡ ያለጥርጥር ከምድረ ገጽ ያጠፏታል። ያንን የዚያች ቤተ እምነት ርዕሰ ጉዳይ በማንሣት፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ "የምድር ነገሥታት ሁሉ፡ መርከበኞች ሁሉ፡ ሌሎች ሁሉ፡ ዋይ ዋይ እያሉ፡ ያለቅሱላታል፡ ታላቂቱ ባቢሎን በአንድ ሰዓት ውስጥ ወደመች ይላሉ" የሚል ቃል መርምረናል። በአንድ ሰዓት፡ ጠፍታለችና! አቤት፡ እንዴት፡ እንደሚገልጻት፡ "ቅዱሳን ሐዋርያት፡ ነቢያትም ሆይ፡ እግዚአብሔር የወንድሞቻችሁን እና የቅዱሳን ደም ተበቅሎባታልና ደስ ይበላችሁ።" አያችሁ፡ እውነት'ኮ ነው። አዎን፡ ልክ ንጉሱ ናቡከደነፆር አይሁድ በበደሉ ጊዜ ሊማርካቸው እንደመጣ። በእጁም አገልጋይ እንደነበረ!... ?... ኮሙኒዝምም፡ እግዚአብሄር በእጁ የያዘው መሳርያ ነው፤

90 ጻድቅ ዘር ምንም ሳይንቀሳቀስ፡ በመጨረሻው ዘራቸው ፈጽሞ እስከማይገኝ ድረስ፡ ኃጢአት እየባሰ እየባሰበት እየተበላሸ ይቀጥላል። ምክንያቱ ከእኛ በፊት የነበሩ እናቶቻቸው እና አባቶቻቸው፡ አንዳች ቅሬታ እስከማይቀርልን ድረስ፡ ወደኖሩት ኑሮ ወደዚያ ድረስ ያደርሳቸዋልና። ኢየሱስ የተናገረውን ታስታውሳላችሁ? እነዚያን ቀናቶች ባያሳጥራቸው ኖሮ፡ ስጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር ብሏል።

91 አይታያችሁም ወይ? ለምን እነዚህን ሰዎች (በመስለኛ አልተናገርኩም።) ታውቋቸዋላችሁ፡ እነ አርተር ጎድፍሬይስ፣ እነ ኤልቪስ ፕረስሊ፣ እና ሌሎች፡ እንዴት በቀሉብን፡ አፍላ ሴቶች የሚሆኑት ነገር ሁሉ፡ ከዳሌው—ታች፣ ቱታዎች፣ ፀጉር አንገታቸው ላይ ማንጠልጠል፣ ይሄ ሁሉ፣ ለምን መጣ? ማን አመጣው? ምንድነው? ከዚህ በፊት ዲቃላ-ሰዎች ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ሰዎች የኖሩት ኑሮ ነው። ሌላ ምክንያት የለውም! እንደነ ኧርኒ፡ እና ሌሎች መሰል-ምናምንቴዎች፡ እየተነሱ "አምላኬ፡ ወደ አንተ፡ እቀርባለሁ፡" እያሉ፡ ልዩ

ጣዕመ ዜማ ሲዘምሩማ፡ አቤት። ወንድሜ፡ ታውቃለህ? ይሄ ማለት፡ ይሄ'ኮ ፍጹም ግብዝነት ነው። አዎን፡ ነው።

92 ብዙ ዓይነት ነገር ውስጥ እየተዘፈቀ ሮክ-እና-ሮል እና ቡጊ-ዎጊ እየተጫወተ ከፑልፒት ጋር ምንም ጉዳይ የለውም። እዚህ መድረክ ላይ ሊቆም አይገባውም። ይሄ እግዚአብሄር ክሃናት እንዲሆኑለት፡ ለጠራቸው ብቻ ነው። በእግዚአብሄር የተጠሩ አገልጋዮች ብቻ የሚቆሙበት ስፍራ ነው። ይሄ ስፍራ እንዲያ ለመሳሰሉ ሰዎች አይገባም። ዛሬ ያለው ችግር ይሄ ነው፡ ቤተ ክርስትያንን እንደ ተራ ሎጅ አድርገው አውርደዋታል። ከሎጅ ጋር ችግር የለብኝም፡ ከፈለጋችሁት፡ የእናንተው ጉዳይ ነው። ግን ልንገራችሁ፡ በሎጅ እና በቤተክርስቲያን መካከል… በሙሉ ማረጋገጫ ሰፊ ልዩነት አለ። አዎን፡ አለ። የለመዳችሁት ነገር፡ ፓርቲዎች እና ፈንጠዚያዎች፡ ሎጅ ሄዳችሁ ማድረግ ከፈለጋችሁ እናንተን ይመለከታል። ቤተ ክርስትያን ግን፡ ወንድሜ፡ ከፑልፒቷ ጀምሮ እስከ ምድር ቤቷ ድረስ መወልወል አለባት። ትክክል። መወልወል አለባት ስል መስኮቶቿ ወዘተ ማለቴ አይደለሁም። እንደ ድሮ-ዘመን፡ አሸንክታቦቹን ከአንዱ ወደ ሌላው ጠርዝ በሚበትነው እግዚአብሔር በሚልከው-ሪቫይቫል ማለቴ ነው። እንዲህ፡ ነው። በተጣለ አፕል ላይ በሰፈሩ በረሮዎች የኤሌክትሪክ መብራት፡ እንደማብራት ማለቴ ነው። አዎን፡ መብራት ሲወነጨፍባቸው፡ ብትንትናቸው ይወጣሉ።

93 አሁን ወረድ ልበል። "አስር ቀንዶችን፡" ተከታተሉኝ። "እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው፡ ሥልጣናቸውም ይሰጡታል።" አዎን፡ ይሰጡታል።

> **እግዚአብሔር በልባቸው ውስጥ ፈቃዱን እንዲያደርጉ፡** (አሁን ተከታተሉ)፡ **የእግዚአብሔርም ቃል እስኪፈጸም ድረስ፡** መንግሥታቸውን **ለአውሬው እንዲሰጡ፡ እንዲሰማሙ አደረጋቸው።**
>
> ስለዚህ፡ **ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት** ሁሉ **ላይ፡** የምትነግሥ **ታላቂቱ ከተማ** ናት።

94 እዚህ ላይ፡ ብዙ መድከም አያስፈልገንም፡ የካቶሊክ የስልጣን ተዋረድ እንደሆነ እናውቀዋለን። ሌላ ሰውም አያስፈልግም… ይሄ—ነገር መንፈስ ቅዱስ መሞላቴ እኔ እርግጠኛ እንደሆንኩ ያህል ነገሩ የጸና መሆኑን አምናለሁ። ዛሬ እኔ እንደ ክርስትያንነቴ እዚህ ስፍራ መቆሜን ያመንኩትን ያክል፡ የካቶሊክ የስልጣን ተዋረድ—መሆኑን… እና በሰባቱ ተራሮች ላይ የተቀመጠች ከተማ—ቫቲካን ከተማ እንደሆነች አምናለሁ። የነበረ፡ አሁን የሌለ የተባለለት የቤተ ክርስትያን የስልጣን ተዋረድ፡ አውሬው ነው። ባቢሎን ናት። በመላው መጽሐፍ ቅዱስ አንዳች ሳይቀር፡ በትክክል ተከትቦ ተጽፏል። የካቶሊክ ቤተ እምነት ናት።

95 አሁን፡ አሰደንጋጩ ነገር ቀጥሎ ያለውን ነው። ምናልባት "ወንድም ብራንሃም፡ እኔ አልገባኝም፡ አልተረዳሁህም፡" በሉ። እኔ ደግሞ ጥያቄ ልጠይቃችሁ። ወደ 5ኛው ቁጥር ወደ ኋላ እንመለስ።

> በግምባርዋም፡ **ምስጢር፡ የሆነ ስም… ታላቂቱ ባቢሎን፡** የምድር ርኩሰት **እናት… የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት ተብሎ ተጻፈ።**

96 ምን ነበረች? ጋለሞታ ናት በተጨማሪም እናት ናት። ደብልዩ-ኤች-ኦ-አር-ኢ እና ኤም-ኦ-ቲ-ኤች-ኢ-አር። ልጆችም ወልዳለች። የወንዶች ልጆች እናት ናትን? አይደለችም የጋለሞታዎች እናት ናት! ጋለሞታ ምን ማለት ነው? አመንዝራ፡ ባለጌ—ሴት ማለት ነው። ባለጌ ያደረጋት ምንድነው? አስተምህሮቿ ነው። የክርስትና ቤተ እምነት ትመስላለች፡ ይሁን እንጂ ሰው-ሰራሽ ዶግማዎችን አሏት። እራሷም ደግሞ ስትመሰክር... የመጀመርያዋ ድርጅት እስከሆነች ድረስ፡ ከእሷ የወጡ ሌሎች ድርጅቶች እንዳሉ ያሳያል። የጋላሞታዎች እናት ተብላለችና። ልክ ነው ወይ? የጋለሞታዎች እናት ተብላለች። ስለዚህ፡ የወንድ ልጆች እናት፡ አይደለችም ማለት ነው። የሴት ልጆች እናት እንጂ... የወንዶች ሊሆን አይችልም። ልጆቿ ሴቶች ከሆኑ፡ እንግዲያውስ፡ እነርሱም አብያተ ክርስትያናት ናቸው። እነማን ከሷ ወጡ። አሁን እንመርምር...

97 የመጀመርያ ድርጅት ማን ነበረች? ካቶሊክ ቤተ እምነት። ሁለተኛዋ ድርጅትስ? ሉተር። ሶስተኛ ድርጅትስ? ዝዊንግሊ። ከዚያ ቀጥላስ ማን መጣች? ካልቪን። ከዚያ በኋላ አንግሊካን መጣች፣ ከአንግሊካን ወደ ሜቶዲስት። ሜቶዲስቶችስ፡ ሜቶዲስት ምን አፈሩ? ከእነርሱ መካከል አሌክሳንደር ካምቤል ወጣ። ከአሌክሳንደር ካምቤል ጆን ስሚዝ። ከ... አሌክሳንደር ካምቤል የክርስትያን ቤተ እምነት ነው፡ ከዚያ፡ አራት አምስት ወጡ፡ የክርስቶስ ቤተ ክርስትያን እና ሌሎች ርዕዮተ ዓለሞች ወጡ። ከዚያ በኋላ የባፕቲስት ቤተ እምነት ወጣች፡ እሷም ብዙ ቅርንጫፎች ዘረጋች። ከሜቶዲስት ቤተ እምነትም... ከሜቶዲስት ቤተ እምነት ውስጥ፡ ቀድማ የወጣችው፡ የዌስሊ ሜቶዲስት ናት፡ እሷም አራት አምስት ቦታ ተቆራረሰች። ከዚያም ሌላ ዓይነት ሜተዲስት፡ እነርሱም ርቀው ጠፉ፡ ከዚያ በኋላ ፍሪ ሜተዲስት በቀለች። ቀጥላ—ከዚያ ቀጥላ ወደ ናዝሪን አደገች። ከናዝሪን ፕሊግሪም ሆሊነስ፡ ከፕሊግሪም ሆሊነስ ወደ ሌሎች። ሌሎች ርዕዮተ ዓለሞች፡ እንዲሁ ተፈለፈሉ፡ እያንዳንዳቸው—ትንንሽ ጀማሪዎች ሌሎችን ፈለፈሉ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ምን አደረጉ? ሁሉንም በጴንጤ ተዋጡ።

98 ጴንጤዎችስ ምን አደረጉ? እናታቸው ያደረገችው ነገር አደረጉ፡ ወደ ኋላ ተመልሰው ድርጅት ሆኑ። ከዚያስ ምን ተፈጠረ? የሐይማኖት ተቋም። አንዳቸው ጋር ብትገቡ፡ የመጀመርያው ነገር፡ "ዶክትሪንህ ምንድነው? ነው" ወንድሜ፡ የእምነትህ አቋም ለመፈተሽ፡ ምንነትህን ለማወቅ፡ በቀጭን-ማበጠርያ፡ በደንብ አርገው ያበጥሩሃል። ወንድሜ፡ ከእምነታቸው ጋር ካልተዛመድክ፡ ወድያው ትወገዛለህ። ይህ ሁሉ እውነት ነው።

99 ጴንጤ ነኝ ስላልክ ብቻ ደህንነትህ እንደተረጋገጠ አይምሰልህ። ወንድሜ፡ ብዙዎች በእውነተኛው መንገድ እንደሚጓዙ ሁሉ፡ ብዙዎች መንገድ ዳር እንዳሉ አትዘንጋ፡ በትክክል። አያችሁ?

100 አሁን፡ ድርጅቶቹ ሁሉ፡ ምንም ሳይደራጁ፡ የጴንጤቆስጤ በረከት እንዲሰራባቸው ስፍራ ቢለቁለት፡ ስራውን እና ውግዘቱን ለመንፈስ ቅዱስ ለቀውለት በወንድማዊ እሳቤ ቢጓዙ ኖሮ። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ያወግዛል። እንዴ ሐናንያ እና ሰጺራ መጡና፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** አሉ፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ግን "ለምን ዋሻችሁ? " አላቸው፤

101 እኛ ግን፡ "ኧረ፡ ወንድም ጆንስ'ኮ ነው፡ ምን ይወጣለታል፡ መጥፎ ነገር አትናገሩ፣ መንፈስ ቅዱስ የተሞላ በልሳን የሚጸልይ ሰው ነው። በመንፈስ

የሚጮህ፡ በቤተ ክርስትያናችን ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ብዙ ገንዘብ የሚከፍል ነው፡” ይባላል። ቁርበት ላይ ውሃን እንደማፍሰስ ነው እንጂ ይሄን ምንም ትርጉም የለውም። አያችሁ? ይሄ ሁሉ ከዚህ ጋር ምንም አይገናኝም። እግዚአብሄር እራሱ ይመስክር። ነው ወይስ አይደለም እግዚአብሄር ይመስክር። ትክክል። የሐይማኖት ተቋማችን አባል እንዲሆን እናደርገዋለን። “በቃ፣ ከጉባኤው—የተወገዘ ሰው፡ ዋንነስ ያነሱታል። ዋንነስ ትንሽ ጊዜ ይሸከሙት እና፡ ያወግዙታል። እነርሱ፡ ተቀብለው የጣሉትን ሰው፡ ኦንሊ ጂሰሶች ያነሱታል። ኦንሊ ጂሰሶች ጥቂት ጊዜ ይሸከሙታል፡ ከእነርሱ በኋላ፡ ከእነርሱ ቀጥሎ የእግዚአብሄር ጉባኤ ይቀበሉታል። የእግዚአብሄር ጉባኤ በትንቢት ይይዙታል፡ ከእነዚህ በኋላ የቶምሊንሰን ንቅናቄ ውስጥ ይገባል።” ኦህ፡ ማይ! ወንድሜ ሆይ፡ ገና ያልተያዝን ከሆንን! ወደ መጨረሻው ሪቫይቫል፡ ወደ ጴንጤቆስጤ እናምልጥ! አሁንማ ሰማያዊ እሳት፣ የዘይት ንግድ፣ ፊት ላይ ደም መቀባት—ሁሉ ተዳርሰዋል። አቤት፡ ይቅር፡ ይበለን፡ ቀጥለው ምን እንደሚያመጡ እኔ አላውቅም።

102 አንድ ነገር ግን አውቃለሁ፡ ነገሩ ሁሉ ተበላሽቷል። ነገሮች እንደሚበላሹ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ እንደሚመሰክር ታውቃላችሁን? መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ዘመን—እንደሚመጣ፡ የጌታን ማዕድ ሁሉ ትፋት የሚሞላበት ዘመን፡ ይመጣል እንደሚል ታውቃላችሁ? “እውቀትን ለማን ይሰጣል? ወይስ ማስተዋልን ለማን ይሰጣል? ትእዛዝ በትእዛዝ፡ ትእዛዝ በትእዛዝ ላይ፡ ሥርዓት በሥርዓት፡ ሥርዓት በሥርዓት።” እውቀትን ለማን ያስተምረዋል? ወተትን ለተዉ፡ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነውን። አያችሁ?

103 አሁን፡ በዚህ ከተማ—ፏሪ የሆነች አንዲት ቄንጠኛ ሴት፡ መቼም ቢሆን ድንግል የሆነች ልጅ መውለዷ አይቀርም። እና፡ ልጅቷ ስትወለድ፡ ጤነኛ አካሄድ መሄዷ አይቀርም። ነገር ግን እናቷ ጋር የነበረውን ቄንጠኛ ባህርይ፡ ካላስተዋላችሁ፡ ልጅቷ፡ ዘጠኝ ከአስረኛ፡ ልክ እንደ እናቷ መሆኗ የማይቀር ነው። እውነት እንደሆነ፡ እናንተም ታውቃላችሁ። መጥፎ ዝነኛ ቤት የምትመራ ሴት፡ ሴት ልጅ ልትወልድ ትችላለች። ልጅቷም አስራ ስድስት ዓመት እስኪሞላት ድረስ፡ እንደ ማንኛውም አበባ በሰነ ምግባር ንጹሕ ልትሆን ትችላለች፡ ችግሩ ግን፡ አለመቆየቷ ነው። ችግሯ ግን፡ እንደናቷ ወጥታ፡ የእናቷ ስራ ትደግማለች።

104 ስለዚህ፡ የካቶሊክ ቤተ እምነት እራሷን በተለያየ አስተምህሮ ሸላልማ የወጣች ባለ አጉል እምነት፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ “ከጥልቅ ጉድጓድ ወጥታለችና፡ ወደ ጥፋትም ትሄዳለች፡” ያላት ይህች ናት። ብሏል መጽሐፉ። ስለዚህ፡ ትምህርታቸው እንዲህ ከሆነ፡ ስሕተት ነው። እንደ እግዚአብሄር ቃል፡ ስህተት ነው። ከሷ በኋላ ከሷ የተወለደች፡ ቆንጆ ወጣት ሴት፡ የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን መጣች፡ መጥታስ ምን አደረገች? ወደ ኋላዋ ዞር ብላ እናቷ የምታደርገውን አይነት ነገር አደረገች። ጉባኤው ሁሉ አጫጭር ቀሚስ ይልበስ። ሲጋራን ያጭስ። እንደለመዱት ክፉ ስራቸውን ቢሰሩ። ትንፍሽ የሚል ሰው የለም። ፓስተሩ ያልተገለበጠ-ቂጣ ነው፡ የቆርቆሮውን ብስኩት እንዳያጣ፡ አንድ ቀን ደሞዜ ሊከለክሉን ይችላሉ ብሎ በመፍራት፡ከፑልፒት ጀርባ ይደበቃል።

105 ወንድሜ ሆይ፡ እኔ ልነገርህ፡ ወንጌልን እየሰበክኩ፡ እውነቱንም እየተናገርኩ፡ ኮሾርዬን በልቼ የጕድጓድ ውሃ ብጠጣ ይሻለኛል። ምእመናኑ ሁሉ ትተውን ቢሄዱም፡ እኔ ግን እውነቱን መናገር ይሻለኛል። አዎን፡ ይሻላል።

106 ችግራቸው ምንድነው? ችግራቸው፡ ደሞዝ ነው። "እኔ፡ በከተማ ውስጥ ካሉ ፓስተሮች፡ የትልቋ ቤተክርስትያን ፓስተር ነኝ" እያለ ይኮፈሳል። ባፕቲስቶች እና ሜተዲስቶችም ሁላችሁ ሐሰተኛውን ነብዪ ታደምጡታላች። ቢከብዳችሁም፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የማያስተምር ሰው ሁሉ፡ ሀሰተኛ ነብዪ ነው። ምንም ያህል የተወለወለ ቢሆን ግድ የለኝም፡ የውሸት ትንቢት ነው። አዎን ውሸት ነው።

107 "ኦህ፡ ሰምሽ መጽሐፉ ላይ ሰለተመዘገበ ሌላው ችግር የለውም ይሉሻል።" ሰምሽ አሰራ ሁለት መጽሐፍ ውስጥ ሊመዘገብ ይችላል። በህይወት መዝገብ እስካልሰፈረ ድረስ ግን፡ ጠፍተሻል! ጥሩ ሰው ልትሆን ትችላለህ፡ ምንም ያህል በሰነ ምግባርህ የማትነቀፍ ታማኝ እና ንጹህ ልትሆን ትችላለህ፡ ይህ ሁሉ ግን የትም አያደርስህም።

108 በሰብዕና ደረጃ፡ ዔሳው ከያዕቆብ ይልቅ በሁለት እጥፍ የተሻለ ነበር፡ ሰለ አይነሰውሩ ሰለ ሽማግሌው አባቱ እና ሰለ ቤተሰብ ሁሉ ያሰባል። ያዕቆብ ግን፡ የእናቱ ቀሚሰ የሚከተል አይናፋር ሴታ ሴት ልጅ ነበር። እግዚአብሄርም እንዳቸው ገና ሳይወለዱ፡ "ያዕቆብን ወደድሁ ዔሳውን ግን ጠላሁ፡" አለ። ሮሜ 8 ላይ ይናገራል። በትክክል።

109 እግዚአብሄር በሰው ዘንድ ያለውን ያውቃል። በቤት ክርሰትያን ዘንድ ያለውም፡ ያውቀዋል። እኛ ግን በህይወት እንጀራ፡ በእግዚአብሄር ቃል እንጀራ የምንኖር ሰዎች ነን። የሐይማኖት ተቋም ያልሆንነው፡ ለዚህ ነው።

110 አሁን ጽፌ የያዝኩት ትንሽ ሌላ ምሳሌ ነገር ይዣለሁ… እና ገለጻ ላድርግላችሁ። "ታላቂቱ… " በራዕይ፡ 19:2። ያሰመርኩባት ትንሽ ነገር አለች። እና አሁን እንከታተል።

> ፍርዶቹ **እውነትና ጽድቅ ናቸውና፡ ታላቂቱን ጋለሞታ ሰለ ፈረደባት፡** በዝሙትዋ **ምድርን ያጠፋችይቱን፡ የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ሰለ** ተበቀለ። (ይህ ማለት የካቶሊክ ቤተ እምነት መጨረሻዋ ነው።)

111 አሁን እዚህ ጋር፡ ሌላ ልታሰተውሉት የምንፈልጋችሁ ነገር አለ፡ ይህም የሐይማኖት ተቋም—የሐይማኖት ተቋም በመጽሐፍ ቅዱስ ውሰጥም፡ የምናየው… መጽሐፍ ቅዱስ የሐይማኖት ተቋም እንዲኖር አይፈቅድም። የሐይማኖት ተቋም ከካቶሊክ ቤተክርሰትያን የመጣ ነገር ነው። የመጀመርያ የሐይማኖት ተቋም እናት ካቶሊክ ናት፡ ሌሎች የሐይማኖት ተቋማት አንድ በአንድ ከእሷ የወጡ ናቸው። አዎን፡ ይህ ነገር ትንሽ ቆንጠጥ ያደርጋል። ዘወትር ቆንጠጥ ማድረጉ ይቀጥላል፡ አያችሁ። እኔ ግን—የሐይማኖት ተቋም ከዲያብሎሰ የተወሰነ ነው እንጂ። ከእግዚአብሄር የተወሰነ ነገር እንዳልሆነ እንድታዩ እፈልጋችኋለሁ።

112 የእግዚአብሄር ቤተክርሰትያን፡ የማትከፋፈል… አንድ አካል፣ አንድ ትምህርት እና ተሰፋ ያላት፣ አንድ ፍቅር ያላት ናት። የሕያው የእግዚአብሄር ቤተ ክርሰትያን እንዲህ ናት። በዙርያችን፡ያሉ ነገሮች እንዳለ ቢኖሩም፡ እኛ አንድ

ነን! አዎን አንድ ነን። ወንድሜ ሆይ፡ ሜቶዲስት ይሁን ባፕቲስት፡ ዳግም ተወልዶ መንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ከሆነ፡ ወንድሜ ነው። ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን እየተራመድን ነው። አዎ። አዎን፡ ወንድሜ። ልዩነት አትፍጠሩ።

113 ሙሴን እዩት። አንዳንድ ጊዜ ዞሬ አይቼ እንዲህ እላለሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እነዚያን አክራሪ የጴንጤቆስጤዎች ሰብሰባ ታውቃቸዋለህ፡ ለምን እንደዚህ አይነት ጉባኤ ትሄዳለህ?" ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሙሴ የእስራኤል ልጆችን ሲያያቸው። ፈርኦን ባየበት በዚያው መስኮት ሙሴ አሻግሮ አያቸው። ፈርኦን ሲያያቸው ጭቃ-የሚያቦኩ ተራ ሰዎች አርጎ ተመለከታቸው፡ ሙሴ ሲያያቸው ግን የተሰፋ ቃል እንዳላቸው ያውቃልና። እንደተመረጡ የአምላክ ልጆች ቆጠራቸው። እንዴት አወቀ? ከእግዚአብሄር ቃል አውቆ። በእምነትም... ፈርኦን ለመባል ተቃርቦ፡ ዓለም ከእግሩ በታች ወድቃ፡ አልጋ ወራሽ ሆኗል፡ ወጣቱ ሙሴ እንደ ንጉስ ነገሰት፡ ቁጭ ብሎ አርፎ ወይኑን እየጨለጠ፡ በአርባ አመቱ፡ እንደ አምባገነን፡ ወይም እንደ ዓለም ንጉስ፡ ደስ በሚያሰኙት ቆነጃጅቶች ተከቦ፡ ሁሉንም በእጁ ጨብጦ፡ ይዟል። በውጭ ወደ ነበሩት ጭቃ-አብኩዎች ሲመለከት ግን፡ እኔም ከእነርሱ ጋር አንዱ ነኝ አለ። ሃሌሉያ! ይሄው ነው። እንደ እነርሱ እንደሆነ አስቀድሞ አውቋል። በእምነት፡ በኩል ብቻ፡ መረጠ!

114 ሰው ሁሉ የየራሱ ምርጫ ይመርጣል። እናንተም መምረጥ አለባችሁ። አሁንም ትመርጣላችሁ። ጠዋት ላይ ትመርጣላችሁ። በህይወት ከቆያችሁ፡ ነገ ማታም ትመርጣላችሁ። አንድ ቀን ትመርጣላችሁ። ወንድሜ፡ እኔም ከብዙ ጊዜ በፊት መርጫለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን መዝገበ ቃላቴ አድርጌዋለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት መዝገቤ ነው። መጽሐፍ ቅዱሴ የእግዚአብሄር ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ኑሮዬ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አቋሜ ነው።

115 ስለዚህ፡ ሙሴ የእስራኤልን ልጆች ባያቸው ጊዜ፡ እንዲህ ብቻ አልተናገረም። "ኦህ፡ እንዴት ያለ ድንቅ ህዝብ ነው። ክፉ ነገር አላየሁባቸውም። ኦህ፡ ፈጽሜ መጥፎ ነገር አልናገራቸውም፡" ብቻ አላለም። ዛሬ ብዙ ሰዎች እንደሚከተለው ብቻ ናቸው። "ኦህ፡ ጴንጤቆስጤዎች'ኮ መንፈስ ቅዱስን የተሞሉ ሰዎች ናቸው፡ በመለኮታዊ ፈውስ ያምናሉ፣ ኦህ፡ እኔ—እነሱን—ምንም አልቃወማቸውም።" የሙሴ ግን እንዲህ አይደለም። ግብጽን በመተው ከእነርሱ ጋር አንድ ሆነ። በወንድሞቹ መካከል መጣ። ከእነርሱም ጋር አንድ ሆነ።

116 ወንድሜ፡ እኔም ምርጫዬ ይህ ነው። ጥቂት ይሁኑ፡ እፍኝ ያክሉ፡ መንገዴ ከተናቁት የጌታ ልጆች ጋር አደርጋለሁ። የተሰፋ ቃል አላቸው፡ ሰሞቻቸው በበጉ የሕይወት መዝገብ ላይ ተጽፎ አይቻለሁ። ወንድሞቼ ናቸው። አዎን ናቸው። ምርጫህን ምረጥና አብረሃቸው ሁን። ቢሳሳቱም ባይሳሳቱም፡ አብረሃቸው ጽና። ከተሳሳቱ፡ አቃናቸው። አዎን። አየህ፡ አውግዘሃቸው። ወደ ውጭ ጎትተሃቸው በፍጹም አይቃኑም።

117 ቻርሊ፡ ስለ ወንድም አለን፡ እሳት... ማለቴ ደም በእጁ ላይ ታየ ብለው ሲያወሩ። እኔ ልንገራችሁ፦ "በፍጹም ወንድም ኤ/ኤ/ አለንን፡ በፍጹም እናንቄው አላውቅም።" ልንገራችሁ፦ "እኔ እንደ ኤ/ኤ/ አለን መሰበክ ብችል ኖሮ፡ የፈውስ አገልግሎት ባላደርግኩ ነበር።" ይሁን እንጂ፡ ደም በእጃችሁ ከታየ፡ የመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማስረጃ ነው ወደ ማለት ሲመጣ አልስማማውም፡ ይሄን እቃወመዋለሁ። ስለ ወንድማማችነት ስንናገር

ግን፡ ወንድሜ ነው። ስልፉ ላይ ትከሻ ለትከሻ ተሰጣጥተን አብረን እንዋጋለን። አዎን። ከተሳሳተ፡ አቃናዋለሁ። ካልተሳሳተ ግን፡ ስሕተቱ እኔ ጋር ከሆነ፡ እንዲያቃናኝ እፈልጋለሁ። አካሄዳችን—አሰራራችን ይህ ነው። አሁን ተከታተሉ።

... ሴቲቱ **የባቢሎን ምሰጢር፡... የጋለሞታዎች እናት** ነበረች...

118 ወዳጆች ሆይ፡ ቤተክርስቲያን ዛሬ እንዴት እንደሆነች ታያላችሁ፡ ዛሬ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በፈለጉት መንገድ እንዴት እንደሚኖሩ ታያላችሁን? አሳማ አሳማውን ሲውጠው፡ የሚገሰጽ የለም፡ "ጉዞህን ቀጥል፡ አልተሳሳትክም።" "ለምን፡ ምንም ጉዳት የለውም። ለምን፡ ለምን ታካብዳለህ።" ባህላቸው እንዲህ ነው። አስተምህሮቻቸውን ተመልከቱ። አሁን እንድትከታተሉ... እፈልጋለሁ። ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ ቪድዮ ቤት እንዲገቡ የፈቀደች ብቸኛዋ ቤተ እምነት ካቶሊክ መሆንዋን ታውቃላችሁ? ሜተዲስቶች ይሄን ፈጽመው አያስቡትም ነበር። ሌሎች የሐይማኖት ተቋማት፡ "አይሆንም! ይህ የሰይጣን ነው ይሉ ነበር።" አሁን ምን እንደተፈጠረ ይገርመኛል። በጣም፡ ይገርመኛል።

119 ያኔ ታስታውሳላችሁ፡ ወጣት ካቶሊክ ሴቶችን ስትቀጥሩ፡ አጭር ነገር ለብሰው... (በእኔ እድሜ ያላችሁ ጎልማሶች፡ ታውቁታላችሁ።)... ከጉልበት-በላይ ተገላልጠው ሲወጡ እናያቸው ነበር። ያ ዘፋኝ፡ ዛሬ ማታ፡ በሲኦል ውስጥ፡ እንዳለ እገምታለሁ። አላውቅም። እኔ ፈራጁ አይደለሁም። ብቻ ግን ያቺን ቆሻሻ ዘፈን ሰርቶ ምንም ሳንሱር ሳይደረግ፡ በየራድዮ ጣብያው፡ "ሴት ልጆች፡ ወዝወዝ፡ ከፍ ከፍ እርጉ፡ ግለጡት ውብ ጉልበታችሁ አሳዩ" እየተባለ ይዘፈን ነበር። የቆየ ነው፡ ያን ዘፈን ሲለቀቅ ሰንቶች ታስታውሳላችሁ? የድጡ-ጅማሬ ከዚያ ነው። አዎን ከዚህ ነው። ሴቶችን ከዚህም ከዚያም ሰብስበው፡ ሴቶቹ ያልሆኑትን ነገር እንደሆኑ አድርጎ ለማቅረብ እና የማይረባ ነገር ለማልበስ የውስጥን ልብስ የሚሰፋ ባለሞያ፡ ከቴክሳስ ድረስ አምጥተው፡ የማይረቡ ነገሮች ለብሰው እንዲታዩ ያደርጓቸዋል። ይህ ነገር መንፈስ ነው። ምን ጠቀመን? አሁን ስተት ብሎ ተሰፋፍቷል።

120 በቀደምለት፡ አንድ ሰው ያጫወተኝ ነገር አለ። ሰውየው ስለ ልጁ ተጨንቆ፦ "ምን ማድረግ እንዳለብ አላውቅም ይላል። እጅግ ቅን፡ እና መልካም ልጅ አለኝ፡ አሁን ግን ልጄ እጁ ላይ ያረፈ ነገር ሁሉ መሰረቅ ጀምሯል" አለኝ።

"ለምን? " ብዬ ጠየቅኩት፤

"ከሌቦች ጋር መዋል ጀምሮ ነው አለኝ።"

121 ከሌባ ሰው ጋር ከዋላችሁ፡ እናንተም ሌባ ትሆናላችሁ። ኬንታኪ ውስጥ ያደገች እናቴ ስትተርት፡ "ማን እንደሆንክ እኔ እንድነግርህ፡ ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝ፡" ትለኝ ነበር። ለምሳሌ—ምናምንቴ ኮረዳ... ወይም ሴት፡ አምጥታችሁ፡ ለመልካም እና ለጨዋ ወንድ ልጅ—ብትድሯት፡ ሳይውል ሳያድር ይቀየራል። ከሁሉ በፊት የሚሆነው እንደ ቁጡ ውሻ መበሳጨት ነው። በጓደኛ ምክንያት ማንነትህ በደንብ ይለያል። ስለዚህ እራሳችሁን ለዩ! "ከመካከላቸው ተለዩ፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ፡ "የተለያችሁ ሁኑ!" አዎን ተለዩ።

122 ህዝባቸውን ገደል ለመክተት የተበላሹ የሐይማኖት ተቋም ከሆኑ ተለዩ... ባለፈው ቀን፡ ዝነኛ የባፕቲስት ቤተ ክርስትያን ውስጥ፡ ሰውየው አልቻለም።

ሰባኪው፡ የሲጋራ ሱስ ስላለበት ከሀያ ደቂቃ በላይ መታገስ አቅቶት፡ ጉባኤውን አቋረጠ። ጉባኤው በሙሉ አብሮት ወደ ውጪ ወጣ። ፓስተሩ እና ሰዎቹ፡ በመደዳ ቆመው ሲጋራቸውን አጭሰው፡ ወደ ጉባኤ ተመልሰው ገቡ። ኮንግሪጌሽናሊስት ቤተክርስትያን ገባሁና፡ ትልቅ እና ዘርፋፋ ቀሚስ የለበሰ፡ ሰውዬው ቆሟል፡ ፑልፒቱን እንዲህ ተደግፎ፡ ተራራ ላይ ሄዶ ስላገኛት የአበባ ዝርያ፡ በተመለከተ፡ **እንዲህ** ተደግፎ ይናገር ነበር። ለእሱ ከዚያ የዘለለ ቁምነገር አልነበረም፡ ይሄን ተናግሮ ወጣ። በቃ። ጣቶቹ ሁሉ በሲጋራ ጭስ ቢጫ ሆኗል። ሰውየው ከሌሎች ሴቶች ጋራ የሚጫወተው፡ የጨዋታ ዓይነት በተመለከተ ተናገረ... ካርዶች ደርድረው—የሚጫወቱት የጀርመን ጨዋታ፡ ስሙን ረሳሁት፡ ንገሩኝ እስኪ ታውቁታላችሁ? አቤት... ደርድረውት፡ አሁን አስታውስኩት። ፒኖክል ይባላል፡ ፒኖክል የካርታ ጨዋታ ይጫወቱ ነበር። ልክ መሰለኝ። አዎን፡ የምታውቁት ነገር ነው። ተራ የካርታ ጨዋታ ነው። ምድር ቤት ውስጥ፡ ፒኖክል ይጫወታሉ! በጌታ፡ ስም! ለካ መሰረታቸው ይህ ነው። ለካ ለዚህ ነው! ይህ ምን ያደርግላቸዋል? የሎተሪ ዕጣ እንዲወጣ በየ ቁማር ቤት እየዋሉ ስለ ካቶሊክ ቤተ እምነት ማቅራራት ምን ያደርጋል። እናንተም፡ ፕሮቴስታንቶች ልክ እንደነሱ ርኩስ ሆናቿል፡ ምን ማለት ይቻላችኋል? እነሰራ ጀበናን "ቆሻሻ" አትላትም። በጭራሽ አትላትም። እናንተው፡ እነዚህ ነገሮች እያደረጋችሁ፡ "ፕሬስባይተርያን ነኝ። ሜተዲስት ነኝ፡" ትላላችሁ። ዳግመኛ እስክትወለዱ ድረስ ተራ ናችሁ። አዎን። ከተወለዳችሁ በኋላ ግን፡ ይገባችኋል፡ የምታደርገው ነገር ስሕተት ነው የሚላችሁ ነገር እንዳለ ይገባችኋል፡ እናንተም ሳትበላሹ ገና-ጊዜ እያላችሁ ከዚያ ነገር ትወጣላችሁ። እውነት ነው ታውቁታላችሁ። በትክክል። አዎን፡ ወዳጄ። ያ ክፉ ልማድ እንዲሁ ይጠፋል። ለምን?

### ... የጋለሞታዎች እናት...

123 አንድ ቀን ይህች አሮጌት እናት፡ "ገብቶሻል? የኔ ማር፡ ምንም ብንሆንም'ኮ፡ ሁላችንም አንድ ነን፡" ማለቷ የማይቀር ነው። ያኔ ምን እንደሚፈጠር ታውቃላችሁ? አሁን እንደጀማመሩት የአብያተ ክርስትያናት ኮንፌደሬሽን አንድነት ይደረጋል። እናንተን የመሳሰሉ ታናናሽ መንጋዎች እጣ ፈንታቸው ምን እንደሚሆን ታውቅላችሁ? ሰዎች ሆይ፡ ዋጋ ትከፍላላችሁ። በትክክል ዋጋ ያስከፍላችኋል።

124 ይሁን እንጂ አይዞአችሁ፡ በጉ ድል ይነሣዋል። የጌቶች ጌታና፡ የነገሥታት ንጉሥ ስለ ሆነ ድል በጉ ይነሣል፡ ቤተ ክርስትያንም በጌታ እንጂ፡ በሐይማኖት ተቋም አትመራም። ቤተ ክርስትያን ላይ ወርቃማው የመንፈስ ቅዱስ ዘይት ያፈስሳል። ወንድሜ ሆይ፡ ከሰማይ እሳት ይዘንባል፡ በዘመናችሁ ሁሉ ያላያችሁት፡ ድንቆች እና ምልክቶች ይሆናሉ። አዎን፡ ይሆናሉ። "ታናሽ መንጋ ሆይ፡ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና፡ አትፍራ።" አዎን፡ አትፍራ። ይሄውልህ። "እስከ መጨረሻ የሚጸና ይላልና!" መንገድህን ጠብቀህ ተጓዝ። አይዞህ። መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ነውና። አሳብህ ሁሉ ወደ ቀራንዮ አድርግ።

125 ተከታተሉኝ። አንድዳንድ ልማድ አላቸው። መዘርዘር እንችላለን። ወደ ፕሮቴስታንት ቤተ እምነታት ሳይቀር። ሾልከው የገቡ፡ አንዳንድ ሰነ ምግባሮች አሏቸው። ይህም፡ የካቶሊክ ሴቶች... ቤተ ክርስትያን ሲሄዱ አንዳንድ

ልማዶቻቸውን ማድረጋቸው፡ ማለት በራሳቸው ላይ ትንሽ ጨርቅ ጣል ብቻ ያድርጉ እንጂ። “እርብ እለትም ስጋን አይብሉ እንጂ፡” አጭር ቀሚስ መልበሳቸው ችግር የለውም። ኧረ፡ እናንተ፡ እስኪ ቃሉን አሳዩኝ። ቤተ ክርስትያን ስትገቡ ራሳችሁን በጨርቅ መሸፈን ከየት አገኛችሁ? ሐሰተኛ ትንቢት ነው። ቤተ ክርስትያን ስትገቡ ቆብ አርጉ የሚል ጽሑፍ ከየት አገኛችሁት? ለእናንተ፡ ለወንዶች፡ እናገራለሁ፡ ቆብ በራሳችሁ ላይ ስታጠልቁ፡ ክርስቶስን ታሳፍራላችሁ። እናንተም ሴቶች መጎናጸፊያ ተሰጥቷችሁ ሳለ፡ ራሳችሁን በቆብ ወይም በጨርቅ ሸፍኑ የሚል አሳዩኝ። ጸጉራችሁ ራሱ መጎናጸፍያቹ ነው! እናንተ ግን ትቆርጡታላችሁ። ንገሩኝ ስትሏቸው? ኧረ፡ ተው ባክህ፡ “ይሄ’ማ ኋላቀርነት ነው ይላሉ።” እንግዲያውስ፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ! የእግዚአብሄር ቃልም የነጠረ ነው።

126 በቀደምለት፡ በጨዋታችን መሃል፡ የኢየሱስን እግር አጥባ፡ እንደምታውቁት፡ በጸጉሯ ሰላበሰች ሴት—እየተጫወትን፡ ነበር። እና፡ “አንድ ሴት እግር አጥባ በጸጉሯ ለማበስ ብቸኛው ዘዴ፡ የምታብሰበትን በቂ ጸጉር ለማግኘት፡ በጭንቅላቷ እንስክትቆም ድርስ በመውረድ ብቻ ነው።” በትክክል። እዚህ የሚያደርጉት ነገር ሰታዩ፡ ኧረ፡ እጅግ ያሳዝናል... ከባድ ብርድ ላይ፡ እርቃናቸው እያሳዩ፡ ብጣሽ ኮት፡ ጣል አርገው ወዲይ ወዲህ ይላሉ።

127 “ሴቶችን ብቻ ነው’ዴ ምትወቅሰው?” ትሉኛ ይሆናል፡ መወቀስ አለባችሁ።

128 ሚስቶቻችሁ እንዲህ እንዲሆኑ የምትፈቅዱ ወንዶች አላችሁ፡ ወንድሜ፡ ስለ አንተ—ምን እንደምልህ አላውቅም። በእውነት፡ እልሃለሁ።

129 ፓስተሮች፡ እዚህ ትኖራላችሁ ብዬ አላምንም። እንዲህ አይነቱ ካለ፡ ወደ እኔ እንዲመጣ፡ ና ይልሃል፡ በሉልኝ። አያችሁ? ጉባኤው በዘልማድ እንዲቀጥል ከመፍቀድ በቀር ለክርስቶስ ክብር የለውም... ምናልባት... እሱ ሳያውቅ ሊያደርጉ ይችላሉ፡ እሱ ካላስጠነቀቃቸው ግን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ለመሆን አይበቃም። አዎን በትክክል አይበቃም። የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ለመሆን አይበቃም። የክርስቶስ አገልጋይ በመጽሐፍ ቅዱስ ጉዳይ የማይደራደር ሊሆን ይገባዋል። አዎን። ይሁን እንጂ፡ ብዙዎች በዘፈቀደ ይሄዳሉ።

130 እና አሁን፡ የመጀመርያ ማወቅ ያለባችሁ ነገር ፕሮቴስታንቶች ዘንድ ገብቶ፡ ተቀብለውታል። አንተ በጎ ሜቶዲስት፣ አንተም ባፕቲስት፣ እና ፕሪስባይቴሪያን፣ ወይም ናዝሬት፣ ፒልግሪም ሆሊነስ፣ እና ሁላችሁ፣ ያው ናችሁ፡ ከአንደኛይቱ ስድስት፡ ከሌላይቱም ግማሽ ደርዘን፡ ይወጣሉ። “የጋለሞታዎች እናት፡” ማለት ይህች ናት። “መነሻችሁ ከዋና መሰርያ ቤት እስከሆነ ድረስ፡” የሐይማኖት ተቋማችሁ፡ ምን ልዩነት አለው? አያችሁ? ልዩነቱ ብዙ ነው። **ይሄን** ዋና መሰርያ ቤት፡ እሰጀምሮ እያውቅም። ምናልባት የእናንተ ምድራዊው ከዋና መሰርያ ቤት ጀምሮ ሊሆን ይችላል፡ ሰማያዊቱ ግን እንዲህ አይደለችም። አፈጣጠራችሁ ይወስነዋል። እውነት ነው።

131 አሁን፡ ይሄኛውን ለመዳሰስ ጊዜ ያለን አይመስለኛም፡ ምናልባት ለጠዋት ብተወው ይሻላል። እሺ፡ አጠር ያለውን ወስደን እንቀጥል። “የውሃ ጥምቀት፡”

እና “አስቀድሞ መወሰን።” ሌላ፡ ብዙ፡ ርዕሶች፡ በዝርዝር፡ ይዣለሁ። ስለዚህ፡ “የሴቶች ሰባኪዎችን፡” በሚመለከት፡ አጠር ያለች ርዕስ እንውሰድ።

132 እናንተ፡ ሴቶች ሰባኪዎች፡ ስሜታችሁን መጉዳት ባልፈልግም፡ አንድ ነገር ግን፡ልንገራችሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እንዲት ቃል አውጥታችሁ አሳዩኝ። አዎን፡ “ሴት እና ወንዶች ልጆቻችሁ ትንቢትን ይናገራሉ፡” የሚለውንን ቃል፡ ከየት ወዴት መውሰድ እንደምትፈልጉ፡ አውቃለሁ። ፓስተራችሁ፡ “ትንቢት” የሚለው ቃል ትርጉሙ ካላወቀው፡ ማወቅ የሚገባውን—አላወቀም። ስለዚህ መሰበክ ትችያለሽ ብሎ ሊያስተምርሽ፡ መድረክ ላይ ለመውጣት ጥሪ የለውም። አየሽ? ከዘፍጥረት ጀምሮ፡ እስከ ራዕይ ድረስ፡ ፈጽሞ የተኰነነ ነው። ተከታተሉኝ አንድ ነገር ላሳያችሁ።

133 አንደኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2:11 ክፈቱልኝ። በተጨማሪም ሐዋርያት ስራ 2 ትከፍታላችሁ፡ ምን ማለት እንደሆነ ብደንብ አርገን እንማራለን። እሺ። መጽሀፍ ቅዱስ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደሚል—በጽሞና ተከታተሉ።

134 አንድ ሰው፡ ደጋግሞ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አንተ‘ኮ ሴቶች እንዲሁ ስለምትጠላቸው ብቻ ነው፡” ይለኛል። እኔ ሴት ጠል አይደለሁም። እኔ የምጠላው... ሴቶች ያልተገባቸው ስፍራ ለመውሰድ ሲጣጣሩ ማየት አልወድም።

ሆዋርድ የመርከብ ስራ ድርጅት፡ በኦሃዮ ወንዝ ካሉ ድርጅቶች ሁሉ ስኬታማ የሚባል የመርከብ ስራ ድርጅት ትዝ ይላችኋል? ሴት አስገብተውበት። ውጤቱ ተመልከቱት።

ሴት ትምረጥ ብለው መብት ሰጧት፡ ውጤቱን ተመልከቱ።

135 ልንገራችሁ። ሴቶችን መውቀስ ብቻ አይደለም። በዚህ ላይ እናንተም ወንዶች ጭምር አላችሁበት። ወንድሞቼ፡ አንድ ነገር ልንገራችሁ። ይህ አገር የሴትነት አገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ወይም እናንተ በመረጣችሁት መንገድ፡ ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። እሺ... በገንዘባችን ላይ ምን ይታያችኋል? ሴት። ከምን የመጣች ሴት? ራእይ፡ ውስጥ፡ ታገኟታላችሁ። ነገሯ ሁሉ፡ መነሻዋ፡ ቁጥር አስራ ሶስት ነው፡ አስራ ሶስት ከዋክብቶች፣ አስራ ሶስት ጭረቶች፣ አስራ ሶስት ግዛቶች አሏት። ከጅምሩ፡ አስራ ሶስት፡ ሁለመናዋ አስራ ሶስት ነው። ራእይ ዮሃንስ ምዕራፍ 13 ላይ ትገኛለች። የአስራ ሶስት፡ ሴት ናት!

136 ጌታ ያኔ፡ በ1933... አሁን ቸርች ኦፍ ክራይስት ያሉበት ቦታ፡ ድሮ የሜሶናውያን የነበረበት ቦታ ላይ በምንሰበሰብ ጊዜ፡ ጌታ አንድ ራእይ አሳይቶኝ “ጀርመን የማዢኖ ላይን ምሽግ ትቆጣጠራለች” ብዬ ትንቢት ተናግሬ ነበር። ብዙዎቻችሁ ታስታውሱታላችሁ። ሁሉም እዚያ ውስጥ እንዴት እንደሚመሽጉ እና አሜሪካውያን እዚያው መሰመር ላይ ታላቅ ድብደባ እንደሚደርስባቸው። ምን እንደሚፈጠር፡ እና ሩዝቬልት እና ስለነሱ ነገሮች፡ እንዴት እንደሚሸሸ እና አራተኛውን የሰልጣን ዘመን ምን እንደሚያደርገው ተናግሬአለሁ። በተፈፀምበት መንገድ፡ በትክክል ተናግሬአለሁ። እንዲሁም መኪኖች እንቁላል እየመሰሉ እንደሚቀጥሉ፣ መጨረሻዎቹ ቀናት ድረስ የእንቁላል ቅርጽ እንደሚኖራቸው። ሌላ የተናገርኩት፡ “መኪናቹ በመሪ የማይነዱበት ዘመን እንደሚመጣ። ሌላ ነገር ይነዳችኋል።” ለደህንነት ሲባል፡ በሪሞት ኮንትሮል የሚነዱ መኪኖች፡ አሁን እያስተዋወቁ ይገኛሉ። በትክክል።

ከተማ ውስጥ መግባት አትችልም... ከዚያ፡ ሃያ-ማይል ዞን፡ ሃያ ማይል ድረስ መሄድ ይቻላል። ሪሞት ኮንትሮል ስላለው፡ ግጭት አይኖርም። አያችሁ፡ እንዲሁ ይሆናል፡ አሁን ጀምሯል። ሌላ የተናገርኩት፡- “አስታውሱ፡ በዚያች ቀን፡ የዘመን ፍጻሜ ከመሆኑ፡ የዘመን ፍጻሜ ከመሆኑ በፊት፡ ታላቅ ሴት ትነሳለች፡ ይህች ሴት... አሁን፡ ሁላችሁ ይህን ጽፋችሁ ያዙ። ታላቅና ኃያል ሴት፡ ትነሣለች፡ ሴቲቱ ፕረዚደንት ትሁን፡ ዲክታተር አላውቅም፡ በዩናይትድ ስቴትስ ግን ታላቅ ሴት ትነሳለች። ይህ ነገር፡ አትርሱ፡ **ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል**። ሴቲቱ በሴቶች ተጽእኖ ስር ትሰምጣለች።” አያችሁ?

137 ትስታለች። መንገድ ለማን ይጠርጋል? ልንገራችሁ። መንፈሳውያን ሁኑ። ለመረዳት... ፍቀዱ። ተከታተሉኝ። ምን እያደረገ ነው? ካቶሊክ ቤተ እምነት የምትገባበት ስፍራ ለማበጀት ነው። ገባችሁ? የፊልም ተዋንያን እና አሁን የመጡ የተለያዩ ነገሮች ታመልካላችሁ። ያኔ እኔ የሰበኩትን ሰብከት አስታውሱ? ከዓመታት በፊት—የአሜሪካን መንግሥት ለመጣል፡ ዩናይትድ ስቴትስ፡ በተወረረች ጊዜ፡ ማርጂን፡ ታስታውሳላችሁ። ከሴቶች፡ ከወይን እና ከክፋ ጊዜ ካዳንናቸው በኋላ እንዴት በፓሪስ እንደተነሳ ተናግሬ ነበር። ከዚያ ተነሰቶ ሆሊውድ ውስጥ ችቦውን ለኰሰ። አሁን፡ እኛ ሞዴሎችን ፍለጋ ፓሪስ ከመሄድ ይልቅ፡ ሞዴሎችን ወደዚህ ይልኩልናል። በምን መንገድ? እንዲህ ነው... ልጆቻችሁ ወደ ቪድዮ ቤት እንዲሄዱ አትፈቅዱላቸውም፡ ነገር ግን በቴሌቪዥን መሰኰት መጣብን፡ በዚህ መንገድ መጥቶ ሁሉንም በከለ፡ እንደፈለገች እንድትንቀሳቀስ አደረጋት። እና ዛሬ ላይ ሁላችንም፡ ሴቶች እና ወንዶች ህጻናት፡ ሁላችንም የቴሌቪዥን ተዋንያን ተከታይ አደረገን። ለምንድነው? መንገድ ለመጥረግ። ወዳጄ፡ ከተማው ውስጥ በመደዳ ያሉ መጠጥ ቤቶች ወደ ገሃነም ከሚልኳቸው ሰዎች ይልቅ፡ አንዲት-ታዋቂ ሴት የምትልካቸው ሰዎች እጅግ ይበዛሉ። እውነት ነው። እስኪ ከመካከላችሁ፡ ማንም ይሁን ወንድ እርቃኗን መንገድ ላይ ስትወርድ ይያት፡ ጤናማ እና ትክክለኛ ወንድ ከሆነ፡ ሴቲቱን አይቶ በውስጡ የሆነ ነገር ሳይመላለስበት አይቀርም። እውነተኞች እነሁን። እኔ ምንም አይመስለኝም...

138 እኔ መንፈስ ቅዱስ ከተሞላሁ ዓመታት አለፉ። ልንገርህ እርቃን የሆነች ሴት ለማየት አይቻልህም... እንደምታውቁት፡ መኪናዬ ውስጥ—መስቀል አንጠለጥላለሁ። እና አንድ ሰው “ካቶሊክ ነህ ወይ፡” ብሎ ጠየቀኝ? መስቀል የካቶሊኮች ብቻ ነው ያለው ማን ነው? መሰቀል ማለት “ክርሰትያን” ማለት ነው።

139 የካቶሊካውያን መታወቅያ ምልክታቸው እነ ቅዱስ ሲሲልያ እና ሌሎች ናቸው። እኛ ግን እንዲህ ያሉ ነገሮች አናምንም። እምነታችን ክርሰቶስ ነው። የሚያመልኳቸው ብዙ ዓይነት ሙታኖች አሏቸው። የመናፍስታዊነት ጥጉ ይህ ነው። ሙታንን ከማምለክ፡ የዘለለ አይደለም። እንዲህ ዓይነት አምልኮ የለም፡ የለን።

140 እንዲህ አልኩት፡ “ቆይ... የመጀመርያው ጳጳስ፡ ጴጥሮስ ነበር ወይ? ብዬ፡ ቄሱን ጠየቅኩት።

“አዎን ነበር፡” ብሎ መለሰልኝ።

141 ታድያ፡ “ጴጥሮስ ራሱ፡ ‘ሰው ከሆነው ከክርስቶስ ኢየሱስ በቀር በሰው እና በእግዚአብሄር መካከል ሌላ የለም ለምን አለ’? እናንተ ግን አምስት ሺ ሙታን ሴቶች፡ እና ሌሎች ሌሎች ነገሮች፡ መካከለኛ አድርጋችኋል። እስኪ ንገረኝ? ” ለዚህ የሚሆን መልስ የላቸውም። እንዲህ ናቸው። አዎን ናቸው።

142 ሌላው ስረተ እምነታቸው ነው፡ ሐሰተኛ ትምህርታቸው፡ ሐሰተኞች የፕሮቴስታንት ነብያት ተነስተው ትምህርታቸውን እያስተማሩ ነው፡ እናንተ ፕሮቴስታንቶችም ሳታጣሩ ትውጡታላችሁ። አዎን በትክክል። የሐይማኖት ተቋማት እና የጥምቀት እና፣ ፈጽሞ የእግዚአብሄር ቃል ያይደለ፡ እናንተ የተቀበላችሁት ብዙ ዓይነት የአምልኮ መልክ አለ። በቅዱስ ቃል መሰረት፡ ስሕተት ነው፡ እናንተ ግን ትለቃቅሙታላችሁ። እውነት ነው።

143 አሁን ስለሴቶቹ ሰባኪዎች ይህን አዳምጡ። እሺ። አንደኛ ጢሞቴዎስ ላይ፣ አንደኛ ጢሞቴዎስ 2:11 እንከፈት። ምን እንደሚል አዳምጡ።

> ሴቶቻችሁ **በነገር ሁሉ እየተገዙ በዝግታ ይማሩ።**
>
> **ሴት ግን** በዝግታ **ትኑር እንጂ፡ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን፡ አልፈቅድም።**

144 በመጽሐፍ ውስጥ ስለመጻፉ እኔ አልጠየቅበትም። የምጠየቀው የተጻፈውን ነገር በመናገሬ ብቻ ነው። እያችሁ? እያችሁ ወይ?

> ሴቶቻችሁ በነገር ሁሉ **እየተገዙ በዝግታ ይማሩ።** (ወደ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ገብታችሁ ተመልከቱ፡ እዩት። እያችሁ? )
>
> **ሴት ግን ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ፡ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን፡** (ፓስተር፣ ዲያቆን፣ ወይም) መሰል ነገሮች አትሁን፡ **በዝግታ ትኑር እንጂ፡ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን፡ አልፈቅድም።**
>
> **አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፡** በኋላም **ሔዋን ተፈጠረች።**

145 ታውቃላችሁ ሴቶች? ይሄን፡ አድምጡኝ። እግዚአብሔር፡ ለአንድ ወንድ ሊሰጠው ከሚችል ነገር ሁሉ የተሻለ ስጦታ መልካም እና ጻድቅ የሆነች ክርስትያን ሴት ናት፡ ባይሆን ግን ሌላ ይሰጠው ነበር። አዎን፡ በትክክል። እያችሁ? ሴቲቱ በኦሪጂናል ፍጥረት ውስጥ እንኳን አልነበረችም። ሴቲቱ ከወንድ-ተገኘች እንጂ። በእግዚብሔር መጀመርያ ከተፈጠሩት ጋር አይደለችም። እግዚአብሄር፡ ወንዱን ሴት እና ወንድ አርጎ ፈጠረው። ከጊዜ በኋላ ለያቸው። ሰውየው እንስሶችን ሁሉ ስያሜ ሰይሞ ብዙ ዘመናት ከኖረ በኋላ፡ ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ፡ ከአዳም ጎን የተገኘች፡ የፍጥረት-ምርት፡ ሴት አድርጎ ለመስራት ከጎኑ አጥንት ወሰደ። “አዳም ቀድሞ ተፈጥሯልና፡ በኋላም ሄዋን ተፈጠረች።” አሁን ተከታተሉኝ።

> **የተታለለም አዳም አይደለም፡ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች።**

146 እግዚአብሄር አዳምን መረጠ። ዲያብሎስ ግን ሴቲቱን መረጠ። ዛሬም ምን እያደረገ እንደሆነ፡ ፊት ለፊት፡ አስተውላችሁ እዩት። እውነተኛዋ የጌታ ቤተ ክርስትያን፡ “ኢየሱስን!” ስትመርጥ፡ ጸረ ክርስቶስዋ ግን፡ “ማርያም!” ሁለቱም መንፈሶች አስተውሏቸው። እነዚህ ናቸው። ገብቷችኋል? “ቅድስት

ማርያም ሆይ፡ የእግዚአብሄር እናት፡ በሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፡ ስለ ሐጥያታችን ለምኚልን፡ በሞትን ጊዜ አማልጂልን። አሜን። ማርያም ሆይ፡ ለምኚልን!" ኧረ፡ በኢየሱስ፡ ስም! እያችሁ፡ "ሴት፡" የዲያብሎስ፡ መጠቀሚያ፡ ስትሆን እዩዋት። የሚመለክ፡ አምላክ፡ ክርስቶስ ብቻ ነው! ይሄው ነው። ይሄው ነው።

147 ሴት ፓስተር እና ሴት ዲያቆን፡ ማን ፈቀደላችሁ? "አዳም ቀድሞ ተፈጥሯልና፡ በኋላም ሄዋን ተፈጠረች።" የተታለለም አዳም አይደለም። የተታለለም አዳም አይደለም፡ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች። በነገራችን ላይ... ሄዋን ወድቃ እንኳን፡ ወድቄአለሁ ብላ አላሰበችም። "የወደቀችው የተታለለችው ሴቲቱ ናት።" ይህ ሁሉ፡ የሷ ነው፡ በጎዳናው ቀብር ባለፈ ቁጥር፡ መነሻው፡ በሴት ምክንያት ነው። ልጅ ኡኡ ባለ ቁጥር፡ በሴት ምክንያት ነው። ሰው በሞተ ቁጥር፡ በሴት ምክንያት ነው። የእያንዳንዱ ሽበት፡ በሴት ምክንያት ነው። ሞት እና፡ ሌላው ሁሉ፡ ምክንያቱ ሴት ናት። ስሕተት የሆነ ሁሉ፡ በሴት ምክንያት ነው። ከዛ በኋላ የቤተ ክርስትያን፡ ፓስተር፡ አንዳንዴም፡ ቢሾፕ ታደርጓታላችሁ። ያሳፍራል።

148 አሁን፡ በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ ወደ ሌላኛው ልውሰዳችሁ። እሺ? አንደኛ ቆሮንቶስ 14:32 እንክፈትና፡ ጳውሎስ የሚናገረውን እይተን፡ በቀጥታ፡ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ማየት እንቀጥላለን። ነገ ጠዋት ደክማችሁ ወደዚህ መምጣት እንዳትሰለቹ፡ አናቆያችሁም። እሺ። ላንብብላችሁ። ጳውሎስ በመገለጥ የሚያስተምር አስተማሪ እንደነበረ ስንቶች ታምናላችሁ? ይህ ነገር፡ ጳውሎስ፡ ለጢሞቴዎስ እንደጻፈለትም አስታውሱ። እሺ? በቀጥታ፡ 1ኛ ቆሮንቶስ 14፡32፣ እናነባለን። አሁን፡ የምናነበው፡ ከ14፡34፣ ጀምረን ይመስለኛል።

**ሴቶቻችሁ በማኅበር** ዝም **ይበሉ፡...**

149 የተናገረውን ሰምታችኋል?

**ሴቶቻችሁ በማኅበር** ዝም **ይበሉ፡ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ** እንጂ፤ **እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና፡...**

150 የዚህን ማጣቀሻ ትፈልጋላችሁ? ከፈለጋችሁ፡ ወደ ኋላ መለስ በሉና ከዘፍጥረት 3፡16 ጋር መሰማማቱን መርምሩ። በባልዋ ፈንታ እባቡን ሰምታለችና፡ እግዚአብሔር ሔዋንን እንዲህ ብሏታል፡ በሕይወቷ ዘመን ሁሉ ባልዋ ገዢ እንደሚሆንባት ተናሯታል። መጽሐፍ ቅዱስ ልክ እንደ መጀመርያው፡ ሴት "ታዛዥ" ትሁን እያለ፡ እንዴት ሴት መጥታ በወንድ ላይ ትገዛለች፡ እንዴትስ ፓስተር ወይም ዲያቆን ትሆናለች? መቼም ጌታ... እግዚአብሄር—እግዚአብሄር አይለዋወጥም። ቃሉ **እዚህ ጋር** አንድ ነገር ተናግሮ **እዚያ ጋር** ሌላ ነገር እንዲናገር ማድረግ አይቻላችሁም። አያደርገውም። ሁልጊዜም ያው ነው።

151 ስለዚህ፡ በመጀመሪያ፡ እንዲህ ነበር፡ ምናልባት ይህ ከማለቁ በፊት፡ ዕድል ካገኘሁ፣ **ጋብቻ እና ፍቺ** በሚመለከት ያለውን ጉዳይ ላስተካክልላችሁ እፈልጋለሁ። በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ እስካሁን ሰብኬው አላውቅም። ስለ ድርብ ጋብቻ ግን ጠብቁኝ። አንዱ ማግባት ትችላለች፡ ሌላ ማግባት አትችልም ይላል፡ ይሄኛውም **ይህን፡ ያን፡** ወይም **ሌላ** ይላል። ብቻ ትንሽ ጠብቁኝና፡ ስንደርስበት መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል እንመረምራለን። እሺ? በጣም ጥሩ። አሁን እንቀጥል።

**ሴቶቻችሁ በማኅበር:...** ዝም **ይበሉ: እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና: ሕግ ደግሞ እንደሚል: በመታዘዝ ሰር እንዲሆኑ ታዘዋልና።**

152 እዚህ ጋር: ጳውሎስ: እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም ነበር እንደሚል: የብሉይ ኪዳን ህግ ይህ ነበር። ልክ ነው? "ሴቶቻችሁ ዝም ይበሉ። መታዘዝ ነው።" ስለዚህ የዚህን ማጣቀሻ ምንባብ ከፈለጋችሁ: ወደ ዘፍጥረት 3:16 ይወስዳችኋል። እሺ? በጣም ጥሩ። "በሕጉ መሰረት: እንደ ሕጉ።"

**ለሴት... በማኅበር መካከል: መናገር... ነውር ነውና—ምንም** ሊማሩ... **ቢወዱ: በቤተክርትያን መናገር** ለሴት **ነውር** ስለሆነ **ቤታቸው ውስጥ ባሎቻቸውን ይጠይቁ።**

**ምን ነው?...**

153 አሁን ሁላችሁ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ: "ምን ነው? " የምትለዋን ጥያቄ ምልክት ተመልከቷት፤ ጳውሎስ ይህን እንዲናገርና በዚያ መልኩ እንዲያደርግ ያደረገው ምንድን ነው? የቆሮንቶስ ሰዎች: ለጳውሎስ የጻፏቸውን ደብዳቤዎች ብታነቧቸው። የቆሮንቶስ ሰዎች: ለጳውሎስ የጻፉትን: በጥሩ ቤተ መዛግብት ውስጥ ልታገኙ ትችላላችሁ። በዚያ ዘመን ከነበረው እምነት ስለተመለሱ: ሴቶች ይነግሩታል... ያኔ በዚያ ዘመን: "ዲያና:" የሚሏት ሴታዊት—አምላክ ነበረቻቸው። የኤፌሶንም አምላክ: እሷ ነበረች። የቆሮንቶስ ሰዎችም አረማውያን ስለነበሩ: ያመልኳት ነበር። አንድ ቀን የሴት ቅርጽ የሚመስል ድንጋይ: ሜዳ ላይ ወድቆ አገኙትና። "አምላክ ሴት ናትና እነሆ ምስሏን ወደኛ ጥላልናለች:" ብለው ወሰዱት። የታሪክ ምሁራን: ቤተ መቅደሳቸው ከሰሎሞን ቤተ መቅደስ ይልቅ: እጅግ የሚበልጥ ነበር ይላሉ። ኦህ: የሰሎሞን ቤተ መቅደስ: በወርቅ የተለበጠ: የሊባኖስ ዝግባ ሲሆን: የሷ ግን: በወርቅ የተለበጠ እብነበረድ ነበር ይላሉ። አያችሁ? ስለዚህ እጅግ ይበልጠዋል። ስለዚህ: አምላክ: ሴት—እስከ ሆነች ድረሰም: የሴት: ካህናት: ሊኖሯት ግድ ነው። አዎን: አምላክ ሴት ከሆነ: የሴት ሰባኪዎችም ትክክል ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን: አምላክ ወንድ ነው ስለሚለን: ወንድ ነው። አምላክ: ወንድ ነው። አያችሁ? አምላክ ወንድ ከሆነም: ወንድ ለመሆን ይገደዳል።

አሁን "ምን ነው? " የሚለውን ቃል አስተውሉት:

154 ያኔ ካህናት የነበሩ: አንዳንድ ሴቶች: ከአረማዊነት ወደ ክርስትና በመጡ ጊዜ: አሁንም ሰባኪ ሆነን አገልግሎታችንን ማስቀጠል እንችላለን ብለው ስላሰቡ: ገብተውም ቀጠሉበት። እዚያ ስለ ዲያና ከሰበኩ: እዚህ መጥተው ስለ ክርስቶስ ይሰብካሉ።

155 "ምን ነው? የእግዚአብሔር ቃል የወጣ ከእናንተ ነውን... " አላቸው። ይሄን ሰሙኻ። ወንድሜ: አገልጋይ እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ያደርጋል? ቁጥር 36።

**ምን ነው? የእግዚአብሔር ቃል የወጣ ከእናንተ ነውን? ወይሰ ወደ እናንተ ብቻ ደርሶአልን?**

**ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ:** የሆነ **ቢመስለው** (መንፈሳዊ-ሰው ብቻ ይሁን: የግድ ነብዪ መሆን አይጠበቅበትም): **ይህች**

**እኔ የጻፍሁላችሁ ትእዛዝ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ።**
(እናንተስ ታምናላችሁ? )

ማንም **ግን፡ የማያውቅ** ቢኖር **ግን፡ አይወቅ።**

156 እንደኔ፡ እንዲሁ በጥሬው መቅረብ ያለበት ነገር ነው። አያችሁ? ጳውሎስ ያለው፡ "ማንም ነቢይ፡ ወይም መንፈሳዊ ቢሆን፡ እኔ የጻፍሁላችሁ ትእዛዝ የጌታ ትእዛዝ እንደሆነች ያውቃል።" "ማወቅ የማይፈልግ—ከሆነ ግን፡ አይወቅ፡" እያለ ነው። አያችሁ? ማድረግ የሚቻላችሁ ብቸኛው ነገር ይህ ነው። መቀበል ካልፈለጉ፡ ተውአቸው ይሂዱ፡ እንዲህ እንድሚሆን አስቀድሞ አውቆታል።

157 አንዳንድ ሴቶች፡ ሲያነጋገሩኝ፡ "ኧይ፡ ጳውሎስ'ኮ የሴት-ጥላቻ ነበረበት፡" ይሉኛል።

158 በጭራሽ የሴት-ጥላቻ አልነበረውም። እንደምታውቁት፡ ጳውሎስ ሐዋርያ ነው፡ የአሕዛብ ቤተ ክርስትያን ሐዋርያ ነው። ተከታተሉኝ። ታውቃላችሁ ጳውሎስ... ሰብከቱ ይህ እንደ ነበረ ታምናላችሁ? ጳውሎስ የተናገረው—እንዲህ ነው አይደል? ጳውሎስ ሲናገር...

159 ምናልባት እናንተ አሁን፡ "ኧረ፡ ቆይ እስኪ፡ ወንድም ብራንሃም። አንዴ ቆይ! ቢሾፓችን'ኮ፡ ምንም ችግር የለውም ብሎናል። ሊቀ ካህኑ፡ ሲኖዶሱ፡ ችግር የለውም ብለውናል። የዋንነስ ቢሾፕም ችግር የለውም ብሏል፡" ትላላችሁ።

160 ማንም ምንም ይበል ግድ የለኝም። ውሸት ነው! ከረር እንደምናደርገው አስቀድሜ ነግሬአችኋለሁ። ሐሰተኞች ነብያት ሁሉ እንዲህ ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን፡ "ማንም ነብዪ፡ ወይም መንፈሳዊ ሰው የሆነ ቢመሰለው፡ እኔ የነገርኳችሁ ትእዛዝ የጌታ ትእዛዝ እንደሆነ ይወቅ ብሏል።" የነብዪው መንፈስ ከቃሉ ጋር ካልተሰማማ፡ ከመነሻው ጀምሮ፡ ሐሰተኛ ነው። የእግዚአብሔርን-ህግጋት ለመቃረን እና በእግዚአብሔር-ቤተክርስቲያን ክፋት ለማኖር፡ አሸንክታብ ለማራመድ፡ የሴት ወዳጅ ከመሆን፡ የሴት ጥላቻ ቢኖርብኝ እመርጣለሁ። ገላትያ 1:8ን ክፈቱ... ጳውሎስ እንዲህ ይላል። ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ "እኔ ከሰበክሁላችሁ ወንጌል በቀር የሰማይ መልአክ ቢሆን ሌላ ወንጌል ቢሰብክ፡ የተረገመ ይሁን" ብሏል። ይሄ ታድያ ምን ልትሉት ነው?

161 እናንተ ግን፡ "ጴጥሮስ በበአለ ሐምሳ ቀን፡ ኢዩኤልን ጠቅሶ፡ 'ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢትን ይናገራሉ፡' በማለት—የተናገረውስ ምን ትለዋለህ ትሉኛላችሁ? " አዎን ትክክለኛ ነገር ነው።

162 ታውቃላችሁ፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን፡ እና በአሁን ዘመን፡ ለአብራህም እንደተሰጠው የተሰፋ ቃል፡ ማንም ሰው፡ ወደ ቃልኪዳኑ የሚገባበት ብቸኛው መንገድ፡ መገረዝ ነበር... የተሰፋው ቃል ማሕተም—መገረዙ ላይ ነበር። ሰንቶች ታውቃላችሁ? የእግዚአብሄር ማረጋገጫ መገረዝ ነበርና።

163 አንድ ባፕቲሰት ወንድም፡ "ወንድም ብራንሃም፡ እኛ ባፕቲሰቶች'ኮ፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል፡" አለኝ።

"መቼ ነው የተቀበላችሁት፡" ብዬ ጠየቅኩት?

"ባመንን ጊዜ፡" ብሎ መለሰልኝ።

164 "ጳውሎስ ግን፡ 'ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስ ተቀበላችሁን? ነው ያለው'" ብዬ ነገርኩት፤ አያችሁ? "እናንተ፡ ባፕቲሰቶች እነኚህ ነገሮች ይዛችሁ

ኑ፡ ስለ ዘለአለማዊው ዋስትናም እንነጋገራለን፡" አልኩት። ኢያችሁ? "ለመሆኑ፡ እንዲህ ያለ ነገር፡ ከየት አመጣችሁት? " አልኩት፤

165 ጳውሎስ ያለው "ካመናችሁ **ወዲህ** ተቀበላችሁን? " ነው፤ እልልታና ደስታ፡ ሌላውንም ሁሉ የተለማመዱ አማኞች። መንፈስ ቅዱስን ግን ገና አልተቀበሉም ነበር። ጳውሎስ እራሱ አለመቀበላቸው መሰክሯል። አይደል? "ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስ ተቀበላችሁን? "

እነርሱም፡ "አልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ስንኳ አልሰማንም አሉት።"

"እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? " አላቸው፡

166 በርግጥ "ተጠምቀናል፡" አሉት። ጥምቀታቸው ግን፡ ጉድለት፡ ነበረበት። ስለዚህ፡ ዳግም ሊያጠምቃቸው ተገባው። እሺ እንቀጥል።

167 አሁን፡ እነዚያ ሴት ሰባኪዎች፡ ወዲህ በመጡ ጊዜ፡ አስቀድሞ የነበራቸው ስልጣን ይዘው የሚቀጥሉ መሰላቸው። እንዲህ ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም የተከለከለ ነገር ነው። ከዚህ ርዕሰ ሳንወጣ፡ ስለ ሴቶቹ... እያችሁ፡ ሁሉም ሊያውቀው የሚገባ። አስቀድሞ፡ እሱም፡ እንደተናገረው፡ "ከእናንተ ማንም ነቢይ፡ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለው፡ ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ። ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን አይወቅ።" በዚህም ምክንያት... በቤተ ክርስትያናችን ሴት ሰባኪዎች፡ እና ሴት ዲያቆናት፣ ወይም በቤተ ክርስትያን ባሉ መሪ አገልግሎቶች ውስጥ ሴት አንሾምበትም፡ ቅዱስ ቃል በፊታችን የተከደነ አይደለምና።

168 አሁን መጽሐፍ ቅዱስ "ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፡" ይላል። እሺ፡ **ትንቢት** የሚል ቃል ትርጉሙ ምን ማለት ነው? ተከታተሉ። ትንቢት ማለት "አንድን ነገር፡ በመንፈስ ሆኖ መናገር፡" ወይም "ወደፊት የሚሆነውን ነገር መንገር" ማለት ነው። ድርብ ትርጉም አለው።

169 ልክ **መቀደስ** ማለት "መንጻት፣ እና ለአገልግሎት መለየት ማለት እንደሆነ ሁሉ።" እያችሁ? ድርብ ትርጉም ያለው፡ ማለት፡ ከአንድ በላይ ትርጓሜ ያለው፡ ኢንግሊዘኛ ላይ እጅግ ብዙ ምሳሌዎች አሉን።

170 ለምሳሌ፡ "ቦርድ፡" እንላለን። እሺ **ቦርድ** ሲል ምን ለማለቱ ነው እንላለን? "**የጉዞን** ክፍያ ከፈለ፡" ማለቱ ነው ትላላችሁ። "አይ፡ አይደለም። **ቦረቦረ** ማለቱ ነው።" "ኧረ፡ አይደለም። **ደበረኝ** ማለቱ ነው።" እያችሁ፡ እንዲህ ከሆነ፡ በአንዲት ቃል፡ የምትናገሩት ነገር ማስተዋል አለባችሁ። እያችሁ?

171 አሁንም፡ "ወንዶች እና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢትን ይናገራሉ፡" የሚለው ቃልም ባለ ድርብ ትርጉም ነው። እግዚአብሄር እንደተቀበለን፡ ብቸኛው ማረጋገጫ...

172 ባፕቲስቱ "ያኔ፡ መንፈስ ቅዱስ ተቀብለናል፡" አለ። መቼ ስለው... "ባመንን ጊዜ።" እኔም... አሁን፡ እዩት፡- "አብርሃም እግዚአብሄርን አመነ።" አለ፡ "እግዚአብሄርም ለአብርሃም... " አለኝ። ያስቀመጠው በዚህ መንገድ ነው። እንዲህ በማለት፡- "አብራሃም እግዚአብሄርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት አለ።" እውነት እንደሆነ ስንቶች ታምናላችሁ? እንግዲያውስ

አሁን—ሰይጣን አንድን ሰው እንዴት በቀላሉ ሊያስተው እንደሚችል እዩ። አያችሁ፡ ቃል ነው። ይሁን እንጂ፡ በቀላሉ ያስታል።

173 ወንድሜ፡ ወደዚህ ከመምጣትህ በፊት፡ ወደ መድረክ ከመውጣትህ በፊት፡ መቀባት እንዳለብህ እመክርሃለሁ። ምሽግ ገብተህ በሰውር ጸልይ። ሰዎች “ወጥተህ ህዝቡን ለምን አታገለግልም?” ሊሉህ ይችላሉ፤ ወንድሜ ሆይ፡ ሰዎቹን ልታነጋግራቸው ወይም ልታስተምራቸው ከፈለግክ፡ ወደ መድረክ ከመውጣትህ በፊት፡ ለተወሰነ ጊዜ፡ ብቻህን፡ ከጌታ ጋር ብትቆይ ይሻልሃል። አየህ፡ የግድ ነው፡ ‘ምክንያቱም ሰይጣን እጅግ አታላይ፣ በጣም አታላይ ነው።

174 ሲናገርም፡ አስተውሉ፡ “አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፡” አለ። ትክክል ነው። አክሎም “እንደው፡ አብራሃም ከማመን በቀር ሌላ ምን ማድረግ ይችላል?” አለ፤

እኔም “አዎን ማመን ብቻ ነው ያለበት፡” አልኩት።

175 አለኝም፡- “አንተ ብትሆን ሌላ ሰው ከማመን በቀር ምን ማድረግ ይችላል?”

176 አዎን፡ “ማመን ብቻ ነው ያሌብን። ይሁን እንጂ ወንድሜ፡ ከዚያ በኋላ እግዚአብሄር የአብርሃምን እምነት ማረጋገጫ መሰጠቱን ወይም ማክበሩን፡ ይሄን አትርሳ። የቃል ኪዳኑም ማኅተም፡ የመገረዝ ምልክት የሆነውን፡ ማኅተም ሰጥቶታል። አየህ? ማኅተም ሰጥቶታል። እንዲህ አለው፡- ‘አብራሃም ሆይ፡ አንተን፡ እንደተቀበልኩህ የሚያሰረዳ ምልክት፡ አሁን እሰጥሃለሁ እምነትህም፡ በዚህ አረጋግጣለሁ።’”

177 አለውና፡ አብራሃምን ገረዘው ይህም የቃልኪዳኑ ማኅተም ነበር። አሁን በዚህ ዘመን... አሁን፡ ያገባች ካልሆነች በቀር፡ ሴት በዛ ቃል ኪዳን ውስጥ አትገረዝም። ምክንያቱ፡ ሴትን መግረዝ አይቻልም፡ በዚህም ምክንያት ባልዋ እና እሷ አንድ በመሆን፡ ወደ ውስጥ መግባት አለባቸው። ከእንግዲህ አንድ ናቸው እንጂ፡ ሁለት አይደሉም። ቅዱስ ቃልም ይደግፈዋል። ሰንቶች ታምናላችሁ? ስለዚህ፡ በማግባቷ፡ አንድ—ትሆናለች። ጢሞቴዎስ ላይ ሄዳችሁ አንብቡት፡ አንድ አይነት በመናገር፡ ያጸናዋል፡- “በእምነትና በቅድስና በፍጹም መታዘዝ፡ ከጸናች በመውለዷ ትድናለች ይላታል።”

178 የብሉይ ኪዳን መገረዝ፡ በሥጋ ነበር፡ በአዲስ ኪዳን ግን፡ በኢዩኤል፡ እንደተነገረ፡ “በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፡” ብሎናል። **ትንቢት** መናገር ማለት፡ ማስተማር አይደለም። **ትንቢት** ማለት “ግንዛቤን፡ በተመሰጦ መናገር፡” ወይ ደግሞ “ሊሆን ያለውን ነገር ከመሆኑ በፊት መናገር ነው።” በብሉይ ኪዳን የሴት ነቢያቶች እንደነበሩ እናውቃለን። በሕንፃው ውስጥ ግን፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በጉባኤ፣ እንደ አስተማሪ መናገር ፈጽሞ አይፈቀድላቸውም። እነ ሀና፡ እና በቤተ መቅደሱ ዙርያ የነበሩ ብዙዎች፡ ነብያት ነበሩ፡ ትንቢትም ይናገሩ ነበር... ሚርያምም ነብዪት፡ ወይም እንዲሁ ነበረች። መንፈስም በላይዋ ነበር፣ እውነት ነው፡ ነገር ግን የቦታ ውስንነቶች ነበራት። ዛሬም ሴቶች ነብያት መሆን ይችላሉ፡ አዎን፡ መድረክ ላይ ወጥተው አስተማሪ፡ ወይም እንዲህ እና እንዲያ መሆን ግን አይችሉም። ብትሆኑ ግን፡ መጽሐፍ—በራሱ እንዲጋጭ ታደርጉታላችሁ። መጽሀፍ **እዚህጋ** አንድ ነገር ተናግሮ፡ **እዚያጋ** ሌላ ነገር አያደርግም። ሁልጊዜ

ተመሳሳይ ነገር መናገር አለበት ወይም የእግዚአብሔር ቃል አይደለም። አይደል? ስለዚህ፡ “ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ።” ማለት “መተንበይ” ወይም “መመስከር፡” ይችላሉ ማለት ነው። ይሄን ከመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡ ፈትሻችሁ፡ ስህተት ከሆነ መርምሩ። “ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ።”

179 እና፡ መጽሐፍ ቅዱስም እራሷን ሌላ ለማስመሰል ስለምትሞክር፡ ወይም ነኝ ስለምትል ሴት፡ ይናገራል... ይህ ሁሉ የካቶሊክ ቤተክርስትያን ላይ፡ እና አሁን ልንናገረው ያለውን ርዕሰ... ላይም የሚሰራ ነገር ነው። የራዕይ መጽሐፍ—ገልጠን፡ ከ2ኛው ምዕራፍ—ቁጥር 20 ላይ እናነባለን፡ በዚህ በመጨረሻው ቀን ይሆናል ብለን የምንናገርለት ይህ ነገር፡ ምን ያህል ሰይጣናዊ ሊሆን እንደሚችል አስተውላችሁ፡ ማየት እንድትችሉ ለማድረግ ስንቃረብ፡ ይህች ሴት ምን እንደምትሆን... እንዴት እንደ ሆነ እንድታዩት ነው። ሴቲቱ የካቶሊክ ቤተ እምነት እንደሆነች፡ አስታውሱ። አንብበናል፡ አይደል? እንግዲያውስ፡ ምን እንደሚናገር አድምጡ። ራዕይ 2፡20፣ “ዳሩ ግን... ” እያችሁ፡ ስለ ትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን እየተናገረ ነው፡ “ዳሩ ግን... ” በጨለማው ዘመን ያለፈች፡ የቤተ ክርስትያን ዘመን-አጋማሽ ናት።

> ዳሩ ግን **ነቢይ ነኝ የምትለውን፡ ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና፡ ለጣዖት** የታረደውን **እንዲበሉ**፡የምታስተምረውንና... **የምታሰተውን** ያችን **ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ** ነገር **አለኝ**። (አያችሁ? )

180 አሁን፡ የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ አስተውላችሁ ተመልከቷቸው፡ ከዚያ እንዘጋለን። ከዚያም ነገ ጠዋት ላይ ሌሎች ነገሮች እናነሳለን። ተከታተሉ። በአይሁድ ቤተ መቅደሰ... ውስጠኛው ክፍል—ህብስተ መና፡ እና፡ የወርቅ መቅረዝ ባለበት፡ ሰባት የቀርቅ መቅረዞች ነበሩ። ይሄን ሁላችሁ ታውቁታላችሁ። አይደል? ይህም ስለ ሰባቱ አብያተ ክርስትያን ዘመናት የሚናገር፡ ብርሃን ነው። ስለዚህ ሰባት የቤተክርትያን ዘመን አለ። እንግዲህ በራዕይ 1 ላይ ካያችሁ፡ ለማየትም ዞር ባለ ጊዜ፡ ኢየሱስን በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል፡ ሲመላለስ፡ የሰው ልጅ የሚመሰለውን፡ ምሳሌዎችን ለብሶ፡ በሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት መካከል ሲመላለስ አየው። በመቅረዙ መካከል ቆማ የምትታየው ምሳሌ፡ ሙሽራይቱ ናት።

181 በብሉይ ኪዳን፡ መጀመርያ፡ አንደኛዋን መቅረዝ... ከለኰሱ በኋላ፡ መንደድ ሰትጀምር፡ ሁለተኛውን መቅረዝ፡ መጀመርያ ከተለኰሰች እሳት ወሰደው ያበሩታል፡ ሌሎቹም፡ ሰባቱ መቅረዞች፡ ፈጽመው እስኪያበሩ ድረስ በዚህ መልኩ ይለኲሷቸው ነበር።

182 ካስተዋላችሁ፡ እግዚአብሄር በአይሁድ ዘንድ ሰራውን በጀመረ ጊዜ፡ አይሁድ ወርቃማ ዘመን አሳልፈው ነበር። ከዚያ በኋላ ግን፡ እግዚአብሄር፡ ከአይሁድ ጋር የነበረው የጨለማ ዘመን በአክዓብ ዘመን፡ነው። የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ስታነቡ፡ ካስተዋላችሁ፡ ታሪኩን ዳግም እየተረከ መሆኑ ታያላችሁ። እርሱም፡ አሁን፡ “ከጥቂት ጊዜ በፊት፡” እንደተናገረ... አንድ ሺ አምስት መቶ ዓመታት በሚሸፍነው፡ በጨለማው ዘመን ላይ፡ ወይም፡ አይሁድ፡ በመጀመርያ፡ የአክዓብ ዘመን ላይ። አክዓብ ኤልዛቤልን አግብቶ ጣኦት ወደ እስራኤል ያስተዋወቀበት፡ ህዝብ ሁሉ አክዓብን ተከትሎ፡ ... የኤልዛቤልን

አማልክት እንዲያመልክ ያደረገበት ዘመን ለእስራኤል እጅግ ጨለማ ነው። የእግዚአብሔርን መሠዊያዎች አፍርሰው፡የማምለኪያ ዐፀዶቹን ሲያቆሙ፡ ታስታውሳላችሁ። “ብቸኛው፡” ኤልያስ ግን ድምጹ አሰማ፡ እግዚአብሄርም ለበዓል ያልሰገዱ ሰባት ሺ ህዝብ ነበሩት። ይሄን ታስታውሳላችሁ? እነዚህ ማለት ተመርጣ የምትወጣው ቤተ ክርስትያን ምሳሌ ናቸው። አያችሁት? ገባችሁ አይደል?

183 እንግዲህ፡ በዚህች ቤተ ክርስቲያን፡የመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን ካያችኋት፡ የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን፡ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን፣ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። “አሁንም ብርሃንሽ አለ፡” ብሏታል። ከዚያ በኋላ ስታዩአቸው ግን፡ እያንዳንዱ ቤተ ክርስትያን፡ ትያጥሮን እስክትመጣ ድረስ እየደበዘዙ፣ እየደበዘዙ፣ እየደበዘዙ፣ ሄዱ። ከዚያ በኋላ፡ ሺ አምስት መቶ አመታት አሉ። ቀጥሎ በሌላ በኩል ወጣ፡ “ትንሽ ብርሃን ቀርቶሃል። መቅረዝህ እንዳይወሰድብህ፡ የቀረህን አጽናው።” እንዲህ እያለ ወደ ፊላደልፊያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ ከዚያም ወደ ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ይመጣል።

184 እጅግ ደስ የሚለኝ ነገር፡ ይህ ነው። ኦህ፡ ማይ! ወንድም ሰሚዝ፡ ይሄን እይልኝ። በጣም የሚመቸኝ ነገር፡ ይህ ነው። አሁን እንቀጥል፡ **በዚህ** ቤተክርስትያን ዘመን፡ አሁን... ተከታተሉኝ። የመጀመርያ የቤተ ክርስትያን ዘመን ኤፌሶን ናት፡ የኤፌሶን የቤተክርስትያን ዘመን። ስለዚህ፡ እያንዳንዳቸው የቤተ ክርስትያን ዘመናት... ምናልባት ጊዜ ካገኛችሁ፡ ዛሬ ማታ፡ ወይም ነገ ጠዋት፡ ወደ ቸርች ከመምጣታችሁ በፊት፡ በራሳችሁ ጊዜ አንብቡት፡ በራዕይ ዮሃንስ 1ኛ፣ 2ኛ፣ እና 3ኛ፣ ምዕራፎች ላይ ታገኙታላችሁ። እስከ ጨለማው ዘመን፡ ለእያንዳንዷን ቤተ ክርስትያን ዘመን፡ ሲናገራቸው፡- “ታግሰህማል፡ ስሜንም አልካድክም፡” እያላቸው፡ እስከ ትያጥሮን ድረስ ለሺ አምስት መቶ አመታት ይህን ቃል ይናገራቸዋል። ከዚያ በኋላ፡ ወጥቶ ይሄኛውን ይናገረዋል፤

... ሕያው እንደ መሆንህ **ስም አለህ**፡ ነገር ግን **ሞተሃል**።

185 ሌሎቹ ግን፡ ሌሎቹ የቤተ ክርስትያን ዘመናት፡ ወይም ፊላደልፊያ ዘመን፡ ይሄኛውን ስም ፈጽመው አልተጠሩበትም። ሰያሜው በዚህ ዘመን ሰላበቃለት፡ ሌሎቹ አልተጠሩበትም። ኦህ፡ አሁን፡ የሐሰት ትምህርቶች ሁሉ ወደዚህ በማምጣት፡ እዚያው ውስጥ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን፡ እናታቸው እንደሆነች፡ የሁሉም እናት፡ “የምስጢረ ባቢሎን፡ እናት፡” እንደሆነች ልናሳያችሁ እንችላለን። አሁን፡ የምታዩአት ይህች ቤተክርስትያን፡ ስትወጣ፡ ትንሽ ብርሃን ነበራት፡ በኋላ ግን እየደበዘዘች፡ እየደበዘዘች፡ በሺህ አምስት መቶ አመታት ውስጥ፡ ድርጅት ሆና ቀረች። ስትወጣ ግን፡ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስትያን ሆና ሳይሆን፡ ካቶሊክ ቤተ እምነት ሆና ወጣች። የሉተር ማን ተብላ ወጣች? ሉተራን ቤተ እምነት። የባፕቲስቶችስ ማን ተባለች? ባፕቲስት ቤተ እምነት። “ሰም አለህ፡” ብሎታል፡ ሰያሜው ግን፡ በሌላ ሰያሜ እንጂ በሰሙ አልተጠራም። “ከኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም በቀር፡ ትድኑበት ዘንድ ከሰማይ በታች የተሰጠ ሌላ ሰም የለምና።” “ሕያው እንደ መሆንህ ሰም አለህ፡ ነገር ግን ሞተሃል፡” የሐይማኖት ተቋሙን ነው።

186 “ኦህ፡ እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ፡” በቃ ሞተሃል! “ኦህ፡ እኔ ባፕቲስት ነኝ፣” ሞተሃል! በክርስቶስ ኢየሱስ ሕያዋን ስትሆኑ ብቻ በሕይወት ትኖራላችሁ። በትክክል። ውኃን፡ በመርጨት፡ እና በማፍሰስ፡ የሚደረግ፡ የውሸት

ጥምቀቶቻችሁ፡ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይልቅ፡ "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣" ብላችሁ የምታደርጉት የሐሰት ጥምቀት ሁሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ እነዚያ ሁሉ ሐሰተኛ ነገሮች፡ የሚቻለውን ያህል ወደዚህ እያፈሰሰ ነው። መጽሐፉ **እንዲህ** ይላል። "እንዲ፡ በኛ ቤተ ክርስትያን የምናምነው **እንዲህ** ነው ይለናል፡" በዚህ ሁሉ ግን ችለናቸዋል። እያችሁ? እንዲህ ብሎ ነገር የለም። እንደዚህ ጭራሽ የለም።

187 ምላሳቸውን እያወጡ ቅዱስ ቁርባንን ይውሰዱ ካህኑም ወይኑን ጠጥቶ መንፈስ ቅዱስ ይጥራ፡ የሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ቦታ የለም። የቀኝ እጅ ሕብረትን መንፈስ ቅዱስ ነው ብለው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጅ ለእጅ የተጨባበጠ የለም። ማንም ተነስቶ፡ "አሁን አማኝ ሆንኩኝ፡" መንፈስ ቅዱስን ተቀበልኩ ያለ ሰው የለም። እንዲህ ቢሆን'ማ ኖሮ፡ ሐዋርያት ስራ 2 ሲነበብ እንደሚከተለው ይሆን ነበር፡- "በዓለ ኃምሳ የተባለ ቀን በደረሰ ጊዜ፡ አንገትጌ ያሰረ፡ አንድ ሮማዊ ቄስ ከመንገድ ወርዶ መጣ። ተብሎ ይነበብ ነበር። ወደ ላይ ወጥቶም፡ 'የጌታን እራት ለመውሰድ፡ ሁላችሁም ምላሶቻችሁን አውጡና ቅዱስ ቁርባንን ተቀበሉ አላቸው ይባል ነበር።'" የሐዋርያት ሥራ 2 የሚነበብበት መንገድ ይህ አይሆንም ነበርን?

188 እናንተ፡ ፕሮቴስታንቶችም ከዚህ እጅግ የከፋችሁ ናችሁ። ይመጡና እንዲህ ይላሉ፡- "አሁን ሜቶዲስቶች ወደ እናንተ እንመጣለን፡ በቀኝ እጅ እንጨባበጣለን፡ ወይም፡ የኅብረት ቀኛችን እንሰጣቸዋለን፡ ስድስት ወር ሙሉ የሙከራ ጊዜ ነው።" ከሐዋርያት ሥራ 2 ላይ የት አነበባችሁት? ንገሩን? ከየት አመጣችሁት? እያችሁ?

189 ቃሉ የሚለው፡ "ሁሉም በአንድ ቦታ፡ በአንድ ልብ ሆነው ሳሉ!" ኤጲስ ቆጶስ መጥቶ **ያደረገላቸው** ነገር የለም፣ ወይም ቄስ ወጥቶ እንዳች ነገር **አላደረገም**። "ነገር ግን እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፡ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው።" አዎን፡ ወዳጄ፡ ሆይ፡ ከክብር እንደሚወርድ እንደ ታላቅ አውሎ ነፋስ ነው የተቀበሉት። በመንገድ ላይ ወይም ከሐይማኖት ተቋም አልተሰጣቸውም።

... ሕያው እንደመሆንህ **ስም አለህ**፡ ነገር ግን **ሞተሃል።**

190 እያችሁ፡ አዋልዶቻችሁ እና የሐይማኖት ተቋሞቻችሁ እንደ ሐሰተኛ ነቢይ ትምህርት ናቸው፡ "የተአምራትም ዘመን አልፏል፡ እኛ የምናምነው **እንዲህ** ነው።" በማለት፡ እግዚአብሄርን አርቃችሁታል። "እጅ በመጨባበጥ መንፈስ ቅዱስ ትሞላላችሁ፡" የሚላችሁ፡ ሐሰተኛ ነብይ ነው። "ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ትቀበላላችሁ፡" የሚላችሁ ሐሰተኛ ነቢይ ነው። "በጥልቅ ውኃ ከመጥለቅ ይልቅ በመርጨትና ውኃን በማፈስስ ተጠመቁ፡" የሚላችሁ ሐሰተኛ ነቢይ ነው። ይሄን የሚደግፍ ቅዱስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሳይኖር "በአባት፣ እና በልጅ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቁ" ብሎ የሚያስተምራችሁ ውሸታም ነቢይ ነው። በትክክል። ከዮሃንስ ደቀ መዝሙር በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ በሌላ የተጠመቁ የሉም፡ የተጠመቁ ሰዎች ሁሉ፡ ጥምቀታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ ነው። እነርሱም፡ መንፈስ ቅዱስ ለመቀበል፡ እንደገና መጠመቅ ስለነበረባቸው፡ መጥተው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ተጠምቀዋል። አዎን በትክክል። ይሄ፡ የኦንሊ ጂሰስ ዶክትሪን

አይደለም። የኦንሊ ጂሰስ ዶክትሪን አውቀዋለሁና። የነሱ አይደለም። ይሄ የመጽሐፍ ቅዱስ ዶክትሪን ነው። አዎን በትክክል።

191 ቃሉ ቀርቦላችኋል። ምን ታደርጉታላችሁ? እናታቸውም ይህች ናት። የአዋልድ ሁሉ እናት ይህች ናት።

192 እስኪ፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ ብላችሁ ውኃን በመረጨት የተጠመቀ አንድ ሰው አሳዩኝ። እናንተ ሜተዲስቶች፣ ፕረስቢተርያኖች፣ ካቶሊኮች ሆይ፣ ውኃን በመርጨት የተጠመቀ አንድ ሰው፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳዩኝ። ወይም ስለ ሐጥያት ስርየት፡ ውኃ የፈሰሰበት ሰው፡ ከመጽሀፍ ቅዱስ አሳዩኝ። ጥቀሱልኝ። መጥቀስ ትችላላችሁ? ከቻላችሁ፡ ኑና ጥቀሱልኝ፡ ጀርባዬ ላይ "ሐሰተኛ ነብይ ነኝ! ተሳስቼ ነበር፡" የሚል ጽሑፍ አንጠልጥዬ፡ በየጎዳናው እዞራለሁ። ወይም፡ ከእናንተ መካከል ስማንያ በመቶ ያህል ህዝብ በአባት፣ በልጅ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደተጠመቃችሁ፡ ከመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ እናንተ የተጠመቀ አንድ ሰው አሳዩኝ። በዚህ መልኩ የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ ከቅዱስ ቃል ጥቀሱልኝ፡ ጀርባዬ ላይ፡ "ሐሰተኛ ነብይ ነኝ፡" የሚል ጽሑፍ አዝዬ በየጎዳናው **እንዲህ** እዞራለሁ። እና በአዲሲቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ በኢየሱስ ስም ብቻ ሳይሆን፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ መጥቶ... "መጠመቅ" የሌለበት ማንም የተጠመቀበትን፡ ቦታ አሳዩኝ። ትክክል ነው። ይህ ትክክል ካልሆነ መርምሩ።

193 ስለዚህ፡ ሴቲቱ፡ ምን ነበረች? የጋለሞታዎች እናት ናት። አመንዝራ ያደረጋት ነገር ምንድነው? ጋለሞታ እንድትሆን ያደረጋት ነገር ምንድነው? ትምህርቷ! እነርሱስ ጋለሞታ እንዲሆኑ ያስቻላቸው ምንድነው? ትምህርቷ!

194 የሐይማኖት ተቋማቸውን እና አዋልዶቻቸውን የማንታገስበት ምክንያት ይህ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ንጹሃን እንሁን። ምን ያህል እንደምትኖሩለት ባላውቅም፡ በደንብ፡ ተምራችሁታል። ጥሩ። ይህ እናንተን የሚመለከት ነው። እውነቱን ብቻ እነግራችኋለሁ እንጂ። እንድትኖሩት ላደርጋችሁ አልችልም። የሐይማኖት ተቋም ያልሆነው ለዚህ ነው። እንደዚህ ባሉ ዶግማዎች ውስጥ ገብተን—እራሳችንን ማበላሸት አንፈልግም፡ እንዲህ አይነት ነገር መግባት አልፈልግም። መንገዴን ሁሉ የጌታ ከሆኑት ጥቂት የተናቁ መንጎች ጋር ባደርግ ይሻለኛል። በእግዚአብሄር እና በቃሉ ፊት በንጽህና እና፡ በቅድስና ጸንቼ "በልብሴ ላይ የሰው ደም የለም፡" ማለት ይሻለኛል። ለዚህ ነው በብራንሃም ተበርናክል ያለነው። ለዚህ ነው አሰምብሊዎች ያልሆንነው። ለዚህ ነው ዋንነስ ያልሆንነው። ለዚህ ነው ኦንሊ ጂሰሶች ያልሆንነው። ለዚህ ነው ሜተዲስቶች ያልሆንነው። ባብቲስቶች ያልሆንነው ለዚህ ነው። በፍጹም የሐይማኖት ተቋም የለንም። ምስኪን—እና ታናሽ ጉባኤ ነን። በክርስቶስ፡ ነጻ ነን። ስለዚህም ነው በአካሄዳችን እንዲህ የጸናነው። እግዚአብሄርም እየረዳን፡ እና እየባረከን ነው።

195 ስለዚህም፡ የጌታ እራት የምንወስድበት ምክንያት ልንነግራችሁ እንችላለን፡ እግር-መታጠብ ለምን እንደምናደርገው እንነግራችኋለን፡ ሐጥያት እንዳለባቸው ካወቅናቸው አባላት እንዳይወስዱ ለምን እንደምንከለክላቸው ልንነግራችሁ እንችላለን። ለዚያም ነው፣ ባለፉት ሁለት ወይም ሶስት ሳምንታት፣ ከአንዱ አባል ወደ ሌላው እየዞርኩ፣ በመካከላችሁ ጥል እንዳይኖር በመፈተሽ ያሳለፍኩት፡ ለዚህ ነው። አንዱ መንገድ ላይ እያየው፡ ረግጦት ያልፋል፡ ሌላኛውም መንገድ ላይ ሲያየው ፊትን አዞሮ ይሔዳል። ታሳፍራላችሁ፡ የተባረከውን የጌታ ጽዋ፡

መድረክ ላይ ይዛችሁ፡ ወንድም እህት እየተባባላችሁ፡ ስልክ ላይ እርስ በእርስ ትተማማላችሁ። እንደዚህ ከሆናችሁ ክርስቲያን ለመባል ብቁ አይደላችሁም። እሺ። ስለ አንድ ሰው ጥሩ ማውራት ካልቻላችሁ፡ ስልኮችን ዝጉ፡ በጭራሽ አትናገሩ። እግዚአብሔር እንደሚጠይቃቹ፡ አትርሱ። እንደዚህ አይነት መንፈስ በውስጣችሁ እስካለ ድረስ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክል እንዳልሆናችሁ እወቁ። ካልሰማችሁ...

196 አንድ ሰው ከተሳሳተ፡ ቀርባችሁ ታረቁት። መታረቅ ካልቻላችሁ፡ አንድ ሰው ከእናንተ ጋር ይሂድ። ትክክል አለመሆናችሁ አይቶ ነው ለካ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን እየቀጣ ያለው። ስልክ ደውሎ የሆነውን ነገር ሁሉ ከማውራት፡ ምን ምን ተከሰተ፡ ስለ የአምልኮ ሥርዓቶች እና በዙሪያው ስላሉ ከማውራት ይልቅ። ይህን ከማድረግ ይልቅ፡ ለምን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን አታደርጉም? አንድ ወንድም ካጠፋ፣ ወደ እሱ በመሄድ ከእሱ ጋር ለመታረቅ እድል ካለ መርምሩ። “ኧረ፡ እንዲህ በድሎኝ፡ እንዲህ አርጎኝ!” ምን እንዳደረገህ ግድ የለኝም፡ ለማንኛውም ቅረበው! እሱ ወደ አንተ ይምጣ አይልም። እሱ ካጠፋ ወደ እሱ ሂድ። “እንዴ፡ ከፈለገ እሱ ይምጣ። ጥፋተኛው ራሱ ነው፡” አትበሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አይልም። መጽሐፍ ቅዱስ አንተ እንድትሄድ ተናግሯል። እሱ ከተሳሳተ፡ አንተ እራስህ ወደ እሱ ሂድ።

197 አንተን ካልሰማህ፡ ለምስክር እንዲሆን፡ ሌላ ሰው ይዘህ ሂድ።

198 ምስክሩን ባይቀበል ግን፡ “ከአሁን በኋላ ለፓስተር አሳልፌ እሰጥሃለሁ፡” በለው። ጨምራችሁም፡ እንዲህ ትሉታላችሁ፡ “ከዛሬ ቀን ጀምሮ እስከ ሰላሳ ቀናት ድረስ፡ ወንድሞች በራሳችሁ ከጨረሳችሁ፡ ወንድማችሁ በራሱ መታረቅ ቢፈልግ... አሳልፋችሁ አትሰጡት። ባይፈልግ ግን ለቤተ ክርስትያን አሳልፈን እንሰጥሃለን በሉት። በሰላሳ ቀናት ውስጥ አልታረቅም ቢል፡ ከዚያ በኋላ ምን ታደርጋላችሁ? ከእንግዲህ ከእኛ ጋር አይደለህም ትሉታላችሁ።”

199 መጽሐፍ ቅዱስም፡ “ቤተ ክርስቲያንን የማይሰማ ከሆነ ግን፡ እንደ አረማዊና ቀራጭ ይሁንላችሁ፡” ይላል። አያችሁ፡ ይህ ወንድም በቤተ ክርስቲያን ሥር እስካለ ድረሰ የክርስቶስ ደም ይጠብቀዋል። ቤተክርስቲያን ላይ በየመንገዱ የማንከባለልበት ምክንያት ይህ ነው። አሁን፡ ከተቀበላችሁት፡ **ይህ** የባ-... የባፕቲስት፡ ወይም የብራንሃም ቤተ ክርስቲያን፡ ትምህርት ነው። ለምን፡ እንደማይቻል...

200 ለምሳሌ፡ ወደዚህ እንምጣና፡ እኔን እና ሌዮን፡ ሁለታችንን፡ እንደምሳሌ እንውሰድ። እኔን... ቢበድለኝ፡ ማንም ይሁን ምን ልዩነት አይፈጥርም። “ይህ ሰው፡ እኔን—ጎድቶኛል፡” ማለቴ አይቀርም። ስለዚህ ወደሱ መሄድ አለብኝ። ይህ ሰው—ክርስትያን ነው። የቤተ ክርስትያን አባል ነው። አብሮኝ ቆሞ ቁርባንን ይወስዳል። ሁለታችንም በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀናል። እንደ ወንድማማቾች፡ አብረን፡ ተጉዘናል፡ ድንገት የሆነ ነገር ተፈጠረ።

201 ዘጠና በመቶው ሰይጣን በሰዎች መካከል ስለሚገባ ነው። እንጂ ሰውየው አይደለም። ሰዎቹ አይደሉም። ሰይጣን ነው። ዲያቢሎስ ስራውን እንዲሰራብህ እስከፈቀድክለት ድረስ ወንድምህን እየጎዳኸው ነው። ትክክል ነው።

202 እሺ፡ በእኔና በሊዮ መካከል ችግር ተፈጥሯል እንበል፡ እስኪ እንፍታው። እናንተም የሆነ ነገር እንዳለ ካያችሁ፣ ወደ እኛ መጥታችሁ፡- እናንተ “ሁለታችሁን

እንፈልጋችኋለን። ኑና ይሄ ነገር እንፍታው፡” የማለት ግዴታ አለባችሁ። እንግዲህ፣ ወደዚያ ከመጣ፣ ነገሩን ለመፍታት ከመጣን፣ እንግዲያውስ፣ መልካም ነው። እንደነገርኳችሁ፦ “መስማማት—ካልቻልን፡ ከሁሉ በፊት መደረግ ያለበት፡ ወደ ቤተ ክርሰትያን ማምጣት ነው።”

203 ባትስማሙ—እና መፍታታ ባትችሉ ግን፡ ምንም ቢሆን፡ የኢየሱስ ክርሰቶስ ደም ሁለታችንም ይጠብቀናል። አያችሁ? ይሁን እንጂ—አሮጌው ካንሰር ሌላ ካንሰር ይጀምራል፡ ይሄኛው ካንሰርም ሌላ ካንሰር ይዞ ይመጣል፡ ከዚያ በኋላ፡ ቤተ ክርሰትያን በሙሉ፡ መታመስ ይጀምራል። ከዚያም ወደ ቤተ ክርሰቲያን ትመጣላችሁ፡ ጉባኤው ሁሉ እንዲገባ፡ የጽዳት ሰራተኛው ደጆቹን ይከፋፍታል፡ ገብታችሁ ግን ቅዝቅዝ ትላላችሁ። አዎን፡ ይህ ትክክል እንደሆነ ታውቁታላችሁ። ቀዝቃዞች ትሆናላችሁ! የምታውቁት ሰው መጥቶ፡ አጠገባችሁ ሲቀመጥ፡ ዝም። “ድሮ’ኮ፡ በመንፈሰ የነቃን ሰዎች ነን።” አብራችሁ አገልግላችሁ፡ አሁን ምን ተገኘ? ታድያ አሁን፡ ምን ገጠመን? አያችሁ፡ ሐጥያታችሁ ለያያችሁ። ወንድሞቼ፡ በእግዚአብሄር ትጠየቃላችሁ። አሁን ጥሉን መፍታት አለብኝ።

204 በእኔ ላይ ምንም ሰህተት የለም፡ በሊዮ ምንም ሰህተት የለም፡ በመካከላችን የገባው ሰይጣን ነው። ትክክል። ነገራችሁን አሰታርቁ። ወደ እሱ ሂድና። ካልሰማህ፡ ወይም እኔ ካልሰማሁህ፡ በየትኛውም መንገድ ቢሆን፡ ለቤተክርሰቲያን ተናገር። በሠላሳ ቀን ውሰጥ መጥቶ ከቤተ ክርሰቲያን ጋር ካልታረቀ፣ ከኢየሱስ ጥበቃ ሥር ወጥቷል። ከዚያ እንሸኘዋለን። በትክክል እውነት ነው። ከዚያ ምን እንደሚፈጠር ጠብቁ። እናንተ የሚቻላችሁን አድርጋችኋል። እጃችሁን ሰብሰቡ። እግዚአብሔር ራሱ ተግሣጹን ይቀጥላል። ጥቂት ጊዜ እግዚአብሄር ከያዘው በኋላ፡ ለሰይጣን አሳልፎ ይሰጠዋል። ያኔ ራሱ ይመጣል። ካልመጣ ግን፡ እድሜው ያጥራል።

205 በመጽሐፍ ቅዱስ ውሰጥ ከእግዚአብሔር ጋር ያልተሰማማ ወንድም እንደነበረ አሰታወሳችሁ? ሰንቶች ይሄን ጉዳይ ታሰታውሳላችሁ? ከአሳዳጊ እናቱ ጋር የሚኖር ወጣት ነበር፡ እና ተመለሰ ቢሉት አልሰማ አላቸው። ጳውሎሰ ሰለሱ ሲናገር “ለሰጋው ጥፋት፡ ለዲያብሎሰ አሳልፌ ሰጠሁት፡” ብሏል። ይህ ሰው ከተገሰጸ በኋላ፡ በሁለተኛው ቆሮንቶሰ ውሰጥ፡ ተቃንቶ ታገኙታላችሁ።

206 አንድ ወንድም አለ፡ ጥሩ ጓደኛዬ ነው፣ ወንድማችን ሰባኪ ነው፡ ሰሙን መጥራት እፈልጋለሁ። ይህ ሰባኪ ወንድማችን፡ ወንድም ራሰሙሰን ይባላል። ብዙዎቻችሁ እዚህ የተቀመጣችሁ አገልጋዮች ሰሙ ወረቀታችሁ ላይ አለ። ቺካጎ ከሚገኘው ከተቋማት-ሕብረት የመጣ ሰው ነው። እና ይህ ሰው፡ አገልጋይ ልጅ አለው። ልጁ በድንገት፡ አንዲት ካቶሊክ ሴት አግብቶ፡ እንዲሁ ሄደ። እናም **ይህን፡ ያንን፡** እና **ሌላውን፡** ሁሉ—ሲያደርጉ፡ የሆነ ችግር ላይ ወደቁ። አባቱም ወደ እርሱ ሄዶ እንዲህ አለው፦ “ልጄ ሆይ፡ ሰማኝ፡ አሁንሰ አካሄድህን ታሰተካክላለህ ወይ አለው? ”

“አባዬ... ” አለ፡

ይሄውልህ አባቴ፡ ቤተ ክርሰትያናችሁ ተራ ወንበር ሰባሪዎች ናቸው አለው። አባቱም በድጋሚ “አሁንም፡ ሰማኝ፡ አካሄድህን ታሰተካክላለህ አታሰተካክልም? ” አለው፤

207 ልጁም አለው፦ “አባዬ፡ ስማኝ፡ አንተ ለእኔ አባቴ ነህ፡ እኔ ከአንተ ጋር ምንም አይነት ጥል መፍጠር አልፈልግም።” አለው።

208 ጉዳዩን ከዲያቆናት ጋር ለማነጋገር አንድ ዲያቆን ይዞ ወደ ልጁ ቤት አመራ። ገብቶም—ጠየቀው፦ “ዌስሊ፡ አሁንም እጠይቅሃለሁ።” “ይህን አካሄድህን በቤተክርስትያን ታስተካክላለህ አታስተካክልም? ” በማለት፡ ሁለት አጫጭር-መልሶች ሰጠው። “ዌስሊ፡ እኔ የቤተ ክርስትያኒቱ ፓስተር መሆኔን፡ አትርሳ። እኔ አባትህ ብሆንም፡ እግዚአብሄር አድርግ የሚለኝን ብቻ አደርጋለሁ። ከቤተ ክርስትያን ጋር ያለህ ጉዳይ በሰላሳ ቀናት እንድታስተካክል ዕድል ሰጥቼሃለሁ፡ ካላስተካከልክ ግን ከእግዚአብሄር መገኘት እናወግዝሃለን። አንተ ልጄ ብትሆንም፡ እርሱ አዳኜ ነው።” አክሎም፦ “እውድሃለሁ። ዌስሊ፡ እንደምወድህ አንተም ታውቃለህ። ቢያስፈልግ አሁን እሞትልሃለሁ። ይሁን እንጂ ከጌታ ቃል ጋር መታረቅ አለብህ። ተረዳኸኝ? ” በድጋሚ ነገረው፦ “እኔ ፓስተር ነኝ። የጉባኤው እረኛ ነኝ። ልጄም ሆንክ፡ አልሆንክ፡ ከእግዚአብሄር ቃል ጋር መታረቅ አለብህ። አልታረቅም ካልክ ግን፡ እኔም እረኛው ለመባል አልበቃም።”

209 ፓስተር ማለት፡ እንዲህ ነው። ወንድ ማለት ይህ ነው። አይመስላችሁም? ወንድ ማለት እንዲህ ነው። የገዛ ልጁን በደንብ ነገረው። “ልጁን ጎዳ፡” እንዲህ አለው። እርሱ ሲናገር፡ “ምን ነው? ማንን ትጎዳለህ፡ ሰውየውን፡ ወይስ፡ አዳኝህን? አለ፡” ከዚያ በኋላ “መንገዳችንን ቀጠልን፡” አለ። ይሁን እንጂ “ልጁ፡ አልመለሰም ብሏል። ስለዚህ... ቤተ ክርስትያንን ነገርኩ አለ።”

210 እንዲህ አላቸው፦ “በዚህ ጉዳይ ላይ፡ ልጄ፡ ዌስሊ፡ አልስማም ብሎኛል። ዲያቆኑን አልሰማም ብሎታል። ወንድም **እከሌ-እና-እከሌ**፡ ለዚህ ምስክር ነህ አይደል? ”

“አዎን፡ ምስክር ነኝ።”

“እሺ። ከዛሬ ጀምሮ ባሉ አራት ሳምንታት፣ እስከ እሁድ ቀን፡ ስምንት ሰዓት ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ይቅርታ ካልጠየቀ፡ ልጄን፡ ዌስሊን፡ ለሥጋው ጥፋት፡ ለዲያብሎስ አሳልፈን እንሰጠዋለን። ከዚያ በኋላ፡ በደሙ... የኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡ እና የቤተ ክርስትያን ጥበቃ አይኖረውም አላቸው።”

211 ያቺ ቀን ደረሰች። ፑልፒት ላይ ቆሞ፡ “ሁለት ደቂቃ ቀርተውታል፡” አላቸው። ጊዜው አለቀ። አላቸው፦ “አሁን፡ ስለ ልጄ፡ ዌስሊ ራስሞስን... ለዚህ ጉባኤ፡ እና ለልዑል እግዚአብሄር፡ እናገራለሁ፤ ያዳነን—ልጅህ፡ እንደሰጠን መመርያ፡ እና እንደሰጠን ቃል መሰረት፡ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል። እኛ አሁን፡ ቤተ ክርስቲያን ከእኔ ጋር በመሆን፡ ልጄን ለጥፋት-... ለሥጋው ጥፋት፡ ነፍሱ ግን እንድትድን፡ ለዲያብሎስ አሳልፈን ሰጥተነዋል።” ሌላ ነገር አልጨመረበትም። ለአንድ ለሁለት ሳምንት ወይም ለአንድ ወይም ለሁለት ወራት፡ ዝም ተባለ።

212 አንድ ቀን ማታ፡ ምስኪኑ ዌስሊ ታመመ። ህመሙም፡ ጸናበት። ዶክተሩን ጠራ። ዶክተሩም መጥቶ መረመረው። ትኩሳቱ መቶ አምስት ደርሷል። የህመሙ መንስኤ ግን ማግኘት አልቻለም። ብቻ መታመም ቀጠለ። ዶክተሩም “አንተ ወጣት፡ እኔ ምን እንደገጠመህ ሊገባኝ አልቻለም፡” አለው። ምን ማድረግ እንዳለበት ስላላወቀ፡ “ባለሙያ መጥራት አለብን፡” አለው። ልዩ

ባለሙያ ተጠራ፡ እና ባለሙያው ተጠርቶ መጣ። ወደ ሆስፒታል ወሰዱት፡ አጠቃላይ ምርመራ፡ አደረጉለት። “ምንም ልላችሁ አልችልም። ልጁ ግን—መሞቱ አይቀርም፡” አላቸው። ሚስቱ ቆማለች፡ ታለቅሳለች፡ ተረባብሻለች። ልጆቹ እዚህ እና እዚያ አልጋውን ከበውታል። ዶክተሩም፡- “በቃ። ይሞታል።” “ቀስ በቀስ፡ የልብ ምቱ እና አተነፋፈሱ እየቀነሰ ነው፡” አላቸው።

213 ልጁም “አባቴን ጥሩልኝ፡” አለ። ኧረ፡ አዎን። መደረግ ያለበት ይህ ነው። አዎን። “አባቴን ጥሩልኝ።” አባቱም፡ ልጁን ለማየት፡ በፍጥነት ወደ ሆስፒታል ሮጦ ወጣ። “አባዬ፡ አሁን አልችልም፡ እግዚአብሔር ግን ቃሌን ይሰማኝ፡ አሁን ስለ ሁሉ ንስሓ እገባለሁ። ሁሉንም ትክክል አደርገዋለሁ። አዎን፡ እታረማለሁ።” አለ። ትክክል፡ እንዲህ ነው፡ ወንድሜ። ወድያውኑ አተነፋፈሱ መስተካከል ጀመረ።

214 እና በሚቀጥለው እሁድ፡ በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ቆመ። እንዲም አላቸው፡- “በዚህች ቤተ ክርስቲያን ፊት፡ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን ሠርቻለሁ። የመጋቢ ቃል አልሰማ አልኩ። እኔ—ዲያቆኑን አልሰማም አልኩ።” “እኔ ላደረኩት ክፋት ሁሉ ይህችን ቤተክርስቲያን ይቅር እንድትለኝ እጠይቃለሁ፡” አላቸው። “እግዚአብሔር ሕይወቴን አትርፎልኛል።” እላችኋለሁ፡ ትክክለኛ እርማት ተቀብሏል። አዎን። አያችሁ፡ ማድረግ ያለባችሁ ነገር ይህ ነው። አያችሁ? ብቻ፡ እናንተ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ አድርጉት! አያችሁ?

215 አሁን ግን እዩት፡ አሁን፡ የምናደርገው ነገር፡ የቦርድ ሰብሰባ ጠርተን፡ “እሺ፡ ምን እንድርግ፡ ዝም እንበል... ” እንባባላለን፡ የኛ ህብረት ማለቴ አይደለም፡ ነገር ግን እንደ ህዝበ ፕሮቴስታንት። የቦርድ ሰብሰባ ጠርተን፡ “ስለ ጆንስ ምን እናድርግ፡ ምን ይመስላችኋል? ምን ብናደርግ፡ የሚሻል ይመስላችኋል? ሜቶዲስት ቢሆን ከእኛ የተሻለ አባል ይሆናል ብዬ አስባለሁ እንላለን።” በቃ ይሄ ነው። ይህ ፍጹም፡ ስህተት ነው። ወኅቻቸውን መከተል የሌለብን ለዚህ ነው። ቢሾፕ እከሌን፡ ልንጠራው ይገባል (መጠርያው-ማነነው... የጴንጤቆስጤ የአጥቢያ መሪዎች? ምን ብላችሁ ነው፡ የምትጠሯቸው? “የአጥቢያው ቄስ”)—የዚህን ሰው ምግባር ለማየት ይጠራ ይባላል።

216 እኛ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል። በሐይማኖት ተቋማት የማንታለልበት ምክንያትም ይህ ነው። ከእንደነዚህ አይነት ነገሮች እንራቅ። አሜን። አትናደዱብኝ፡ ተናዳችሁብኛል እንዴ? አትናደዱ። እሺ። ምናልባት ነገ ማታ ከባባድ ጥያቄዎች አስተናግዳለሁ ብዬ እገምታለሁ። ቢሆንም፡ ትክክለኛው ነገር፡ ይህ ነው። አያችሁ? ይሄን አትርሱ።

217 አሁን ይህን እላለሁ። ከተለያዩ ሐይማኖት ተቋማት ለመጣችሁ ሰዎች፣ ሐይማኖት ተቋሞቻችሁ፡ እና፡ ወንድሜ፡ ክርስትያን አይደላችሁም ማለቴ አይደለሁም። በሐይማኖት ተቋማችሁ ውስጥ ብዙ እውነተኛ ክርስትያኖች የሉም ማለት አይደለም። እኛ የሐይማኖት ተቋም ያልሆንንበት ምክንያት እየገለጽኩላችሁ ነው። ምክንያቱ፡ እኔ ይሄን ለመናገር አልተጠራሁም። አይደለም፡ ወዳጄ። እንደማላደርግም እርግጠኛ ነኝ። ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ሊነግሯችሁ የሚሞክሩ አሉ። እኔ ግን እግዚአብሔር ወንጌልን እንድሰብክ ከጠራኝ፣ እግዚአብሔር እንድሠራው በነገረኝ መንገድ እሰብካለሁ። ይህም፡ በመጽሀፍ ቅዱስ እንደ ተጻፈው መሰረት ነው። እንዲህ አይነት ነገር አልደግፍም፡ ምክንያቱ... እግዚአብሄር ይፈርድብኛልና። ተኩላ፡ ወይም ጠላት፡ እየመጣ—

አይቼው—ካልሰጠነቀቅኳቸው ግን፡ እግዚ አብሄር ከእኔ ይፈልጋቸዋል። ካሰጠነቀኳችሁ ግን፡ ያኔ ጉዳያችሁ ይሆናል። ገባችሁ?

218 አስታውሱ፡ “በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ቀን ይመጣል። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፣ ጉረኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች ይሆናሉ።” እያችሁ፡ ተሳዳቢዎች ይሆናሉ፡ “ኦህ፡ የተአምራት ዘመን አልፏል ይላሉ። የባለጌዎች ጉባኤ ናቸው። እንዲህ ብሎ ነገር የለም።” ያረጀ ሐሰተና ነብዪ ነው። “አሁን፡ ሴቶቻችን ከወንዶቻችን እኩል የሆነ ስሜት እንዳላቸው እናውቃለን።” በዚህ ላይ አንዳች አልጠራጠርም፡ የእግዚአብሔር ቅዱሱ መጽሐፍ ግን ፑልፒትን ከልክሏት ብሏል። እያችሁ፡ ይሄ ለኔ—በቂዬ ነው። አዎን በቂ ነው። እሺ። እያችሁ?

እናም እላችኋለሁ፡ “በሕብረታችን ውስጥ ብዙ መልካም ሰዎች እንዳሉን ሁሉ፡ በየሐይማኖት ተቋማት ውስጥም፡ እጅግ ብዙ፡ መልካም ሰዎች አሉ።” ሰለ ሐይማኖት ተቋማት ግን እኔ አልልም፡ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ያወግዘዋል። በትክክል። ሰለዚህ፡ እኔ እንዲህ ሰል፡ በየድርጅታችሁ መልካም ሰዎች የሉም ማለቴ አይደለም። ይደንቃል። ብዙ መልካም ሰዎች አሉ። ከሁሉም ድርጅቶች እና ከካቶሊክ፡ መልካም ሰዎች፡ በጥቂቱ ተዋውቄአለሁ። ያገኘኋቸው ሁሉ፡ በጣም መልካም አባላት ናቸው።

219 ወዳጆች ሆይ፡ አሁን፡ እግዚአብሄር ቢፈቅድ፡ በሚቀጥሉ ሁለት ጥናቶች፡ ይሄን ርዕሰ የምናቀርብበት መንገድ፡ ምናልባት… ነገ ጧት ወይም ከሰአት ምን ማድረግ እንዳለብን ወይም እንደሌለብን፡ አይተን ለመረዳት፡ አሳውቃችኋለሁ። አሁን የምንሞክርበት ምክንያት፡ አንድ ነጥብ ላይ ለማድረስ ፈልጌ ነው። እና፡ ሰው ጋብዛችሁ መምጣት ከፈለጋችሁ፡ ደስ ይለናል ይዛችሁ ኑ። አንድ ነገር ግን ተጠንቀቁ፡ ሰሕተትን ብቻ ለቅሞ ለመሄድ—አትምጡ። እናንተ ኑ… እኔ የማወራው ነገር ሁሉ ግን—ለራሴ ጉባኤ፡ እንደሆነ እወቁ። ይህንን ከጉባኤዬ ውጭ አላሰተምርም፣ ምክንያቱም ሌላው የሌላው ሰው ጉዳይ ነው። የዚያ መንጋ እረኛ፡ እራሱ። ሌላው—እንደ እኔ… [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

220 በቀጥታ ወደ ዘፍጥረት እንመለስ፡ ከዚያ አውጥታችሁ፡ የት እንዳለ ታገኙታላችሁ። አሁን ወደ ዘፍጥረት ተመልሰን፡ ዲቃላ ልጅ እስከ አሥራ አራት ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ የማይገባበትን ምክንያት እናያለን። ያንን ሐጥያት እንዲደመሰስ ምን ያህል ይፈጃል… አራት መቶ አመታት ይፈጃል። የወላጆች በደል—በልጆችና በልጅ ልጆች እንዴት እንደሚተላለፍ፡ በዘፍጥረት እና በሌላውም ሁሉ፡ ያለውን አጀማመር እንዴት እንደሆነ እናያለን።

221 ከዚያም… ወደ ኋላ ተመልሳችሁ፡ እግዚአብሄር፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ አንዲት ነጠላ አቶም ሳይፈነዳ፡ ገና አንዲት ብርሃን ወደ ሕልውና ከመምጣትዋ በፊት፡ ፍጥረታትን ሁሉ፡ እና በምድር ሊመጣ ያለውን ሁሉ እንደሚያውቅ ታያላችሁ። “ፍጻሜ የሌለው” ማለት… ምን ማለት እንደሆነ፡ ማብራራት ወይም መተንተን የማይችል ሰው እዚህ ይኖር ይሆን። ካሜራዎቻችሁ—ያለ ከልካይ እንዲቀዳ እንደምታስተካክሉት አይነት ነው። በቃ፡ ከጀመረ፡ የሚቀጥል ማለት ነው። ፍጻሜ የሌለው! እያችሁ? ሰለዚህ፡ በዚህ ውሰን አእምሮ፡ ፍጻሜ የሌለውን አእምሮ ያዘለውን ነገር መረዳት ፈጽሞ አይቻልም። እያችሁ፡ አይቻለንም። እያችሁ? እናንተም፡ አይቻላችሁም። ነገር ግን ዝም ብላችሁ፡

መንፈሳችሁን ከጠበቃችሁ፡ በዚያ ውስጥ የሚስማችሁ ነገር ይኖራል። ስለዚህ—ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ቀድሞ ወደ ነበረ፡ ወደ ቅዱስ ቃል ልመልሳችሁና አንድ ነገር ታያላችሁ።

222 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ ይናገራል። ሲጠናቀቅ ለመስማት፡ ምናልባት፡ ነገ የማትመለሱ አንዳንዶች ካላችሁ፡ በደንብ ተከታተሉኝ። ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የታረደ፡ የእግዚአብሔር በግ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። አይደል'ዴ? መቼ ነው የታረደው? ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ። ይህ ዓለም ማለት፡ ከጸሀይ መፈንጠቅ ጋር ተያይዞ፡ ከተፈጠሩ የአቶም ስብርባሪ፡ የተፈጠረች ዓለም ከመኖሯ በፊት። ገና፡ የመጀመርያው አቶም፡ ምናልባትም በራሪ ኮከብ ከጸሀይ ፈንጥቆ ከመውጣቱ አስቀድሞ፡ ገና አንድ በራሪ ኮከብ ከመውጣቱ ከአንድ መቶ ቢልየን ትሪልየን ትሪልየን ትሪልየን ዓመታት በፊት፡ ክርስቶስ ታርዷል። እግዚአብሄር በታላቅ ሐሳቡ አንድ ነገር ካሰበ፡ ያለቀለት ጉዳይ ነውና። እግዚአብሄር "ይሁን፡" ካለ፡ ሆነ ነው። አንድ መቶ ቢልየን አመታት ቢወስድም'ኳ፡ እርሱ ይሁን ብሎ በተናገረበት ቅጽበት ሆኗል። "በጉ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ በታረደ ጊዜ።" ያው መጽሐፍ ቅዱስ እና ያው መንፈስ ቅዱስ፦ "ዓለም ሳይፈጠር በፊት ስማችን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ መኖሩ" ጻፈ።

223 ስለዚህ "በእርያም የተጻፈ አዲስ ስም አለ፡" ብሎ የዘመረው ዘማሪ፤ ምንም እንኳን ጥሩ ትርጉም ቢኖረውም፡ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ግን አይደለም። አያችሁ? ስማችን ገና ዓለም ሳይፈጠር በፊት... በክብር ተጽፎ የነበረ ነው። በጉ በታረደ ጊዜ ስማችን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ተቀምጧል።

224 አንዲት ቃል—ላንብብላችሁ። አንድ ደቂቃ ትጠብቁኛላችሁ? አሁን ወደ ልቤ ስለመጣ ነው። የሚገኝበት ቦታ የማውቀው ይመስለኛል። እርግጠኛ አይደለሁም። ስላቆየኋችሁ ይቅርታ አርጉልኝ፡ እንደነገርኳችሁ ግን፡ እኩለ ሌሊት ቢሆንም'ኳ ችግር የለውም። ይህ ቃል ግን—በጣም ወሳኝ ቃል ስለሆነ፡ ማዳረስ—አለብኝ።

አሁን ከእኔ ጋር የሮሜ መጽሐፍ ክፈቱና፣ ከእኔ ጋር ይህን እንድታነቡ እፈልጋለሁ። እስቲ፡ ሮሜ ሰዎች ውስጥ፡ ላላገኘው ከቻልኩ፡ እስቲ፡ አሁን እንይ። አሁን ሁላችንም ሮሜ 8 እንክፈት፡ እና—ሮሜ ሰዎች 8ኛው ምዕራፍ 28ኛው ቁጥር እናነባለን። እና ስታነቡት በመንፈስ ሆናችሁ እንድታነቡት እፈልጋለሁ። እግዚአብሄር የሚናገረንን አሁን ስሙት።

> **እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት፡ ነገር ሁሉ... ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።**
>
> **አስቀድሞ ያወቃቸው፡...**

225 ይህ የሚያስረዳችሁ... አብራችሁኝ ታነባላችሁ? "ልጁ... "

> **ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፡ አስቀድሞ ያወቃቸው** (በጣም ጥሩ) **የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወሰናቸውና።**

**አሰቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ፡ ጠራቸው፡ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ፡ አጸደቃቸው፡ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ፡ አከበራቸው።**

226 ከዓለም ምሰረታ ጀምሮ! እግዚአብሄር ወደ ምድር ሲመለከት… እግዚአብሄር፡ ስራውን ሲሰራ፦ “እስቲ፡ አሁን፡ ምን እና ምን ላድርግ… ኧይይ፡ አሁን ምን ምን እናደርጋለን?” አይልም፡ እያችሁ? እንዲህ ብሎ ነገር የለውም…

227 ሐጥያት ወይም፡ ሐጥያተኝነት፡ የተጣመመ ጽድቅ እንደሆነ፡ አትርሱ። ዲያብሎስ መፍጠር አይችልም። ሁላችሁ፡እያንዳንዳችሁ፡ ይሄ ገብቷችኋል? ይሄ የዚህች ቤተክርስትያን ዶክትሪን ነው። ዲያብሎስ መፍጠር አይችልም። እግዚአብሄር የፈጠረውን ያጣምማል እንጂ። እስቲ፡ መጣመም ምንድነው? እዚህ ያላችሁ፡ ብዙዎቻችሁ፡ አዋቂዎች ትመሰሉኛላችሁ። ትዳር ያለን ሰዎች ነን። ይሄን ሰሙኝ። ያገባችሁ ወንዶች እና ያገባችሁ ሴቶች እንደ ባልና ሚስት አብራችሁ መኖር ትችላላችሁ፡ እና ሴቶቹ ከባሎቻቸው ጋር እስከሆነ ድረስ፡ ከዚህ በፊት ምንም እንዳልፈጸሙ… እንደ ድንግል ሴት ናቸው። በትክክል ናቸው። ይህም፡ ሕጋዊ እና ሕግ የሚደግፈው ስለሆነ፡ ምንም ችግር የለበትም። እንዲደረግ የእግዚአብሄር ፈቃድ አለበት። ሚስትህ የምታደርገው በእግዚአብሄር ፊት ጽድቅ ሲሆን፡ ከሴቶች መካከል፡ ሌላ ሴት የምታደርገው ያንኑ ድርጊት፤ ይህ ተመሳሳይ ድርጊት ሌላ ሴት ብታደርገው፡ በእግዚአብሄር ፊት፡ የሞት ኩነኔ አለባት። ምን ስለሆነ? የተጣመመ ጽድቅ ስለሆነ፡ እያችሁ፡ የተጣመመ ጽድቅ ነው። ስለዚህ ዲያብሎስ፡ እግዚአብሄር የፈጠረውን ብቻ ያጣምማል እንጂ፡ መፍጠር አይችልም።

228 ውሸት ምንድነው? እውነት ሲጣመም ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው፦ “ኧረ፡ ሰሙኝ፡ ቅዳሜ ማታ፡ ልክ፡ ዘጠኝ ሰዓት ላይ፡ ቢሊ ብራንሃም ጀፈርሰንቪል ነበር፡” ትክክል። “አንቲዝ ሳሎን ላይ፡ ሰክሮ ነበር፡” ውሸት። ምንድነው? ጀፈርሰንቪል መኖሩ። ትክክል ነው። ጽድቅን ውሸት አድርጎ ማጣመም ነው። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ? እያችሁ፡ ውሸት እውነትን አጣመመ። የት እንደነበርኩ ይተርካል። “ቸርች ውስጥ፡ እየሰበኩ፡” ቢባል፡ ኖሮ፡ ትክክል ነው። ይህ ማለት ጽድቅ ነው። ጽድቅ ተናገረ ይባላል። “ባንኮኒ ላይ፡ እየጠጣ፡” ውሸት። እያችሁ፡ ጠማማ፡ የተጣመመ እውነት ነው። አባባሌ ገባችሁ? ክፋት ሁሉ፡ ጠማማ ጽድቅ ነው።

229 ሞት፡ ምንድን ነው? ጠማማ፡ ሕይወት። በሽታስ? ጠማማ፡ ጤና። ጤነኛና፡ ጠንካራ ሰው ልትሆን ይገባል። ቢሆንም። በሽተኛ ከሆንክ፡ ምን ማለት ነው? ጤናህ ታውኳል ማለት ነው። እያችሁ? ፍሬ ነገሩ ይህ ነው። ቆንጆ፡ እና ወጣት ሴት፡ ነበርሽ፣ አንተም ጠንካራና፡ ቆንጆ ወንድ ነበርክ። አሁን ምን ገጠመህ? እየሸመገልክ፡ የፊት መጨማደድ ጀምሮሃል። ምን ገጠመህ? እያችሁ፡ ህይወት፡ ሲጣመም ነው፡ እንደገና ወደ ነበርክበት እየተመለሰክ። እያችሁ? መመለሰም አለበት። የጌታ ሰም ይባረክ! ዳግም እንደሚመልሰው ጌታ ቃል ገብቷልና። እንደው በትክክል—በትክክል (እሱ እዚህ መሆኑ እናውቃለን)፡ በትክክል፡ ጌታ እንደገና ይመልሰልናል። እንደሚመልሰልን ቃል ገብቶ በራሱ ምሏል። ፍጻሜው ይህ ነው።

230 ታድያ፡ እኛስ፡ ምን አይነት ሰዎች መሆን ይገባናል? ነግሮች እንዴት እንደሚፈጸሙ አስተውላችሁ ተከታተሉኝ። አስቀድሞ ያወቃቸው እነዚህን ደግሞ፡ ጠራቸው፡ የጠራቸውም፡ አጸደቃቸው። መቼ? ከዓለም ፍጥረት በፊት፡ ዓለም ከመጀመሩ በፊት። ይህ ቃል ምን ማለት እንደሆነ ወደ መተንተን ከገባን፡ ብዙ ሰዓታት እንፈጃለን፡ ይሁን እንጂ ወደዚያ መግባት አሁን—አንፈልግም። ክፋቶች ሁሉ ግን፡ ወደ ክፋት የተጣመሙ ጽድቆች ናቸው። የዲያብሎስ ስራ ይህ ነው።

ስለዚህ፡ ክፉ እና መልካም የምታውቁበት፡ ወደተጠያቂነት ዕድሜ ስትደርሱ፡ ከስሕተት ለመመለስ ትገደዳላችሁ። ምክንያቱ፡ በሐጥያት ተወልዳችሁ፡ በአመጽ የተጸነሳችሁ፡ ሐሰትን እየተናገራችሁ ወደ ምድር የመጣችሁ ናችሁና። በመሰረቱ—በፍትወት የተወለዳችሁ ስለሆናችሁ፡ አዲስ ልደትን ለማግኘት፡ እና ወደ ገነት ለመግባት፡ ዳግም መወለድ አለባችሁ። ምክንያቱ፡ እዚህ የተወለዳችሁበት መንገድ ይህ ነው...

231 ጅሆቫ ዊትነሶች ዳግም ልደት የሰጋ ትንሳኤ ነው ማለታቸው፡ ከእውነት ምን ያህል እንደራቁ ይታያችኋል? አያችሁ፡ እንዲህ አይደለም። ገባችሁ? ሌላ ነገር ነው...

232 እናንተ አሁን፡ በጊዜ አድማስ ውስጥ ናችሁ። ዘለአለማዊ የሆነ ነገር ግን፡ ጅማሬ እና ፍጻሜ የለውም። ዘለአለማዊ የሆነ ነገር ሁሉ መጀመርያ የለውም፡ መጨረሻ በፍጹም አይኖረውም። ገባችሁ? ስለዚህ የእግዚአብሔር አካል ከሆናችሁ፡ በእናንተ የሚኖረው መንፈስ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የለውም፡ እናንተም በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ምክንያት ዘለአለማዊ ናችሁ። አያችሁ? ልክ—**አጋፔ** ፍቅር—ሲወርድ፡ **ፊልዮ** ፍቅር እንደሚሆን፡ ከዚያም ሲወርድ የምኞት ፍቅር እንደሚሆን እንደዚያ ነው። እየተበላሸ ሄዶ የብልሽት ክምር እስኪሆን ድረስ፡ እየወረደ እና እየወረደ ይሄዳል። ኢየሱስ ግን፡ ከወረደ እና ከተበላሸው ማንነት፡ እጅግ፡ ከፍ ወዳለው ማንነት ከሞት ወደ ህይወት፡ ከበሽታ ወደ ጤና፡ ከክፋት ወደ ጽድቅ፡ እንዲያወጣን፡ በተመሳሳይ መሰላል፡ ከሰማይ የወረደበት ብቸኛ መንገድ ይህ ነው። አያችሁ? የተዋረዱትን ወደ ክብር ሊያወጣ፡ ከከበረው ወደ ተዋረደው መጣ። እኔ በጸጋው እርሱ እሆን ዘንድ፡ በክብር ያለውም ዙፋን ከእርሱ ጋር ወራሽ እሆን ዘንድ፡ እርሱ እኔን ሆነ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? በእነዚያ አተሞች።

አሁን ተከታተሉኝ። የአሁኑ ዓለም በእነዚያ አተሞች ውስጥ ከመጀመሩ በፊት፡ ያኔ ምን ሊሆን እንደሆነ ጌታ ባየ ጊዜ፡ አንተን አይቶሃል፡ እኔን አይቶኛል፡ እያንዳንዱ ቁንጫ፣ እያንዳንዱ ዝንብ፣ እያንዳንዷ እንቁራሪት፣ እያንዳንዷ ቢንቢ በእርሱ ዘንድ ታይታለች። በምድር ሊመጣ ያለው ሁሉ፡ ያኔ አይቷል። አዎን፡ በርግጥ አይቶታል።

233 ስለዚህ፡ ፈጽሞ፡- "አንድ ቀን ልጄን እልከዋለሁ፡ ምናልባት የሚያዝንለት አንድ ሰው ያገኝ ይሆናል። እጅግ የሚያሳዝን ፍጻሜ ይሆናል፡ ምናልባትም የሆነ ሰው ይድን ይሆናል" አላለም።

234 ማን እንደሚድን አስቀድሞ ያውቃል! አዎን፡ ወዳጄ። አንዳቸውም ክፉ እና ደጉ መለየት ከመቻላቸው በፊት ነበር፡ "ኤሳውን ጠላሁ፡ ያዕቆብን ግን ወደድሁ፡" ያለው፤ ይህም ማንነታቸው በትክክል ያውቅ ስለነበረ ነው።

አስቀድሞ ያውቃል። ሁሉንም ያውቃል። ከመወለድህ በፊት፡ ወይም ከዓለም ምስረታ በፊት፡ ምን እንደምትሆን እርሱ ያውቅሃል።

235 አሁን ተከታተሉኝ። እናንተም እንደምታውቁኝ፡ እኔ—እኔ—ታጣቂ ነኝ። ጠመንጃን—እወዳለሁ። እና ከቴክሳስ የመጡ ጥቂት እህቶች፡ ከቴክሳስ ይመስሉኛል፡ እና ሰዊፍት፡ ሁለት-ሃያ ሰዊፍት አምጥተውልኛል። ሲተኰስ እጅግ ሃይለኛ ጠመንጃ ስለሆነ። ሁሌ ላየው እፈልግ ነበር። በኖረኝ የምለው ጠመንጃ ነበር። ባለ ሃያ-ሁለት ጠመንጃ፡ እና ባለ አርባ-ሰምንት-ጠጠር ጠመንጃ ነው። በእጅ ማቀባበልም ትችላላችሁ። ይሁን እንጂ፡ “እጅግ አደገኛ ነው፡ በእጅ እንዲቀባበል፡” ፋብሪካው አይመክርም። ይሁን እንጂ ያንን ጠመንጃ በሴኮንድ አምስት ሺ ጫማ ብታነጣጥሩትም፡ ዒላማውን አይስትም። አምስት ሺ ጫማ ማለት፡ በሴኮንድ አንድ ማይልስ ማለት ነው። በሌላ አባባል፡ ከሁለት መቶ ያርድ ርቀት ላይ፡ ያለ ጭልፊት ማለት ነው። ጭልፊቱን ብትተኩሱበት፡ ጠመንጃው እናንተን ከመግፋቱ በፊት ላባዎቹ ሲረግፉ ታያላችሁ። አያችሁ? ወይም፡ የእስቴኪኒን ጠፍጣፋ ጫፍ፡ ውሰዳችሁ፡ ባሩድ አምጥታችሁ፡ ከባሩዱ **ጋር** ቀላቅሉት፡ የሚበቃችሁን ያክል እስቴኪኒ ላይ በመጨመር፤ ከዚህ ህንጻ መጨረሻ ላይ ተቀምጦ የሚያያችሁ፡ የጉድጓድ አሳማ ላይ ተኩሱበት። ምን ይሆናል? በፍጠት ስለሚምዘገዘግ፡ አረሩ ይበታተናል፡ እና-... ከዚህ እዚያ የሚደርሰ ጨርቅ ብትዘረጉም፡ ጨርቁ ላይ የረገፈ ቅንጣት ያህል ቅሪት አታዩም። ከመቶ ቢልየን አመታት በፊት፡ ወደ—ነበረበት፡ ወደ ድሮው ሁኔታ፡ ይመለሳል። ተራ አመድ ወይም የእሳተ ጎመራ አመድ አይሆንም ከዚያ እጅግ ወደ ኋላ ይመለሳል። ኮፐርን እና ሊድን ወደሚሰራበት ወደ ኦሪጂናል አሲድነቱ ወደ ኋላ ይመለሳል። እጄ ላይ፡ ጥይት ይዣለሁ፡ ከሁለት ሴኮንዶች በፊት ባለ አርባ-ሰምንት ጥሬ ባሩድ፡ የነበረው ጥይት ወድያውኑ ከመቶ ሚልዮን አመታት በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ ይቀየራል። ምናልባት ምድር ሌላ አንድ መቶ ሚልየን ዓመታት የመኖር ዕድል ካገኘች፡ እንደገና ጥይት ይሆናል፡ እንደገና ወደ ኮፐርነት ስለሚመለስ፡ በድጋሚ ጥይት ይሆናል።

236 አሁንም እግዚአብሄር ያደረገውን ነገር ተመለከቱና፡ እጅግ ትወዱታላችሁ። ወደየቤታችሁ ትሄዳላችሁ፡ አርፍዳችሁ ትተኛላችሁ። ከዚህ—በፊት—ከምትወዱት መውደድ አብዝታችሁ ትወዱታላችሁ። እግዚአብሄር፡ እናጺ መሆኑን ሰንቶች ታውቃላችሁ? ኮንትራክተር ነው። እናጺ ነው። እሺ። በደንብ አድምጡኝ። አሁን፡ ያኔ ያኔ በጥንቱ፡ ወይም... የጊዜ ቅደም ተከተል በመጠቀም... የክሮኖሎጂስቶች እሳቤ እንጠቀማለን። እግዚአብሄር፡ ዓለምን፡ መፍጠር ሲጀምር፡ ከአንድ መቶ ቢልየን አመታት በፊት፡ ነበር የጀመረው። ያኔ፡ ጌታ በአእምሮው ውስጥ የያዘው የራሱ... እሳቤ ነበረው።

237 ምናልባት እናንተ “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ጌታ ይሄን ያክል ገናና ከሆነ፡ ዲያብሎስ ሐጥያትን እንዲያደርግ ፍቃድ ለምን ሰጠው?” ትሉኛላችሁ፤ ዲያብሎስ ገና ሳይፈጠር፡ ዲያብሎስ እንደሚሆን፡ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው። ክብር ይሁን! መንፈሳዊነት ተሰማኝ። ኦህ፡ ማይ! ዲያብሎስ ገና ሳይፈጠር፡ ዲያብሎስ እንደሚሆን፡ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው። አሁን “ምን ማለት ነው?” ብላችሁ ጠይቁ፡ እንዲሁም፡- “ዲያብሎስ እንዲሆን ለምን ፈቀደለት ብትሉ?” እግዚአብሄር መሆኑ እንዲታወቅ ነው። የፈቀደለት ለዚህ ነው። “ክፋ እንዲኖር ለምን ፈቀደ? ለምን?”

238 ማን ይቀድማል፡ አዳኝ ወይስ ሐጥያተኛ? የቱ ይቀድማል? አዳኝ ይቀድማል። ማን ይቀድማል? ፈዋሽ ወይስ የታመመ ሰው? ሐጥያተኛ እንዲኖር ለምን ፈቀደ? በመገለጫው አዳኝ ስለሆነ ነው። ሐጥያተኛ ባይኖር ኖሮ፡ እንደ አዳኝ ባልታወቀም ነበር። ሃሌሉያ! ነገሮች ሁሉ በክብሩ ዙርያ የሚሰሩ ናቸው። "ሸክላ ሰሪውን እንዲህ ይላልን... ማለቴ፡ ሸክላ ሰሪውን፡ 'ለምን እንዲህ ሰራኸኝ ይለዋልን?'" መንኰራኩሩን የያዘው ማን ነው? ጭቃውንስ የያዘ ማንነው? ሁሉን የያዙ የማን እጅ ናት? ጳውሎስ ሲናገር፦ "አንተ ሞኝ ሰው፡ ስለዚህ አሳብ ፎርኦንን እነሳሁ አይልምን?" ይላል እንጂ። አስቀድሞ ያውቀዋል። ዓለም ሳይፈጠር፡ ማን ምን እንደሚሆን ያውቃል። አዳኝ ይሆን ዘንድ፡ ሐጥያት ይሁን አለ። ፈዋሽ ይሆን ዘንድ፡ በሽታ ይሁን አለ። ፍቅር ይሆን ዘንድ፡ ጥላቻ ይሁን አለ። አዎን፡ ይሁን አለ። አምላክ ነውና፡ መገለጫውም ይህ ነው። ስለዚህ መገለጫዎቹን የሚያሳይበት አንዳች ነገር ሊኖረው ያስፈልጋል።

239 ሌሊት እንደሆነ እንዴት ታውቃለህ፣ አለመሆኑንስ እንዴት ታውቃለህ? ቀን ብቻውን ቢሆን፡ የሌሊት መኖር እንዴት ታውቃለህ? ስለዚህ የሌሊት መኖር፡ ቀንን ለማሳየት ነው። አዎን፡ አለ። አሜን። ያደረገውን አያችሁት?

240 ነገር ግን ዓለም ሳይፈጠር፡ ያኔ ድሮ በነበረ ጊዜ፡ ይህን አሮጌውን ፀሐይ ሳይወሰድና አሁን በምንኖርበት በዚህች አሮጌ ኮከብ፡ በዚች ምድር ዙሪያ ሳያንቀሳቅሰው፡ በፀሐይ ቀርጾ፡ በጸሓይ ዙርያ ከማኖሩ በፊት። ጸሐይ **ይህ** ነው፡ ብሎ ወሰኖታል። በዚህ **በኩል** ጸሐይ ቀርጾ፡ ለመቶ ቢልየን አመታት እዚሁ እንዲንጠለጠል አደረገው። ምን እያዘጋጀ ነበር? ጋዞችን። ከዚያም **ወደዚያ** በኩል በተንቀሳቀሰ ጊዜ፡ ሌላ ነገር ሰራ። ምን ሰራ? ፖታሽየም ሰራ። ከዚያም **ወደዚህ** አቅጣጫ በዞረ ጊዜ፡ ምን ሰራ? ካልሽየም ሰራ። ምን ሰራ? እኔን እና እናንተን ሰራን። ምን እየሰራ ነበር? እንደ ኮንትራክተር ሁለት-በ-አራት እና ሁለት-በ-ሰምንት እያነጠፈ፡ ቆርቆሮውን፡ እና ቋሚ ግድግዳዎችን እየሰቀለ፡ ስንት ህንፃዎችን እንደሚገነባ ያውቃል። እኛን ሁላችንም ዓለም ወደ መኖር ከመምጣቷ በፊት፡ ከአስራ ሰድስት የከርሰ ምድር ንጥረ ነገሮች፡ ሰርቶ አስተኝቶን ነበር። እርሱም... በዚያን ጊዜ ምን አይነት እንደነበረ አላውቅም፡ ሞላላ ሊሆን ይችላል። ወርቅን፣ ኮፐርን፣ ናሰን፣ ውሃን፣ እነዚያን ነገሮች ሁሉ ለምን ሰራቸው? ኮንትራክተር ስለሆነ። አናጺው... እያንዳንዱ ነገር፡ እንደየቅርጹ እና እንደየ መልኩ ተቀርጾ፡ ቦታ ቦታ አሰይዞት ነበር። ሁሉንም ነገር ሰርቶ በጨረሰ ጊዜ፣ ታላቅ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሆነ። ትንሽ ካልሲየም ለመሥራት፡ እሳተ ገመራዎቹን ለመቶ ሚሊዮን ዓመታት አስታቅፎ አቆያቸው። ምንድነው? አካላችሁ ነው።

241 ስለዚህ፡ በምድር ላይ አንድ የህይወት ነጥብ ከመምጣቱ በፊት፣ ሰውነታችን እዚህ ተቀምጦ ነበር። ሃሌ ሉያ! አንድ የእርጥበት ጠብታ ወደ ምድር ከመውረዷ በፊት፡ እዚህ ተኝተን ነበርን። አዳም በኤደን ገነት ወዲያ-እና-ወዲህ በተጓዘ ጊዜ፡ እኔ እዚህ ተኝቼ ነበር። ኣሜን። አዎን፡ ጌቶች ሆይ። ክብር፡ ይሁን! ኪሩቤል፣ የንጋት ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ፣ የእግዚአብሔርም ልጆች በደስታ እልል ሲሉ፡ የህይወት እስትንፋስ እስኪነፍስ ድረስ ተኝቼ እየጠበቅሁ እዚሁ ነበርኩ። እዚህ ነበርኩ። እዚህ ሰራኝ፡ ስጋየንም እዚህ አስተኝቶ አቆየ። አዎን፡ ወዳጄ። ባይሆን ግን ከየት መጣ? ኸረ? እንዴት እዚህ ደረሰ? እግዚአብሔር በዚህ ውስጥ አስቀምጦት ነበር። እግዚአብሔር

ሠራው። እኛ ከአስራ ስድስት ንጥረ ነገሮች፦ ከፔትሮሊየም፣ ፖታሽ፣ እና የጠፈር ብርሃን፣ ተጨማሪ ምን-አለ። አያችሁ፡ እዚሁ ተኝተን ነበር።

242 ታዲያ ምን ተፈጠረ? ከዚያም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን፦ አሁን አካል እንለብሳለን፡ "አንተም ውጣ፡ እኔ ፍቅር ነኝና አንተም የእኔ ነህና። ለአለም፡ ፍቅር ልታደርግ፡ ትሄዳለህ፡ አሁንም ሂድና ለዓለም ፍቅር ሰጣት።" ታላቁ መንፈስ ቅዱስም፡ እኛ አሁን እንደምንሰለው፡ እንደምናሰበው፡ ወጣ እንዴ። እንደዚያ አይደለም። ይቅርታ አርጉልኝ። እርግጥ ነው፡ መንፈስ ቅዱስ እና እግዚአብሔር አንድ-ዓይነት፣ ባለ-አንድ ዓላማ፣ አካል ነው። እና ክንፋን በምድር ላይ ዘርግቶ፡ ማቀፍ ጀመረ። ማቀፍ ማለት ምንድነው? ደሮ "ኩኩ፣ ኩኩ፣ ኩኩ።" እጮኸች ጫጩጦቿን፡ አቅፋ፡ እንደምትወዳቸው፡ ኦህ!

243 "ሕይወት ሆይ፡ ተገለጥ!" ብሎ ጮኸ። ከዚያ ዙሪያውን ተመለከተ። "በዚህ ምድር ላይ ውበት እፈልጋለሁና፡ አንተም ብርሃን ሆይ፡ ውጣ!" መንፈስ ቅዱስ ህያው ነው። ይሁን ካለ በኋላ፡ ከኮረብታው ማዶ ሾልኮ የሚፈስ ነገር ይታየኛል፡ በጥቂቱ ካልሲየም ሲወጣ፡ ከፖታሽ ጋር ተቀላቅሎ ሲወጣ አየሁ። ምን ይዞ እየወጣ ነው? ትንሽዬ አደይ አበባ ከድንጋይ ንቃቃት በታች ስትወጣ ያያል። "ሕይወት፡ ወጣ!" "አባት ሆይ፡ ወደዚህ ናና፡ ይሄን ተመልከት።"

244 "አዎን በጣም ያምራል። መቀፍቀፍህ ቀጥል።" በዚህ መልኩ አበቦቹን ሁሉ ቀፈቀፈ፡ አትክልቶቹን ሁሉ አበቀለ። የእንስሳትን ሕይወት አወጣ። ወፎቹ ከአፈር ውስጥ በረሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወንድና ሴት ወጡ፡ ወንድ ወጣና፡ ወንዱም ራሱ ወንድና ሴት ነበረ። ሄርማፍሮዳይት ግን፡ አይደለም። ብቻ፡ በውስጡ፡ ሴታዊ መንፈስ ነበረበት።

245 በጣም ሴታሴት የሆነ ወንድ ካያችሁ፡ ምናልባት ጤነኛ፡ ደህና ሊሆን ይችላል፡ ቢሆንም ግን የሆነ ችግር አለ። አንድ ሴት ባለ ማንገቻ ቱታ ለብሳ፡ ጸጉሯን ለመቁረጥ፡ ወጥታ ካያችሁ፡ አያችሁ፡ "ጌታ ይባረክ፡ እላችኋለሁ!" የሆነ ችግር አለ። ሴት ሴታዊት መንፈስ አላት፣ ወንድም ደግሞ ወንዲላ ነው። እናውቃለን። እናንተም ታውቃላችሁ። እንደ ወንድ አክት የምታደርግ፡ ወንድ ለመምሰል የምትሞክር ሴት፡ ትክክል ትመሰላለችን?

246 የደን ጥበቃ ስራ በምሰራበት ጊዜ፡ አውቶቡሰ ውስጥ ተቀምጠን፡ ስንሄድ፡ አውቶቡስ ውስጥ አጠገቤ ያለችው ሴት እግሯን በእጄ እየመታሁ፡ እያወራኋት ስንሄድ አስታውሳለሁ፡ የብየዳ ቆብ አጥልቃ ነበር፡ ሴት መሆኗን አላወቅኩም። ፊቷ ላይ ትልቅ መነጽር **እንዲህ** አርጋለች፡ እኔም እንዲህ ብዬ፡ በዚህኛው በኩል ቁጭ ብያለሁ፡ የሆነ አንዴ ሰለደረገ ነገር እየተናገረች ነበረች። እና "ታውቃለህ" አለች፤ ሲጋራ እያጨሰች፡ ለማየት-በሚሰቀጥጥ ፊት፡ "ትናንት ማታ" እንዲህ እና እንዲህ ሆነ። እንዲህ ብላ ተናገረች፦ "ልንገራችሁ፡ ትላንትና ማታ፡ ሰውዬው፡ ከላይ ተንሸራትቶ ወረደና። ከላይ እየወረደ፡ 'ወይኔ!' ብሎ ጮኸ።" "በህይወቴ ይህን ያህል ሰቄ አላውቅም፡" አለች።

247 እኔም አብሬአት፡ **እንዲህ ብዬ**፡ በጣም እየሳቅኩ ነበር። ከዚያ "እንዴ፡ ይህች፡ ቁጭ ብላ ስታወራ የነበረች አይደለችም'ዴ? " ኧረ እሷ ናት አልኩ። ያንን ቆብ አውልቃ ጭንቅላትዋን ባትነቀንቅ ኖሮ፡ ባትጠራርግ ኖሮ፡ ሴት እንደሆነች ባላወቅኳት። በህይወቴ እንደዚያች ቀን አፍሬ አላውቅም። እንዴ—አንቺ "ሴት ነሽ እንዴ? " አልኳት፤

“አዎን፡ ምን ማለትህ ነው!” አለችኝ፤

248 “ይቅርታ አርጊልኝ፡” አልኳት። እኔ እንደዚህ አይቼ አላውቅም ነበር። የምላችሁ፡ ሁሉ፡ እውነት ነው።

249 ባለፈው ቀን ያየሁት ማስታወቂያ፡ በጣም ሲያስደንቀኝ። “ሴቶች ልብስ ለመልበስ ተዘጋጅቷል፡” የሚል ትልቅ ማስታወቂያ ተለጥፎበታል። እና “ጌታ ይባረክ፡” ብዬ አሰብኩ። እያችሁ? ታውቃላችሁ፡ ልብሱ ግን፡ አሁን በቅርብ ያዘጋጁላቸው፡ ተራ ልብስ እንደሆነ ዘግይቼ ተረዳሁት። እኔ የመሰለኝ—የምር ልብስ የሚያለብሷቸው መስሎኝ ነበር። እውነቴን ነው። “ሴቶች ልብስ ለመልበስ ተዘጋጅቷል፡” ይላል። “ጥሩ ነው። ስለ እነሱም እግዚአብሄር ይመስገን። በእውነት፡ ጌታን አመሰግናለሁ፡” አልኩ። እያችሁ፡ ልብሱ ግን፡ አሁን በቅርብ የሰሩላቸው፡ ተራ የሆነ ልብስ ነው። እዚህ ሀገር ውስጥ፡ እንደው፡ አስቂኝ ነገር መሆን አልነበረበትምን? እሺ እንመለስ።

250 ከዚያም አዳም በመጣ ጊዜ። አዳምም ብቻውን ነበር፡ ከጎኑም የጎድን አጥንት ወሰዶ፡ ሄዋንን ለእርሱ የፍጥረት-ምርት አደረገለት። ሴታዊውን መንፈስ፣ ጨዋ የሆነውን፣ ርህሩህ የሆነውን፣ ፍቅር የሆነውን፣ ሴትነትን መንፈስ ከአዳም አውጥቶ፡ በሴቲቱ ውስጥ አኑሮ... ሰራት። የወንድነት መንፈስንም በአዳም ውስጥ አስቀረው። ስለዚህ አሁን፡ ከዚህ የተለየ ነገር ከመጣ፡ የተጣመመ ነገር አለ ማለት ነው። ያኔም ሁለቱ አንድ ነበሩ፡ አሁንም ናቸው።

251 እስቲ ከመዝጋታችን በፊት ትንሽ ድራማ መሰል ነገር እንውሰድ። እና... እነሆ አዳም፡ ሄዋንን እጇን ይዞ ሽርሽር ይወጣሉ። ይሄ በጣም የምወደው ታሪክ ነው። እና እየተዝናኑ ሲሄዱ፡ ሄዋን፡ ታናግረዋለች። “የኔ፡ ፍቅር፡ ይሄኛው ስም አወጣህለት? ”

“አዎን፡ ሰይሜዋለሁ።”

“ማን አልከው? ”

“ፈረስ ይባላል። አህ-ኧ።”

“ያ ምንድነው? ”

“ላም ናት። አህ-ኧ።”

“ያንንስ ሰይመኸዋል? ”

“አዎ። አህ-ኧ።”

252 “እዚያ ተቀምጠው ጭንቅላታቸውን አንድ ላይ ያደረጉትስ፡ ማን ብለህ ጠራሃቸው? ”

“የፍቅር ወፎች ናቸው።”

253 “ኦህ፡ ገባኝ። ገባኝ።” እንደዚሁ ቀጠሉ። “ይሄኛውስ ማን አልከው? ”

“ይሄኛው፡ የሚጠራበት ስም፡ **እንዲህ** ነው።”

254 ኦህ፡ “አሁን፡ ገባኝ። አህ-ኧ። በጣም ያምራል።” ወድያው አንበሳ አገሳ። “ይሄስ ማን ነው? ”

“ያ አንበሳ ነው።”

“ምንደነው **ይሄ**? ”

“ነብር ነው።”

255 አዎን፡ ኦህ፡ ልክ፡ እንደ ድመት… “ኦህ፡ ገባኝ።” አየኸው፡ ሚያው እያለ ወረደ።

256 ትንሽ ቆይታ፡ ዙርያውን፡ ቃኘችና። “ውዴ፡ እያት’ማ፡ ጸሀይ እየጠለቀች ናት። የቸርች ጊዜ ደረሰ፡” አለችው።

ታውቃላችሁ፡ ፀሐይ ስትጠልቅ፡ አምልኮ እንዲያምራችሁ የሚያደግህ ነገር አላት። በዚያ ምሽት ቸርች ካልሄድኩ፡ ክፍል ውስጥ ገብቼ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እወዳለሁ። ወደ ራሳችሁ መመለስ፡ ስንቶች ደስ ይላችኋል? እያችሁ? የሰው ባህርይ ነው። ማድረግ አለባችሁ።

“የቸርች ጊዜ ነው።”

257 እያችሁ፡ በፍጹም ብለውት የማይውቁ ነገር፡ “ቆይ፡ እከሌ’ኮ፡ ጆንስ’ኮ፡ አሰምብሊስ ነው፡ እኛ ግን እንዲህ እና እንዲያ ነን… ” በፍጹም፡ ብለው አያውቁም፡ ዝም ብለው ሄዱ። ያኔ ምቹ ወንበር ያለበት ቸርችም፡ አልነበራቸውም። ወደ አንድ ትልቅ የጫካ ካቴድራል ስር ሄድው፡ ተንበረከኩ።

258 የእሳት አምድ መጥቶ በጫካዎቹ ራስ ላይ ይመላለሳል። እያችሁ? ድምጽ መጥቶ ሲናገራቸው ይሰማኛል፡ “ልጆቼ፡ ጌታ አምላካችሁ በምድር ላይ በሰጣችሁ ነገር፡ ዛሬ ተደሰታችኋልን? ”

259 “አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ እጅግ ሐሴት አድርገናል።” “አይደለም’ዴ፡ የኔ ውድ? ”

260 “አዎን። አዎን፡ ውዴ፡ በጣም ደስ ብሎናል።” “ጌታ ሆይ፡ በእውነት እናመሰግንሃለን። አሁን እንድተኛ ፍቀድልኝ።” እያችሁ? እናም ትልቅ ክንዱን ዘርግቶ፡ እሷም በክንዱ ላይ ተኛች፡ ነብሩንም አስተኝቶ አንበሳውንም አስተኝቷል። ነገር ሁሉ፡ በታላቅ ሰላም ጸጥ ብሎ አርፏል።

261 ስለዚህ እግዚአብሔር የገነትን ፍጥረት ሁሉ፡ ብዙ መላዕክትን፡ እነ ገብርኤልን ሁሉ ይዞ ወረደና። ዙርያ ዙርያቸውን እያዩ፡ ድምጽ ሳያሰሙ በጫፍ-እግራቸው እየረገጡ፡ ወደ መኝታ ክፍል መጡ። ገብርኤልም መጣና “አባቴ፡ ና። ጠጋ በል። እዚህ ናቸው። ልጆችህ፡ ደክሟቸው እዚህ ተኝቷል፡ እያቸው፡” አለው።

262 እናቶች የሆናችሁ፡ አባቶች የሆናችሁ እንዲሁ፡ አልጋው አጠገብ ቀርባችሁ፡ እየው’ማ ልጅህን፡ ኧረ ሚጣን ተመልከቻት፡ እየተባባላችሁ፡ “**እንዲህ** ሲል——**እንዲህ** ሲሆን፡ አንተን አይመስልም? ” ተባብላችሁ አታውቁም ወይ? እኔም፡ ብዙ ጊዜ ወደ ዮሴፍ ሄጄ፡ ሜዳን ብያት አውቃለሁ። እሷም “ቢል፡ ልክ እንዳተ ግንባራም ነው፡” ትለኛለች።

263 “አዎን። ሚዳ፡ አይኖቹ ግን፡ እንደ አንቺ ትልልቅ ናቸው።” እንዴት ሆኖ? ከትዳራችን——ከእኛ የተገኘ-… የአብራክ ክፋይ ስለሆነ።

264 አሁንም፡ አባት በዚህ ጉዳይ ላይ፡ ስለ እኛ መመስከር ይችላል። ምክንያቱ፡ ገብርኤል ሲናገር፡ “እንደሰማችሁት… ” “ቁርጥ አንተን፡ ይመስላል ብሏልና።” እራሳችሁን ተመልከቱ፡ አምላክ የሚመስለው እናንተን ነው። የአምላክ ምስል እናንተ ናችሁ። የአብራኩ ክፋይ ናችሁ። ቁርጥ እናንተን ይመስላል። ይህን ስንቶች ታውቁታላችሁ? እያችሁ?

265 አሁን ተከታተሉኝ። በጣም ዝቅተኛው የህይወት ዝርያ ምንድነው? እንቁራሪት ከፍተኛው የሕይወት ዝርያስ ምንድን ነው? ሰው። በትክክል። ከፍተኛው ዝርያ ምንድነው? ከዝቅተኛው ጀምሮ፡ ወደ ላይ፡ ከእንቁራሪት ወደዚህ **ከዚህም** ወደዚያ፡ **ከዚያም** ወደ አእዋፋት፡ ወዘተ፡ በመቀጠል፡ አለ ወደሚባለው፡ ወደ ከፍተኛው የሕይወት ህልውና ደርሶ፡ በእግዚአብሔር መልክ እስኪገለጥ ድረስ ይቀጥላል። ይሄ ነው። ሴት ግን በወንድ መልክ እንጂ፡ በእግዚአብሔር መልክ አልተፈጠረችም። እያችሁ?

አሁን እነሱ፡ አሁን፡ እንዲህ ናቸው። እግዚአብሔርም አያቸውና፡ "በጣም፡ ዉብ—በጣም የሚያምሩ ናቸው፡" አለ።

266 ምን ነበር፡ ወንድሜ? የማይሞቱ ነበሩ። የመጀመርያዎቹ እፍኝ ካልሺየም፣ የመጀመርያ ፖታሽ፣ እና የሁሉም ጅማሬ እነዚህ ነበሩ። አያምርም? ነገር ግን ኃጢአት መጥቶ ምስሉን አበላሸው። እግዚአብሔር... ከትንሽ ጊዜ በፊት እንደተነጋገርነው፡ ምን እንዲያደርግ ይህን ፈቀደው? ሐጥያት እንዲኖር ለምን ፈቀደ? አዳኝ መሆኑን እንዲያረጋግጥ ስለፈለገ ፈቀደ። እራሱ አደረገው። ፈዋሽ መሆኑን ማረጋገጥ ይችል ዘንድ በሽታ እንዲፈጠር ፈቀደ። እርሱ ሕይወት መሆኑን ለማረጋገጥ ሞትን ፈቀደ። አስተውል? እሱ ማንነቱን ለመግለጽ፡ ቸር መሆኑን እንዲታወቅ፡ እነዚህ ሁሉ መጥፎ ነገሮች እንዲፈጠሩ ፈቀደ። እኛም...

267 የቤዛነት ስራ ስለመዘመር እንናገር የለም'ዴ! ለምን፡ ወንድሜ፡ ኢየሱስ ሲመጣ፡ ቤተ ክርስቲያን በምድር—ዳርቻዎች ላይ ትቆማለች የቤዛነት ስራን መዝሙር ትዘምራለች፡ የምንናገረው ነገር መላእክት ምን መሆኑን ሳይረዱት፡ ጎንበስ ብለው ይሰግዱላታል እያልን እንዘምራለን። አዎን፡ ወድቀትን እያውቁትምና። እኛ የምናልፍበት መከራ አይገባቸውም። እኛ ግን መውደቅ እና መዳን ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቀን እናውቃለን። ለእነሱ አዳኝ አይደለም። አቤት፡ ስለ ክብሩ እልል በሉ! መዳን በፍጹም አያስፈልጋቸውም። ለእነርሱ ፈዋሽ አይደለም። አይደለም። ክብር ይሁን! እሱ ለመላእክት—ሕይወት አይደለም። በኃጢአትና በበደል ፈጽመው አልሞቱምና። በፍጹም አይደለም። እኛ ግን ሙታን ነበርን፡ ህያዋን አደረገን። እንዲሁ ነው። አክሊሎቻችን እያወጣን፡ ምን እንለዋለን፡ "ኦህ፡ ሬቨረንድ፡ **አከሌ-እና-አከሌ** ነህ እንላለን"? አይ፣ አይ፣ አይ፣ አይ፣ አይ። ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን! በቃ። ይህ ነው። እኛ እንዴት ድል እንደነሳን ያኔ እንናገራለን። ያኔ በተሻለ ሁኔታ እንረዳዋለን።

268 እሺ፡ ከዚያ በኋላስ፡ ምን ተፈጠረ? እግዚአብሄርስ እንዲህ አለን፦ "በቃ፡ ካልሲየሜ እና ፖታሼ ሁሉ ስለ ተበላሸ። እኔም ላጥፋው አለን"? በፍጹም፡ አላለም። እንደዚያ እንደሚሆን አስቀድሞ ያውቀዋል።

አሁን፣ መንፈስ ቅዱስ እኔን አርጎ ከሰራኝ፡ ምግብም በልቼ ወደ ሰውነቴ ገብቶ፣ አሁን ያለሁትን እንድሆን አድርጎ ከፈጠረኝ። ነገር፡ ግን፡ በአንድ ቅርጽ መሰረት ሰርቶኛል። እግዚአብሄር ዓለም ሳይፈጥር ፍጥረት በፊት፡ ባየው ምሳሌ መሰረት፡ እያደግኩ፡ ቅርጽ አሰይዞኛል። እያችሁ? እንደ ተናገረ፡ ከሴት ተወለድን፡ በሚቀጥለው ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተወለድን። ያኔ፡ ከሴት ነበርን፡ አሁን ግን፡ ከወንድ ነን። እያችሁ? ያኔ፡ በፍትወት ምኞት ተወለድን፤ አሁን ግን በተነገረው በእግዚአብሄር ቃል ተወለድን። እያችሁ?

269 እሺ፡ ከዚህ፡ የሚለየኝ ነገር አለን? በፍጹም፡ አይኖርም። ሊለየን የሚችል አንዳች ነገር የለም። ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ “በሽታ፣ ወይስ ሞት ነውን፣ ያለውም፣ የሚመጣውም ቢሆን፣ በክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ምንም ሊለየን አይችልም ብሏል።” ሊለየን የሚችል ነገር የለም።

270 ከዚህ በፊት እንደነገርኳችሁ ታሪክ። እኔ አምስት ፀጉሮች ብቻ የቀሩኝ፡ ሙሉ በሙሉ ራሰ በራ የሆንኩ ሰው ነኝ። እና አንድ ቀን ጥቂት ጸጉሬን እያበጠርኩ፡ ባለቤቴ መጣችና “ቢሊ፣ ራስ በራ ልትሆን ነው፡” አለችኝ።

እኔም “ከጸጉሬ አንዲት የጠፋች ጸጉር ግን የለችም፡” ብዬ መለስኩላት።

“ታድያ የት ናቸው? ” ጠየቀችኝ፤

271 እኔም “የእኔ ከመሆናቸው በፊት የት ነበሩ? ” አልኳት፤ አያችሁ? “የእኔ ከመሆናቸው በፊት በነበሩበት አሉ።”

ስለዚህ፡ ከአንድ መቶ አመታት በፊት፡ እነዚህ ጸጉሮች፡ በምድር አፈር ውስጥ እንጂ፡ በፍጹም እዚህ ያልበሩበት ጊዜ ነበረ። ልክ ነው? ከሃምሳ አመታት በፊት ግን፡ ጭንቅላቴ ላይ መውጣት ጀመሩ። ከየት ነው የመጡት? ከአፈር ውስጥ። አሁንም ወደነበሩበት ይመለሳሉ። ልክ ነው? ድሮ ያልነበሩ፣ በኋላ ግን የነበሩ፣ አሁን እንደገና የሌሉ ናቸው። የሆኑትን እንዲሆኑ ያደረጋቸው ማን ነው? ምንድን ነው? እግዚአብሄር! እርሱ ነው። ሰዕልን ሰሎ፡ “እንዲህ እንዲሆን እፈልጋለሁ፡” አለ።

272 “ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? መቃብር ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ? ” ከዕለታት አንድ ቀን ልትቀብሩኝ ትችላላችሁ። እኔ አላውቅም። ነገር ግን፡ ወንድሜ ሆይ፡ እኔ አልሞትም። ደግሜ እላችኋለሁ። አልሞትም፡ ወንድሜ። ኦህ!

እንነሳለን፡ (ሃሌ ሉያ!)
እንነሳለን!
በትንሣኤው ማለዳ፡
የሞት መዝጊያዎች ሲሰበሩ፣
እንነሳለን፡ (ሃሌ ሉያ!) እንነሳለን።

ከመነሳት የሚያግደኝ ምንም ነገር የለም። በገሃነም ሁሉ ውስጥ እኔን ከትንሳኤ ሊከለክሉኝ ብቃት ያላቸው ሰይጣኖች የሉም። እንዳልነሳ የሚከለክለኝ ምንም በቂ ነገር የለም። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አለኝ። መንፈስ ቅዱስ አለኝ። ዞዊ የሆነውን፡ የእግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት፡ በዚያ ሞልቷል። ይህ አሮጌ ሬሳ ከአፈር የመጣ ነው፣ እግዚአብሔር ከመሬት ፈለፈለኝ። ከምድርም የፈለፈለኝ እንደ ሆነ...

273 አሁን በዚህ ሽምግልናዬ፡ አሁን፡ የቤተ ክርስቲያን ደወል በሰማሁ ቁጥር፡ አንተ ህጻን ልጅ፡ የሚለኝ ነገር ይሰምኛል። አንድ መልአክ ከቁጥቋጦው ተናገረ፡ እንዲህም አለኝ፦ “በአንተ የምሠራው ሥራ አለኝ። ፈጽመህ አትጠጣ፣ አታጭስ። ሰውነትህን አታርክስ፣ ወይም ሴቶች እና ነገሮች አትፈልጋቸው። አንተ ስታድግ፡ የምትሰራው ነገር አዘጋጅቼልሃለሁ።”

“ማነህ? ማነህ? ”

274 “ጊዜው ሲደርስ በበለጠ ታውቀኛለህ።” ጊዜው ሲደርስም፡ እነሆ አሁን ተገለጠ። ያኔ በማጥመቂያው አጠገብ መጥቶ ቆመ። ራሱን አሳየ። እራሱንም

ገለጠ። መልሰ ሰጥቷል። አሁን በሁሉም ቦታ በሁሉም አቅጣጫ፡ ቆሞ አየዋለሁ።

275 የእኔ ምርጫ ሳይኖርበት... እኔ አሁን እኔ እንድሆን ማድረግ እንዴት ተቻለው? እኔ ራሴ ሄጄ “ቻርሊ ብራንሃም፡ ሂድና፡ ኤላ ሃርቬይን አግብተህ እኔን ከምድር አውጣኝ፡” ብዬ አልጠየኩትም። በጭራሽ፡ አልጠየኩም። እንዲህ አይነቱ ምርጫም አልነበረኝም። ይሄን ያደረገ ግን እግዚአብሄር ነው።

ያለ ምርጫዬ፡ እኔ እንድሆን ካደረገኝ፡ ይልቅሰ ያ መንፈሰ ቅዱሰ በእኔ ላይ በመጣ ጊዜ፡ እንዴት አብልጦ አይፈለፍለኝም፤ እኔም “አዎን፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ ፈጣሪዬ ነህ። እወድሃለሁ፣ እንደ አዳኜም እቀበልሃለሁ!” እለዋለሁ፤ አፈር ላይ እኔን እንዴት ልትይዝ ይቻልሃል? አትችልም፡ ወንድሜ። ልትይዘኝ አትችልም።

276 እግዚአብሔር ከካልሲየሙም፣ ወይም ከፖታሹም፣ ወይም ከሌላው ነገር፣ ቅንጣት ያክል ይጠፋ ዘንድ—አልፈጠረውም። “ዓለም ሳይፈጠር፡ አብ የሰጠኝ ሁሉ፡ ወደ እኔ ይመጣል።” ዋው! ጩኸ ጩኸ አለኝ፡ በእውነት። “አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡ አንዳቸውም አይጠፉም፡ በትንሣኤ ግን ደግሜ አነሣዋለሁ።” ወደ እርሱ ሰመጣ፡ ሲጠራ ሰምቻለሁ። በምድር ትቢያ ውሰጥ እኔን መያዝ እንዴት ይቻላቸዋል? እኔን በምድር ትቢያ ውሰጥ ቀብረው ለማሰቀረት የሚችል አቅም ያላቸው፡ አካሏ የያዙ በቂ ቀባሪዎች ሊኖሩ አይችሉም። አንድ ቀን በደሙ ታጥቤ፡ ከመንፈሱ ተወልጄ፡ በእርሱ አምሳያ ለመቆም እነሳሉ! ሃሌ ሉያ! የሐይማኖት ተቋማትን ለራሳችሁ ውሰዷቸው፡ ለእኔ ግን ኢየሱሰ ይሻለኛል። አሜን!

277 ዊልመር ሰናይደር የመድን ድርጅት ሰራተኛው፡ የቅርብ ወዳጄ ነው። እና አንድ ቀን መጣና። “ቢሊ፡ መድን ፖሊሲ እሸጥልሃለሁ ግዛኝ፡” አለኝ።

278 “ቀድሜህ ገዝቻለሁ፡” ብዬ መለሰኩለት። (ሚሰቴም፡ ዞር ብላ አየችኝና “ሰውዬው፡ ለምን ትዋሻለህ? ”) የምትል ትመሰላለች፤

“መድን ገዝተሀል´ዴ? ” አለኝ፤

“አዎን፡ ገዝቻለሁ፡” አልኩት።

“ከየትኛው ኩባንያ? ማን ይባላል? ” ጠየቀኝ፤

279 እንዲህ አልኩት፦ “ኢየሱሰ የእኔ ነው፣ ኦህ፣ መልካም ተሰፋ፤ መለኮታዊው ክብሩ ይሰፋ! የህይወት ወራሽ፡ ልንሆን ገዛን፡ በመንፈሱና፡ በደሙ አጥቦን።”

280 “ቢሊ፡ ጥሩ ነገር ነው፡ ቢሆንም ቀብርህን አያሰፈጽምልህም፡” አለኝ።

281 “ከመቃብር ያሰወጣኛል፡” አልኩት። ሃሌ ሉያ! ከመቃብር እንዴት ልውጣ እንጂ፡ እንዴት ልግባ አያሰጨንቀኝም።

282 ሰለዚህ፦ “አብ የሰጠኝ ሁሉ የእኔ ነው፡ እኔም አሰነሳዋለሁ።” ብሎ የነገረኝ መድን አለኝ። አባቴ ምን ሰራ፣ እናቴ ምን አደረገች፣ ሌላው ሁሉ እንዴት ነበር አያሰጨንቀኝም። “አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡ አባቴም ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም።” ሃሌ ሉያ! ለምን ይሰባቸዋል? “ዓለም ሳይፈጠር አሰቀድሜ አውቃቸዋለሁ። በጉን ባረድሁት ጊዜ፡ ከእርሱ ጋር አርጃቸዋለሁ።” ኣሜን። “ቤተክርሰቲያንን አሰቀድሜ ወሰኛታለሁ።” ማንን አሰቀድሞ ወሰነ? ቤተ ክርሰቲያንን። ወደ ቤተክርሰቲያን እንዴት ይገባል? “በአንድ መንፈሰ ሁላችንም አንድ አካል ለመሆን በተቀበልነው

ጥምቀት።” እኛ በአካሉ ውስጥ እንደምንሆን፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ያውቅ ነበር። “አስቀድሞ ያወቃቸው እነዚህን ደግሞ፡ ጠራቸው። የጠራቸው እነዚህን ደግሞ፡ አጸደቃቸው። ያጸደቃቸው እነዚህን ደግሞ፡ አከበራቸው።”

283 በእግዚአብሔር መጻሕፍት ውስጥ፣ እዚያው አገኛሃለሁ ብሎ ነግሮኛል። እግዚአብሄር አስቀድሞ ተናግሯልና እነሱን ከመቃብር ውስጥ እንዳይወጡ አስሮ ሊያስቀር የሚችል አቅም ያለው፡ ሊከለክላቸው የሚችል ሰይጣን የለም፡ በቃ አከተመ። ከመቶ ቢሊዮን ዓመታት በፊት ገና ዓለም ሳይፈጠር በፊት፣ የንጋት ከዋክብት አብረው ሲዘመሩ፣ የእግዚአብሔር ልጆችም ዓለም ሳይፈጠር በፊት በደስታ እልል ሲሉ፣ እያችሁ፡ ገና መሰረት ሳይጣል-... ገና ዓለም ሳይፈጠር፡ መሰረት ሳይጣል፡ መላእክት ሁሉ በደስታ እልል ካሉ፡ ዲያብሎስ በምድር ትቢያ ውስጥ እንዴት ይይዘኛል? ፈጽሞ አይችልም። ትክክል።

284 አሁን፡ እንከታተል። እኔ ጋር፡ በዲሞክራቶች ሰዓት አቆጣጠር ነው። ሀያ ጉዳይ ለአስራ አንድ ይላል። ሃያ ጉዳይ ለአስር ማለት ነው። ልክ ነው፡ ወንድም ዉድ? አዎን፡ ሃያ ጉዳይ ለአስር ነው። ደስተኞች ናችሁ ሁላችሁ?

ኦህ፡ ተጓዝ ሂድ ይለኛል፡
ተጓዝ ሂድ ይለኛል፡
የሰማይ ቤቴ ብሩህ እና ውብ ናት፣
ተጓዝ ሂድ ይለኛል፡

ኦህ፡ ተጓዝ ሂድ ይለኛል፡
ተጓዝ ሂድ ይለኛል፡
የሰማይ ቤቴ ብሩህ እና ውብ ናት፣
ስለዚህ ተጓዝ ሂድ ይለኛል፡

285 የጥንት መዝሙሮቹን ትወዳላችሁ? ድሮ የምንዘምራት የቆየች መዝሙር አለች፡ እንዲህ ነበረች፡- “የንጋት ኮከብ አበራብኝ። ጸጋው እና ምሕረቱም አገኙኝ።” እንዲህ ነው፡ እህት ገርቲ? እንሰማት እስቲ። እንዴት... ነበር፡ ወንድም ኔቪል? “ጸጋው እና ምሕረቱም አገኙኝ። ደማቁ የንጋት ኮከብ... ? ... በዙርያዬ ምን ሲል።” ኧ-ሀ። አዎን። “መሰቀሉ ስር።” **በመሰቀሉ ጥግ**፡ ኮርድ፡ ሰጪን፡ እህታችን። ወደዚህ ና ወንድም ኔቪል። መንፈስን የሚያነቁ የድሮ መዝሙሮችን ስንቶቻችሁ ትወዳላችሁ? ኦህ፡ እነዚህን እወዳቸዋለሁ። የፈለጋችሁትን ዝላይ-ወደ-ታች-ወደላይ እና ቡጊ-ዉጊ ለራሳችሁ ውሰዱ። ለእኔ ግን ይሄን ሰጡኝ፡- “ጸጋው እና ምሕረቱ ያገኘኝ እዚህ ነው።” በቃ። በጣም በጥሩ ሁኔታ፡ እንዘምረው።

ኢየሱስ፡ ከመስቀሉ ጥግ፡
ከድንቁ ፏፏተው ጠበቀኝ፡
የፈውስ ምንጭ፡ ለሁሉ ተገልጧል፡
ከቀራንዮ በነጻ አፍሰሶልኝ።

በመስቀል ስር፡ በመስቀል ስር፡
ክብሬ ሁን ለዘላለም፡
ነፍሴ በንጥቀት እስክታገኝ
እረፍት ከወንዙ ባሻገር።

286 [ወንድም ብራንሃም **በመስቀል ጥግ** እያለ አንጎራጎረ—አርታዒ።] ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! እስቲ አስቡት! እዳኛ ባይኖርስ? ይህ ቃል ባይኖረንስ? እሱ ባይጠራችሁስ? አስቀድሞ ባያውቃችሁ ኖሮ፣ በዛሬው ምሽት በዓለም ውስጥ ብትሆኑ ኖሮስ? ትወዱታላችሁ ወይ? ኦህ፡ ማይ! የነገ ጉባኤ እንዳትረሱ፡ ጠዋት፡ ዘጠኝ ሰዓት-ተኩል ነው።

በመስቀል ስር፡ በመስቀል ስር፡
ክብሬ ሁን ለዘላለም፡
ነፍሴ በንጥቀት እስክታገኝ
እረፍት ከወንዙ ባሻገር...

287 ሌላ ቆንጆ የቆየ መዝሙር **ከምንጩ ስር ቤት አለ፡** እስቲ የምንዘምርበት ኮርድ ስጪን። "ከምንጩ ስር ቤት አለ።" ስንቶች ታውቁታላችሁ? "ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት፡ ከምንጩ ዘንድ ቤት አለ።" አሁን ስትዘምሩት፡ ጎናችሁ ያለውን ወንድም፡ እጁን እየጨበጣችሁ፡ በእርጋታ ዘምሩት። ይሄውላችሁ፤ ለሜቶዲስቶች ሁሉ በቂ ቦታ አለ። ለባፕቲስቶች ቦታ አለ። ጴንጤቆስጣሎች የሚሆን ቦታ አለ። ከምንጩ ስር፡ ለሁላችንም የሚበቃ ቤት አለ። የጥንቱን መዝሙር ስንቶች ታውቁታላችሁ? ኦህ፡ አዎን ታውቁታላችሁ። አንዳንድ አንጋፋ-ለሆናችሁ ሰዎች፡ መዝሙሩ፡ የድሮ የኬንታኪ መዝሙር ነው።

ቤት፡ ቤት...

እጅ ተጨባበጡ።

... አዎን፡ ቤት አለች፡
በምንጩ ላይ ቤት አለ፤
ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት አለች፤
በምንጩ ላይ ለአንተም ቤት አለ።

ኦህ፡ ቤት፡ ቤት፡ ብዙ ቤቶች አሉ፡
በምንጩ ላይ ለአንቺም ቤት አለ፤
ኦህ፡ ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት አለ፤
በምንጩ ላይ ለእናንተም ቤት አለ።

288 አሁን፡ ለሁላችሁም የሚሆን ሰርፕራይዝ አለኝ። በሚቀጥለው ሳምንት በሚኖረን ጉባኤ፡ በቅርብ ጊዜ የተሰበኩ ስብከቶች፣ እና መጽሐፍቶች ሁሉ፣ ቴፖች እና፡ በጥሩ ስነ ጽሑፍ የተፃፉ ነገሮች ሁሉ፡ በቤተክርስቲያን፡ ሌላኛው ጥግ ላይ፡ በሽያጭ ይውላሉ። ከበስተጀርባ ባሉ ክፍሎች በአንዱ በአንዱ ክፍል ጠረጴዛ ይዘጋጃል። በቅርብ የተሰበኩ ሰብከቶችን፡ እና ስነ ጽሁፎችን፡ እና አስቀድሞ የወጡ ጥሩ ጽሑፎች ጭምር፡ በአዲስ መጽሐፍ፡ በአዲስ እትም፡ ተዘጋጅተው—በሚቀጥለው እሮብ ማታ፡ በህንጻው ጥግ ላይ፡ ይቀርባሉ።

ጌታ ጥሩ ግዜ እንዲያደርግልን—እንጠብቃለን። እናንተም፡ መጥታችሁ፡ ጸልዩ። የታመመና፡ የተጎዳ ወዳጅ ዘመድ ካላችሁ፡ ደብዳቤ ጽፋችሁ ጥሯቸው። አምጧቸው። በተጨማሪ... እግዚያብሔር በታላቅ ፀጋው ይሰራል። አሁንም እንደሚሠራ እናውቃለን።

289 እንደምታስታውሱት፡ ከዚህ ቀደም ነግሬአችኋለሁ። ያልተስተካከሉ ነገሮችን፡ እና አንዳንድ ያልተፈቱ ነገሮች፡ ከመንገድ ያፈነገጠ ሁሉ ለማረም ወደየ ሰዉ ቤት ሁሉ ዙርያለሁ። አሁን ያለው መንፈስ ያኔ ከነበረው መንፈስ

የተለየ መንፈስ መሆኑን መረዳታችሁ አውቄአለሁ። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ? ትክክል። ከአሁን በኋላ፡ መንፈሱን አታሰባርሩ። በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እምላችኋለሁ፡ አታሰኪዱት። አብራችሁ ቆዩ፡ የተጩማደደ ነገር ሁሉ አስተካክላችሁ መንገዳችሁን ቀጥሉ፡ እሺ። ወንድማማች ናችሁ። የዲያብሎስ መንፈስ ገብቶ ስለሚያውካችሁ እንጂ፡ ስህተቱ የስራው እህታችሁ ወይም ወንድማችሁ አይደለም። አያችሁ፡ ክፉው ይዞራል። ከዚያ በወንድም ወይም በእህት ላይ ቂም ትይዛላችሁ፡ ስለዚህ ሰይጣን መሆኑን እወቁ። ስለዚህ፡ በወንድማችሁ የተለየ ስሜት ከተሰማችሁ፡ ሳይበላችሁ፡ በፍጥነት አስወግዱት። አዎን፡ ይባላችኋል። ስለዚህ፡ ከሱ ራቁ። ይሄን አትርሱ።

ቤት አለ፡ ቤት፡ ብዙ ቤቶች፡ አሉ፡

ለሜቶዲስቶች ቤት አለ፣ ለባፕቲስቶች ቤት አለ፣ ለፕሬስባይቴሪያን ቤት አለ። ለሁሉም ቦታ አለ።

ቤት፡ ቤት፡ አዎን፡ ቤት አለች፤
በምንጩ ላይ ለአንተም ቤት አለ።

290 የድሮ፡ የሽኻት መዝሙራችን ሰንቶች ታስታውሱታላችሁ?

የኢየሱስ ስም አብሯችሁ ይሁን፣
የዋይታና የሐዘን ልጆች፡
ደስታ እና ምቾት ይገላችኋል፣
በሄዳችሁበት አትለዩት።

ወንድም ጄፍሬስ፡ አንተ እና እህት ጄፍሬስ፡እዚያ ያሉ ልጆች ሁላችሁ፡ እና ሁሉም ከእኛ ጋር ብትቆዩ፡ እመኛለሁ።

ለኢየሱስ ስም ሰገዱ፣
ከእግሩ ስር ውደቁ፡ (ኦህ፡ ማይ!)
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

የኢየሱስ ስም አብሯችሁ ይሁን፣
ዛሬ ጋሻችሁ አርጉት፡
አቤት፡ ፈተና ሲቃረብ፡
በጸሎት ያን ቅዱስ ስም ተንፍሱ።

ኦህ፡ ድንቁ የኢየሱስ ስም! በጣም ደስ ይለኛል። እናንተስ አይላችሁም? አሁን፡ መዝሙሩን እየዘመርን፡ ሁላችንም እንነሳለን። በጣም ጥሩ።

የኢየሱስ ስም አብሯችሁ ይሁን፣
የዋይታና የሐዘን ልጆች፡
ይደግፋችኋል… (… ? … )

… ኦህ ግሩም ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም (ኦህ፣ ውብ ስም!) ኦህ ግሩም ነው!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

291 ይህ አሁን ትንሽ የተለየ ነው። አሁን አንገታችንን እናጎንበስ፡ እና፡ በጸጥታ፡ አንድ እጃችንን አንስተን፡ እንዘምራለን፡

ለኢየሱስ ስም ሰገዱ፣
ከእግሩ ሰር ውደቁ፡
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

ድንቅ ስም፣ ኦህ ግሩም ነው!
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ፡
አዎን፡ ድንቅ ስም፡ ኦህ ግሩም ነው!
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ።

292 ጭንቅላታችን እንዳቀረቅርን፡ እንዲህ እንላለን… [ወንድም ብራንሃም **የኢየሱስ ስም አብሯችሁ ይሁን** አንጎራጎረ—አርታዒ።]

**የሐይማኖት ተቋም ያልሆንነው ለምንድን ነው?** AMH58-0927

(Why Are We Not A Denomination? )

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ መሰከረም 27፡ 1958፡ ቅዳሜ ማታ፡ በዩ/ኤስ/ኤ/ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ ከሚገኘው ብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org